# ኢፕድ አዲስ ዘመን

ሰኞ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 077 ኅዳር 17 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ:-በረከት ታደሰ

## በቀን 10 ሺህ ቶን ሲሚንቶ የሚያመርተው የለሚ ፋብሪካ ግንባታ በመጋቢት ወር ይጠናቀቃል

ገጽ 4

## «የከተማዋ አስተዳደር የኑሮ ውድነቱን ለማቃለል በዓመት ስምንት ቢሊዮን ብር ድጎማ እያደረገ ነው»

- ከንቲባ አዳነች አቤቤ



ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- የከተማዋ አስተዳደር የኑሮ ውድነቱን ለማቃለል በዓመት ስምንት ቢሊዮን ብር ድጎማ እያደረገ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ አስታወቁ።

ሦስተኛው የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ሦስተኛ ዓመት የሥራ ዘመን አንደኛ መደበኛ ጉባዔውን ሰሞኑን ሲያካሂድ ከምክር ቤቱ አባላት ለተነሱ ጥያቄዎች ከንቲባ አዳነች አቤቤ ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል።

በወቅቱ ከንቲባዋ እንደገለፁት፤ የከተማዋ አስተዳደር በመዲናዋ የሚስተዋለውን ከፍተኛ የኑሮ ውድነት ለማቃለል ለሚያግዙ የተለያዩ ሥራዎች በየዓመቱ ስምንት ቢሊዮን ብር ድጎማ ያደርጋል።

የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት የግብርና ምርቶችንና የመሠረታዊ ፍጆታ ዕቃዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለኅብረተሰቡ እየቀረበ መሆኑን ተናግረዋል።

«የከተማዋ አስተዳደር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## የሀሮማያ ሐይቅ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት ሊጀመር ነው

ገጽ 4

## ለሙስና ሊውል የነበረ ከዘጠኝ ቢሊዮን ብር በላይ ከምዝበራ ማዳን ተችሏል

-ከ829 ሚሊዮን ብር በላይ በሙስና የተገኘ ገንዘብ ተመላሽ ተደርጓል

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- ባለፉት አራት ዓመታት በኢትዮጵያ ሙስናን ለመከላከል በተሠራ የቅድመ መከላከል ሥራ ከዘጠኝ ቢሊዮን ብር በላይ ከምዝበራ ማዳን መቻሉን የፌዴራል ሥነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን አስታወቀ፡ ፡ከ829 ሚሊዮን ብር በላይ በሙስና የተገኘ ገንዘብ ተመላሽ መደረጉ ተጠቅሷል፡፡

ለሙስና ሊውል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል
















# በመዲናዋ በሦስት ወራት ውስጥ 106 ሰዎች በትራፊክ አደጋ ሕይወታቸውን አጥተዋል

**ዳግማዊት አበበ**



አዲስ አበባ፡- በ2016 ዓ.ም የመጀመሪያው ሩብ ዓመት 106 ሰዎች በትራፊክ አደጋ ሕይወታቸውን ማጣታቸውን የአዲስ አበባ ፖሊስ ትራፊክ ቁጥጥር መምሪያ አስታወቀ፡፡ከ541 ሺህ በላይ የደንብ ተላላፊዎች ላይ ርምጃ መወሰዱም ተጠቁሟል፡፡

በአዲስ አበባ ፖሊስ ትራፊክ ቁጥጥር መምሪያ ትራፊክ ሙያና የሕዝብ ግንዛቤ ዲቪዥን ኃላፊ ኢንስፔክተር ሰለሞን አዳነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መምሪያው በመዲናዋ የተሳለጠ የትራፊክ እንቅስቃሴ እንዲኖር ሰፊ ሥራ እየተሠራ ቢሆንም በመጀመሪያው ሩብ ዓመት በትራፊክ አደጋ የ106 ሰዎች ሞት ተመዝግቧል፡፡

በሩብ ዓመቱ 494 ከባድና 385 ቀላል የአካል ጉዳት ተመዝግቧል ያሉት ኃላፊው፤ ስምንት ሺህ 253 የንብረት አደጋም ደርሷል ብለዋል፡፡

ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ ጋር ሲነፃፀር የሞትና ከባድ የአካል ጉዳት መጠን መቀነሱን አስረድተው፤ ቀላል የአካል ጉዳት እና የንብረት አደጋ ደግሞ ጭማሪ ማሳየቱን ተናግረዋል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ የትራፊክ አደጋውን ለመከላከል ከሚሠሩ ሥራዎች ዋነኛው የትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች ላይ ቁጥጥርና የሕግ ማስከበር ሥራዎች ናቸው፡፡

በሩብ ዓመቱም የትራፊክ ፖሊስ ተደራሽ በሆነባቸው ቦታዎች ብቻ 541 ሺህ 420 ደንብ ተላላፊዎች ላይ ርምጃ ተወስዷል ብለዋል፡፡

ከደንብ ጥሰቱ ሰፊውን ድርሻ የሚወስደው በትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ላይ የሚስተዋለው ትርፍ የመጫን ችግር ነው ያሉት ኃላፊው፤ የትራፊክ መብራት መጣስ፣ የደህንነት ቀበቶ አለማሰር፣ ሕጋዊ የመንጃ ፍቃድ ሳይዙ ማሽከርከር የሚጠቀሱ የደንብ ጥሰቶች መሆናቸውን አስረድተዋል።

ተቋሙ በተለይም የትራፊክ ማመላከቻዎችን የመትከልና የማደስ ሥራዎች ላይ ከአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ጋር በየጊዜው በመነጋገር በቅንጅት ሰፊ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቁመዋል።

አደጋዎችንና የደንብ ጥሰቶችን ለመቀነስ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ለትራፊክ ተጋላጭ ናቸው ተብለው የሚታሰቡ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ የግንዛቤ ሥራዎች መሠራታቸውን ኃላፊው ገልጸዋል፡፡

በ166 ትምህርት ቤቶች ላይ በመገኘት ለ149 ሺህ 684 ተማሪዎች፣ መምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች ስለትራፊክ ደህንነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎችን መስጠት ተችሏል ብለዋል፡፡

ለሕዝብ ትራንስፖርት አሽከርካሪዎች፣ ለሞተር ሳይክል አሽከርካሪዎች ደግሞ የተለያዩ የግንዛቤ ፈጠራ መድረኮችን በማዘጋጀት ሥልጠናዎች እየተሰጡ እንደሚገኙ አመላክተዋል፡፡

በከተማዋ ያለውን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ ብሎም ለመከላከል አንድ ተቋም ብቻውን የሚሠራው ሥራ የተሟላ ስለማይሆን፤ ሁሉም ሰው ከእኔ ምን ይጠበቃል? የሚለውን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሊንቀሳቀስ ይገባል ሲሉ ኢንስፔክተር ሰለሞን መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

# ከውጭ የሚገባውን የብቅል ገብስ ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ መተካት ተችሏል

**ሞገስ ጸጋዬ**



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ለቢራ ፋብሪካዎች ግብዓት ከውጭ ሀገራት ታስገባ የነበረውን የብቅል ገብስ ሙሉ ለሙሉ በሀገር ውስጥ ምርት መተካት መቻሉን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ፡፡

በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የትራንስፎርሜሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ፍጹም ከተማ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ለቢራ ፋብሪካዎች ግብዓት ከውጭ ሀገራት ስታስገባ የነበረው የብቅል ገብስ አሁን ላይ ሙሉ ለሙሉ በሀገር ውስጥ እየተዘጋጀ ይገኛል።

በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ የቢራ ብቅል የሚያመርት ኩባንያ ከ60 ሺህ በላይ ለሚሆኑ አርሶ አደሮች በቀጥታ ትስስር በመፍጠር ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል ብለዋል፡፡

በደብረ ብርሃንና በጅማ የግብርና ማቀነባበሪያ ትስስር እየተፈጠረ መሆኑን ጠቁመው፤ በሌሎች ዘርፎችም ትስስሮችን በማጠናከር ግብርናውን ለማሳደግ እየተሠራ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ከአኅዋ መታገድ ጋር በተያያዘ በርካታ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የምርታቸውን ዓይነታቸውን አስፍተዋል ያሉት አቶ ፍጹም፤ ቀደም ሲል በስፋት ያመርቱት የነበረውን የጨርቃጨርቅ ምርት ላይ የተለያዩ ምርቶችን በመጨመር ወደውጭ የሚልኩ በርካታ አምራቾች መኖራቸውን ጠቁመዋል።

በተለይ የተሽከርካሪ መገጣጠሚያ፣ የግብርና ማቀነባበሪያ፣ ፋርማስቲካልና የመሳሰሉት ላይ ትኩረት በማድረግ የውጭ ምንዛሬ ግኝቱን የተሻለ እንዲሆን እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

አቶ ፍጹም እንደገለጹት፤ ሁሉም ፓርኮች በተለያዩ ምርቶች ላይ የተሰማሩ በመሆኑ የአኅዋን ተጽዕኖ መቀነስ ተችሏል፡፡በቀጣይ ከገበያ ትስስር ጋር በተያያዘ በቀጥታ ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ዘርፎች ላይ ትኩረት ተደርጓል፡፡

ኢንቨስትመንቱ በብዙ ፈተና እያለፈ ነው ያሉት ፍጹም፤ ዓለም አቀፍ ችግሮች ሰፊና ውስብስብ ናቸው፡፡ ከአኅዋ መሰረዝ ሌላው ችግር መሆኑን አንስተዋል፡፡ይህን ሁሉ ችግር በመቋቋም ሁሉም ኢንዱስትሪ ፓርኮች ሥራ እየሠሩ ነው ብለዋል፡፡

ወደፊት ከውጭ ሀገራት ትላልቅ አልሚዎችን በመሳብ ኢንዱስትሪ ፓርኮችን በመገንባት ተጨማሪ የሥራ ዕድልና ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ግኝት ላይ ትኩረት ተደርጓል ሲሉ ተናግረዋል።

በአሁኑ ወቅት በኮርፖሬሽኑ ስር የሚተዳደሩ 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች ያሉ ሲሆን የሚሠሩበት አቅም የሚለያይ ቢሆንም ሁሉም ሥራ ላይ መሆናቸውን አስረድተዋል።

ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ከ100 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ፈጥረዋል፤ ለሀገሪቷም በየዓመቱ በሚሊዮኖች ዶላር የሚቆጠር የውጭ ምንዛሬ እያስገቡ መሆኑን አንስተዋል።

አቶ ፍጹም እንዳመለከቱት፤ የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና እንደ ሀገር የመጀመሪያ ነው፡፡በቀጣይ ወደ ሌላ አካባቢ ይሰፋል፡፡ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ለነፃ የንግድ ቀጣናው ቅርብ በመሆኑ በተለያዩ ምርምሮችና ሥልጠና በመደገፍ ማኅበረሰቡን ግንዛቤ እያስጨበጠ ነው፡፡

የባለሀብቱን ግንዛቤ በማሳደግ እንዲያለሙ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ፍጹም፤ ነፃ የንግድ ቀጣናው የውጭና የሀገር ውስጥ ባሀብቶችን ጨምሮ በርካታ አካላት የሚሳተፉበት በመሆኑ የሰለጠነ የሰው ኃይል ይፈልጋል፡፡በቀጣይም ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል እንደሚፈጠር ይጠበቃል ብለዋል፡፡

በ2014 ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተገኙበት በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የተመረቀው ሱፍሌ ማልት የብቅል ማምረቻ ፋብሪካ ከ50 ሺህ ከሚበልጡ አርሶ አደሮች ጋር ትስስር በመፍጠር የብቅል ገብስ እያመረተ ይገኛል።

# ዘንድሮ 13 የመስኖ ፕሮጀክቶችን በከፊል ለማጠናቀቅ ታቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ግንባታቸው እየተካሄደ ከሚገኙ 28 የመስኖ ፕሮጀክቶች ውስጥ 13ቱን በከፊል ለማጠናቀቅ ጥረት እየተደረገ መሆኑን የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ በበጀት ዓመቱ ለመስኖ ፕሮጀክቶች ስምንት ነጥብ 03 ቢሊዮን ብር መመደቡ ተመልክቷል፡፡

የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት እና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ ብዙነህ ቶልቻ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ በአሁኑ ጊዜ በሀገሪቱ 28 የሚደርሱ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ግንባታቸው በመከናወን ላይ ነው፡፡በበጀት ዓመቱም 13 ፕሮጀክቶችን በከፊል አጠናቆ ለልማት ዝግጁ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

13 የመስኖ ፕሮጀክቶች በከፊል ሲጠናቀቁ ሁለት ሺህ 450 ሄክታር መሬት ወደ ልማት መግባት የሚችልበት ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችሉ ናቸው ብለዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ 27 የመስኖ ግድቦችን ለመገንባት የጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት በማከናወን ላይ እንደሚገኝ አመልክተው፤ በተያዘው በጀት ዓመትም ሰባት የጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት ለማጠናቀቅ መታቀዱን ጠቅሰዋል፡፡

የመስኖ ግድብ የጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶች በሰባት ክልሎች ላይ የሚገኙና ሲጠናቀቁ 103 ሺህ ሄክታር መሬት ማልማት የሚችል መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን የመጠገን ሥራ እየተከናወነ እንደሚገኝ ገልጸው፤ ለአብነትም የቆቦ ጊራና የከርሰ ምድር ውሃ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት በ138 ሚሊዮን ብር ተጠግኖ አቅሙን የማሳደግ ሂደት ተጀምሯል፡፡ይህም ሦስት ሺህ 600 ሄክታር መሬት ማልማት የሚያስችል መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

እንዲሁም 31 ጥልቅ ጉድጓዶችን በመጠገን እና የውሃ መሳቢያ ሞተር ተከላ በማከናወን በፊት ይለማ የነበረውን ሁለት ሺህ 800 ሄክታር መሬት ወደ 800 የሚሆን ተጨማሪ ሄክታር ማልማት የሚቻል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በጋምቤል ክልል ከ30 ዓመታት በፊት የተሠራው የአልዌሮ የመስኖ ልማት 10 ሺህ ሄክታር ለማልማት የሚያስችል መሆኑን አውስተው፤ የመስኖ ግድቡን መሠረተ ልማት ለመጠገን እንደሚሠራም አመላክተዋል።

በተያያዘም በቆላማና አርብቶ አደር አካባቢዎች በሚከናወኑ የልማት ሥራዎች 90 የንጹህ መጠጥ ውሃ ቁፋሮ፣20 የአነስተኛ መስኖ፣ ስድስት የመካከለኛ መስኖ የማስፋፊያ ግንባታዎች እንደሚከናወኑ ገልጸዋል፡፡

በአካባቢዎቹ የሚገነቡ አነስተኛና መካከለኛ የመስኖ ግድቦች 830 ሄክታር መሬት ሰብልና የግጦሽ ሣር ለማልማት የሚያስችሉ መሆኑን ጠቁመው፤ በፀሐይ ኃይል የሚሠሩ የመስኖ ውሃ መሳቢያ ሞተሮች (ፓምፖች) በ150 ሚሊዮን ብር የሚሰራጭ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

በ11 ክልሎች 178 ሺህ ሄክታር መሬት የሚሸፍኑ 509 አነስተኛና መካከለኛ የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ እንደሚካሄድ ጠቁመው፤ 237 ሺህ ሄክታር የሚሸፍኑ 231 የአነስተኛ እና መካከለኛ የመስኖ የጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶች የሚሠሩ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

209 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 204 የመስኖ አውታሮች ጥገናና 27 ሺህ 644 ውሃ መሳቢያ ፓምፕ ጥገና በስምንት ክልሎች ይካሄዳል ብለዋል፡፡

የሥራ ተቋራጮች የአቅም ውስንነት፣ የሲሚንቶ እጥረት፣ የካሳ ክፍያ እና የጸጥታ ችግሮች ፕሮጀክቶቹን በተያዘላቸው ጊዜ ለማጠናቀቅ ተግዳሮት መሆናቸው ገልጸዋል፡፡

ዜና

# ሀገራዊ ምክክሩን ማሳካት ከተቻለ እንደ ዓድዋ ሊዘከር የሚችል ድል ይሆናል

**ተስፋ ፈሩ**

አዲስ አበባ፡- በሰከነ የውይይት መንፈስ በዘመናት ሂደት ሲንከባለሉ የመጡ ሀገራዊ ጥያቄዎችና የተበላሸውን የፖለቲካ ሥርዓት የምናርምበት ሀገራዊ ምክክሩን ማሳካት ከተቻለ ልክ እንደ ዓድዋ ሊዘከር የሚችል የትውልዱ ድል ይሆናል ሲሉ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ምክትል ሊቀመንበር ዮሐንስ መኮንን (አርክቴክት)ገለጹ።

ዮሐንስ (አርክቴክት) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፤ የዓድዋ ድል የጥቁር ሕዝብ አኩሪ የድል ምዕራፍ እንደሆነው ሁሉ፤ ሀገራዊ ምክክሩንም በተሳካ ሁኔታ ማካሄድ ከቻልን ልክ እንደ ዓድዋ ትውልድ የሚዘክረው ከጠላት ሳይሆን ከራሳችን ጋር ታግለን ብልሹ የፖለቲካ አስተሳሰብና አሠራራችንን ያረቅንበት ታሪካችን ሆኖ ለትውልድ ይቆያል ብለዋል።

ሀገራዊ ምክክር በብዙ ዓመታት ውስጥ አንድ ጊዜ የሚከሰት ከፍ ያለ ፋይዳ ያለው ተግባር ነው ያሉት ምክትል ሊቀመንበሩ፤ ምክክሩ ትውልድ የተሻገሩ የፖለቲካ ጥያቄዎችንና የማንግባባቸውን የታሪክና የፖለቲካ ሥርዓት አረዳዶች ፈትሾ ለማረም ዕድል ይሰጣል።

ምክክሩ በኢትዮጵያ የተረጋጋ መንግሥት ለመመሥረት የሚያስችል አንድ ሁነኛ መሣሪያም መሆኑን ተናግረው፤ በአግባቡ ከተጠቀምንበት የምናተርፍበት ድል



አርክቴክት ዮሐንስ መኮንን

ይሆናል ሲሉ ሃሳብ ሰጥተዋል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት እንደ ሕዝብ በአውዳሚ ጦርነት ውስጥ አልፈናል፤ አሁንም የማያባራ ግጭት ውስጥ ነን፡፡ ከዚህ የምንወጣበት አንዱ መዳኛ ሀገራዊ ምክክር ነው ሲሉ ዮሐንስ (አርክቴክት) ተናግረዋል።

ሀገራዊ ምክክሩ ስኬት እንደሀገር፣ በሕዝብ፣ በተለያዩ ተቋማትና በሚዲያዎች ዘንድ የቅድሚያ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ አጀንዳ መሆን እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

«ሚዲያዎች ለሀገራዊ ምክክሩ አነስተኛ ትኩረት መስጠታቸው ያሳዝነኛል» ሲሉ የወቀሱት ዮሐንስ (አርክቴክት)፤በዚህ ጊዜ በእያንዳንዱ ቀዳሚ ዜና፣ ርዕሰ አንቀጽ እና የፊት ገጽ ላይ የሀገራዊ ምክክር አጀንዳ ቀዳሚ አጀንዳ ሆኖ በየዕለቱ ከዜና በፊት ልንሰማው የሚገባን አንዱ ጉዳያችን ሆኖ መቀመጥ ይገባው ነበር ብለዋል፡፡

ምክክሩ ለሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ብቻ የሚጣል ተግባር አለመሆኑን ገልጸው፤ ምክክሩ የመላው ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያዊ ተቋማት ጉዳይ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

ምሁራን፣ ሲቪክ ማኅበረሰቡ፣ ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ መንግሥት፣ መገናኛ ብዙኃንና በኢትዮጵያ በጎ ቀን እንዲመጣ ያገባናል የሚሉ ሁሉ ሀገራዊ ምክክሩን በፍጹም ቅንነት ሊደረግ እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊም ልክ ለዓባይ ግድብ የሚሰጠውን ዓይነት ከፍተኛ ትኩረት ለሀገራዊ ምክክሩም ሊሰጥ እንደሚገባም ሃሳብ ሰጥተዋል።



# በመዲናዋ ለኢንተርፕራይዞች ከ2 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር በላይ የገበያ ትስስሮች ተፈጥሯል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ሩብ ዓመት በመዲናዋ ለሚገኙ ነባርና አዳዲስ ኢንተርፕራይዞች ከሁለት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ የገበያ ትስስር መፈጠሩን የአዲስ አበባ ከተማ የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ አስታወቀ፡፡

በቢሮው በኃላፊ ደረጃ የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ዘርፍ ኃላፊ አቶ ፍሰሀ ጥበቡ፤ በሩብ ዓመቱ በመዲናዋ ለሚገኙ ለሁለት ሺህ 359 ነባርና አዳዲስ ኢንተርፕራይዞች የተለያዩ የገበያ አማራጮች መፈጠራቸውን ገልጸዋል።

በባዛርና በተለያዩ የገበያ ልማት መርሐ ግብሮች ኢንተርፕራይዞቹ ምርቶቻቸውን ለማኅበረሰቡ እንዲያቀርቡ አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር የሀገር ውስጥ የገበያ ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ ከሁለት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ የገበያ ትስስር መፍጠር ተችሏል ብለዋል፡፡

በአንድ ሺህ 108 ኢንተርፕራይዞች የተደራጁ አራት ሺህ 719 አንቀሳቃሾችን በአገልግሎት፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በከተማ ግብርና፣ በኮንስትራክሽንና በንግድ ዘርፎች ሥራ እንዲጀምሩ በማድረግ የሥራ ዕድል መፈጠሩን አመላክተዋል።

በሩብ ዓመቱ ለተቋቋሙት ኢንተርፕራይዞች 323 ሚሊዮን ብር የብድር አገልግሎት ተሰጥቷል ያሉት አቶ ፍሰሀ፤ 824 ኢንተርፕራይዞች የመሥሪያ ቦታ እንዲያገኙ መደረጉንና በኮንስትራክሽንና በከተማ ማስዋብ የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች የመስሪያ ቦታ የማያስፈልጋቸው በመሆኑ የገበያ ትስስር ተፈጥሮላቸው ወደሥራ እንዲገቡ መደረጉን ጠቁመዋል፡፡

በተጨማሪ አቅማቸውን ያጎለበቱ 800 ኢንተርፕራይዞችን ከጥቃቅንና አነስተኛ ወደአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ የማሸጋገር ሥራ መሠራቱንም አስታውቀዋል።

ኢንተርፕራይዞች ተኪ ምርቶች በብዛት እንዲያመረቱ በማድረግ ለውጭ ምንዛሬ የሚውለውን ሀብት በማዳን ረገድ የተሻለ እንዲንቀሳቀሱ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አስረድተዋል።

በሩብ ዓመቱ 90 ሺህ ሥራ አጦችን ለመመዝገብ ታቅዶ 84 ሺህ መመዝገብ የተቻለ ሲሆን በዚህም 14 በመቶ የቴክኒክ፣ ሙያና ከዚያ በላይ ምሩቃን ሲሆኑ የተቀሩት 86 በመቶዎቹ ከዚያ በታች ናቸው ብለዋል፡፡

በአጠቃላይ በሩብ ዓመቱ ከ36 ሺህ 836 በላይ ለሆኑ ዜጎች በቅጥር የሥራ ስምሪት የሥራ ዕድል መፍጠር እንደተቻለ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ፍሰሀ ገለጻ፤ በሥራ አጥነት ከተመዘገቡ ዜጎች መካከል ተጨማሪ ሥልጠና የሚያስፈልጋቸው 20 ሺህ ዜጎች ተለይተው በቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች አጫጭርና ረጃጅም ሥልጠናዎችን እንዲወስዱ ተደርጓል።

ሥልጠና የማያስፈልጋቸውን ሥራ አጥ ዜጎች ደግሞ ቀጥታ በኢንተርፕራይዝ በማደራጀት የገበያ ትስስር ተፈጥሮላቸው ወደሥራ እንዲገቡ ተደርጓል ሲሉ ጠቁመዋል።

አዲስ አበባ የሀገሪቱ መዲና ከመሆኗ ጋር ተያይዞ ወደከተማዋ የሚደረግ ፍልሰት እየጨመረ በመምጣቱ የሥራ አጥ ቁጥሩ ከፍተኛ ሆኗል ያሉት አቶ ፍሰሀ፤ የሥራ አጥ ምጣኔው ከዚህ ቀደም 18 በመቶ የነበረ ቢሆንም አሁን ላይ አድጎ 22 ነጥብ ስምንት በመቶ ደርሷል ብለዋል።

ቢሮው ምጣኔውን በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ውስጥ ወደአንድ አሀዝ ዝቅ ለማድረግ እየሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ እንደሀገር ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር አለመቻል፣ ከሥራ ባህልና ማማረጥ ጋር ያሉ ችግሮች አለመፈታት፣ የሥራ አጥ ዜጎች ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ችግሩ እንዲባባስ ምክንያት መሆናቸውን አመላክተዋል።

ኢንዱስትሪዎች በመዲናዋ በስፋት በመኖራቸው ዜጎችን አሰልጥኖ የክህሎትና የሙያ ባለቤት እንዲሆኑ በማድረግ ከኢንዱስትሪዎች ጋር የማስተሳሰር ሥራ አስፈላጊ በመሆኑ ከአጋር አካላት ጋር በመሆን በትኩረት እየተሠራበት እንደሚገኝ አቶ ፍሰሀ አብራርተዋል፡፡



አቶ አቤል ጌትነት

# በፍርድ ቤቶች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን ሊቀርፍ የሚችል የሕግ ማሻሻያ ሊደረግ ነው

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ተገልጋዮች በፍርድ ቤቶች ላይ የሚያነሷቸውን ቅሬታዎች ለመቅረፍ፣ የዳኝነት አገልግሎት ተጠያቂነት ለማስፈንና የዳኝነት አካል ሥልጣንን የሚሸረሽሩ ሕጎችን ለመከለስ የሚያስችል የሕግ ማሻሻያዎችን ለማድረግ መዘጋጀቱን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ገለጸ፡፡

በጠቅላይ ፍርድ ቤት ስትራቴጂክ ዳይሬክተር አቶ አቤል ጌትነት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ፍርድ ቤቶች ያልተሻገሯቸውን ችግሮች ለማለፍ እንዲሁም የፍርድ ቤት አሠራርን፣ ቅልጥፍናን እና ውጤታማነትን ለማሳደግ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የለውጥ ፍኖተ ካርታ ወጥቷል፡፡

የፍኖተ ካርታው ዋነኛ ዓላማ ተገልጋዮች በፍርድ ቤቶች ላይ የሚያነሷቸውን ችግሮችና ቅሬታዎች መቅረፍ፣ የዳኝነት አገልግሎት ተጠያቂነትን ማስፈን እንዲሁም በዳኝነት ነፃነትና ተጠያቂነት መካከል ያሉ ሚዛኖችንም አስጠብቆ ለመሄድ የሚያስችል መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ፍኖተ ካርታው የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን በክልሎች ለማደራጀት የሚጠይቅ እና የበጀት አስተዳደር ነፃነት ችግር ለመፍታት የሚያስችል መሆኑም ተመልክቷል፡፡

የበጀት አስተዳደር ነፃነት ችግር፣ የዳኝነት ውሳኔዎች አለማክበር፣ በተገልጋይና አገልግሎት ሰጪዎች መካከል አልፎ አልፎ ያልተገቡ ግንኙነቶች መኖር እንዲሁም በግልጽ ችሎት አለማስቻል ፍርድ ቤቶች ያልተሻገሯቸው ችግሮች መሆናቸው በፍኖተ ካርታው መመላከቱን አቶ አቤል ተናግረዋል፡፡

ውጤታማነትን የሚቀንሱ አሠራሮችን ፈትሾ ማስተካከል፣ የውዝፍ መዛግብት መቀነሻ ስትራቴጂ አዘጋጅቶ ለመተግበር መታቀዱንም ጠቁመዋል፡፡ በተገልጋዮች ዘንድ በቅሬታ የሚነሳውን የመዝገቦች አያያዝ ችግርን ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ለማስተካከል በለውጥ ርምጃው ትኩረት ተሰጥቷልም ነው ያሉት፡፡

በለውጥ ፍኖተ ካርታው ግልጽነትን ማረጋገጥ፣ የላቀ እና ውጤታማ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ፣ ቅንጅታዊ አሠራርን ማጠናከር እና ተደራሽነትን ማስፋት ትኩረት የተሰጠው መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

በጥራት በኩልም ትእዛዞች፣ ብይኖች እና ውሳኔዎች ግልጽ ወጥና ተገማች አለመሆን በፍርድ ቤቶች አሁንም እንደሚስተዋል በፍኖተ ካርታው የተለዩ ችግሮች መሆናቸውን የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፤ የሀሰተኛ ማስረጃዎች መበራከት፣ የጥራት ስታንዳርድ አለመኖርም ችግር ፈተና መሆኑን አንስተዋል፡፡

ሥራን ማቀላጠፍ ላይ የተነሳሽነት እና ችሎታ ማነስ እንዲሁም የክህሎት ችግር እንደሚስተዋል፤ የሕግ እና ፍሬ ነገር ትንተና ችግር፣ ሕግን ተከትሎ ክስ መስማት እና ቃል ክርክር አለማድረግ እንዲሁም ጭብጥ አያያዝ ላይ ክፍተት መኖሩንም በግምገማ መለየቱንም ነው የጠቆሙት፡፡

አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ችግሮች አሉ፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ክህሎት አጠቃቀም ዝቅተኛ መሆን ጠንካራ እና የተናበበ የኮሙኒኬሽን ሥራዎች ክፍተት መኖሩንም ተመልክቷል፡፡ ትግበራው ችግሮቹን እንደሚፈታም ጠቁመዋል፡፡

ከተጠያቂነት አኳያም የሙስና መከላከልና መቆጣጠር ስትራቴጂ ደንብ ትግበራ ዳሰሳ እንደሚካሄድና የዳኝነት አገልግሎት ጥራት ማረጋገጥን መሠረት እንደሚያደርግም ነው የተናገሩት፡፡

የሕዝብን አመኔታ ያተረፈ፣ ቀልጣፋ፣ ጥራት ያለው የዳኝነት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ለመፍጠር የሚያስችል ውጤት የሚያስገኝ መሆን አለበት፡፡ በኅብረተሰቡ ዘንድ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ መገኘትን፡፡ ወጥና ተገማች አገልግሎት መስጠት የሚያስችል የዳኝነት አገልግሎት ስታንዳርድ ይዘጋጃል ብለዋል፡፡

ፍኖተ ካርታው በዘርፉ አገልግሎት አሰጣጥ ግልጽ፣ ቀልጣፋ እና ተደራሽ ማድረግን ታሳቢ ማድረጉንም አመልክተዋል፡፡ ውዝፍ መዝገቦች የዳኝነት አገልግሎቱ አንድ ተግዳሮት ሆኗል፤ የመዝገቦች የማጥራት ምጣኔን ማሳደግ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ የተገልጋዮች ቅሬታዎች እና አገልግሎቶች ቀልጣፋ ምላሽ መስጠትን ትኩረት ያደረገ ዓላማ መሰነቁም ተቀምጧል፡፡

# በቀን 10 ሺህ ቶን ሲሚንቶ የሚያመርተው የለሚ ፋብሪካ ግንባታ በመጋቢት ወር ይጠናቀቃል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

እንሳሮ:- በቀን 10 ሺህ ቶን ሲሚንቶ የማምረት አቅም ያለው የለሚ ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ በመጪው መጋቢት ወር እንደሚጠናቀቅ የኢስት አፍሪካን ሆልዲንግስ ግሩፕ አስታወቀ።

የሲሚንቶ ግብዓቱን የማብላላት ተግባር ያለው (ክሊንከር) የተሰኘው የፋብሪካውን ክፍልና የተብላላውን ግብዓት ወደ ቀጣዩ ሂደት የሚያስተላልፍ ቱቦን የመገጣጠም ሥራ ትናንት ተካሂዷል።

የኢስት አፍሪካን ሆልዲንግስ ግሩፕ የቦርድ ሊቀመንበር ብዙአየሁ ታደለ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደተናገሩት፤ የለሚ ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ ግንባታን በመጪው መጋቢት ወር ለማጠናቀቅ እየተሠራ ነው።

የሲሚንቶ ማምረቻ ዋነኛ ክፍል የሆኑት ግብዓቱን የማብላላት ተግባር የሚከናወንበት (ክሊንከር) የተሰኘው ክፍልና የተብላላውን ግብዓት ወደ ቀጣዩ ሂደት የሚያስተላልፍ ግዙፍ ቱቦ የመገጣጠሙ ሥራ ተጠናቋል ብለዋል።

በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በእንሳሮ ወረዳ ግንባታው እየተከናወነ የሚገኘው ለሚ ናሽናል የሲሚንቶ ፋብሪካ ከተጀመረ 11 ወራትን ያስቆጠረ ሲሆን፤ በቀን 10 ሺህ ቶን ለማምረት የሚያስችለው "ፕሪ ሂተር" የተሰኘውን ዋና የፋብሪካውን መሣሪያ የመገጣጠም ሥራ እንደተከናወነም ገልፀዋል።

የለሚ ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ ፕሮጀክት ምክትል ሥራ አስፈፃሚ አበባው በቀል (ኢ/ር) በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ በሀገሪቱ እያደገ የመጣው የኮንስትራክሽን ዘርፉ ያጋጠመውን ከፍተኛ የሲሚንቶ እጥረት በዘላቂነት ለመፍታት ፋብሪካው ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

ፋብሪካው በመጀመሪያው ዙር በዓመት አምስት ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ ያመርታል ያሉት ኢንጂነር አበባው፤ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ስኬታማ ከሚያደርጉ የግል ዘርፎች መካከል የለሚ ናሽናል ሲሚንቶ አ.ማ ኢንደስትሪያል ኮምፕሌክስ አንዱ እንደሚሆን ይታመናል ብለዋል።

ፋብሪካው ሲጠናቀቅ በሀገሪቷ ያለውን 50 በመቶ የሲሚንቶ እጥረት እንደሚቀርፍ ገልፀው፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ባስቀመጡት አቅጣጫ መሠረት በ15 ወራት ግንባታውን ለማጠናቀቅ እየተሠራ መሆኑን ኢንጂነር አበባው ጠቁመዋል።

በቀጣይም ከሲሚንቶ ምርቱ ባለፈ በሌሎችም ሀገራዊ ፋይዳ ባላቸው የኢንዱስትሪ ዘርፎች ግንባታ በስፋት በመሰማራት ፋብሪካውን ወደኢንዱስትሪ ፓርክነት ለማሳደግ የሚያስችል እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል።

አሁን ላይ በሲሚንቶ ፋብሪካው ግንባታ ለሁለት ሺህ ሰዎች የሥራ ዕድል የተፈጠረ ሲሆን፤ በቀጣይ ሙሉ ሙሉ ወደ ሥራ ሲገባ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለ10 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድልን መፍጠር ይቻላል ብለዋል።

የለሚ ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ ወደሥራ ሲገባ በአፍሪካ ትልቁ የሲሚንቶ ፋብሪካ እንደሚሆን ይጠበቃል ያሉት ደግሞ የሲኖማ ኢንተርናሽናል ኢንጂነሪንግ ኩባንያ ዳይሬክተር ሊን ዧንግ ናቸው።

እንደ ሊን ዧንግ ገለፃ፤ ሲኖማ ፋብሪካው መገንባት ከጀመረ ጊዜ አንስቶ በኃላፊነት እየሠራ አሁን ላይ የፋብሪካው የመጨረሻና ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ደርሷል።

የፋብሪካውን ዘመናዊ ማሽኖች የመገጣጠም ሥራ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እየተከናወነ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል።

በሥነ ሥርዓቱ ላይ የኢስት አፍሪካ ሆልዲን እና ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ ሊቀመንበር ብዙአየሁ ታደሰ፤ የዌስት ኢንተርናሽናል ሆልዲግ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ዋንግ ፋይን፤ የናሽናል ሲሚንቶ ሆልዲንግ ሥራ አስፈፃሚ ሊዩ ጂያንጁን፤ የሃይማኖት አባቶችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

በአማራ ክልል እንሳሮ ወረዳ ልዩ ስሙ ለሚ በተባለ አካባቢ እየተገነባ የሚገኘው የለሚ ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ በኢትዮጵያና የቻይና ባለሀብቶች ጥምረት የተቋቋመ የቅንጅት ኢንቨስትመንት ሲሆን፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቅርቡ የሲሚንቶ ፋብሪካ ግንባታ ሂደቱን መጎብኘታቸው የሚታወስ ነው፡፡

# ከሥጋ ወጪ ንግድ 135 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ለማግኘት ታቅዷል

**ፍሬሕይወት አወቀ**

አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት 25 ሺህ 607 ቶን የሥጋ ምርት ወደ ውጭ ገበያ በመላክ 135 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት መታቀዱን የኢትዮጵያ ሥጋ አምራችና ላኪዎች ማኅበር ገለፀ፡፡

የኢትዮጵያ ሥጋ አምራችና ላኪዎች ማኅበር ዋና ጸሐፊ አቶ አበባው መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የሥጋ ወጪ ንግድ ኢንዱስትሪን ከተቀላቀለች ረዘም ያሉ ዓመታትን አስቆጥራለች፡፡

ሆኖም ሀገሪቷ ካላት እምቅ የእንስሳት ሀብት አንጻር እንዲሁም በኢንቨስትመንቱ ከነበራት ቆይታ የኤክስፖርት አቅሙ አላደግም ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ የሥጋ ምርትን በብዛትና በጥራት ኤክስፖርት ማድረግ አልቻለችም ያሉት አቶ አበባው፤ በ2016 በጀት ዓመት 25 ሺህ 607 ቶን የሥጋ ምርት ወደ ውጭ ገበያ በመላክ 135 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት መታቀዱን ገልፀዋል፡፡

በ2015 በጀት ዓመትም 14 ሺህ 575 ቶን ሥጋ ወደ ውጭ ገበያ ተልኮ 89 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር መገኘቱን ያስታወሱት አቶ አበባው፤ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከሥጋ ወጪ ንግድ የሚገኘው ገቢ እየቀነሰ መምጣቱን ተናግረዋል፡፡

ለሥጋ ወጪ ንግዱ መቀዛቀዝ የሀገር ውስጥ የዋጋ ንረት አንዱ እንደሆነ የጠቀሱት አቶ አበባው፤ ለዋጋ ንረቱ



መባባስም ሀገሪቱ ያለችበት የሰላምና ጸጥታ ሁኔታ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

በሌላ በኩል የቁም እንስሳት ኮንትሮባንድ ንግድ መባባስ የሥጋ ወጪ ንግድ ላይ ተፅዕኖ እንዳለው ጠቁመው፤ ሌሎች ተያያዥ ችግሮች እንዳሉም ተናግረዋል።

በተጠቀሱት ችግሮች ምክንያትም በሀገሪቱ የሚገኙ የኤክስፖርት ቄራዎችም ዝቅተኛ አፈጻጸም እያስመዘገቡ እንደሆነ ነው የተናገሩት፡፡

የቄራዎችን ቁጥር ማበራከት እና የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች ወደ ኢንቨስትመንቱ እንዲገቡ ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር ቢቻልም፤ የሥጋ የኤክስፖርት መጠንን ከፍ ማድረግ አልተቻለም ነው ያሉት፡፡

በአሁኑ ወቅት 11 የኤክስፖርት ቄራዎች በሀገሪቱ የሚገኙ እንደሆነ የገለጹት አቶ አበባው፤ ሁለቱ የኤክስፖርት ቄራዎች በውጭ ባለሀብቶች የሚመሩ እንደሆነና ቀሪዎቹ ኤክስፖርት ቄራዎች ደግሞ ሀገር በቀል በሆኑ ባለሀብቶች ኢንቨስት የተደረጉ መሆናቸውን ነው የተናገሩት፡፡

እነዚህ 11 ሥጋ አምራችና ላኪ ኤክስፖርት ቄራዎች ከፍተኛ አቅም ያላቸው በመሆኑ በዓመት እስከ ሁለት መቶ ሺህ ቶን ሥጋ አምርተውና አቀነባብረው ለዓለም ገበያ የማቅረብ አቅም ያላቸው መሆኑን አቶ አበባው ጠቅሰዋል፡፡

ኤክስፖርት ቄራዎቹን እየፈተኗቸው በሚገኙ የተለያዩ ችግሮች ምክንያት በአሁኑ ወቅት ከአቅም በታች እያመረቱ እንደሆነና የገቢ መጠናቸውም ዝቅተኛ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመቅረፍ ሀገሪቷ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ ግኝት ከፍ ማድረግ እንደሚቻል ጠቅሰዋል፡፡

# የሀሮማያ ሐይቅ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት ሊጀመር ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የሀሮማያ ሐይቅ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት በተያዘው ሳምንት ግንባታው እንደሚጀመር የማያ ከተማ ከንቲባ ኢፍራ ወዚር (ዶ/ር) አስታወቁ፡፡በከተማዋ በ400 ሚሊዮን ብር የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶች እየተገነቡ ነው።

ከንቲባ ኢፍራ ወዚር (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሀሮማያ ሐይቅ ዳርቻ ፕሮጀክት የአካባቢውን የቱሪዝም ሀብት አቅምና መሠረተ ልማት ለማሳደግ ያግዛል።

በዘንድሮ ዓመት በማያ ከተማ ሊሠሩ የታቀዱት 22 አዳዲስና ሁለት ነባር ፕሮጀክቶች መኖራቸውን የገለጹት ዶክተር ኢፍራ፤ ከፕሮጀክቶቹ አንዱ የሆነው የሀሮማያ ሐይቅ ዳርቻ ልማት ጥናት ተጠናቆ ወደ ሥራ ሊገባ መሆኑን አመላክተዋል።

በፕሮጀክቱ ዲዛይን መሠረት የሀሮማያ ሐይቅ ዳርቻ ልማት የመጀመሪያ ምዕራፍ ግንባታ በተያዘው ዓመት መጨረሻ እንደሚጠናቀቅ ጠቁመው፤ በተጨማሪም ባለሀብቶች አካባቢውን እንዲያለሙ ይደረጋል ሲሉ አስረድተዋል።

ለፕሮጀክቱ የመጀመሪያ ምዕራፍ ሥራ 80 ሚሊዮን ብር መነሻ በጀት ተይዞለታል ያሉት ከንቲባዋ፤ ፕሮጀክቱ የአካባቢው ወጣቶች ተደራጅተው ወደሥራ እንዲገቡ ዕድል በመፍጠር ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን የሚያሳድግ መሆኑን አመላክተዋል።

የሀሮማያ ሐይቅ ለ17 ዓመታት ደርቆ የተመለሰ በመሆኑ ፕሮጀክቱ ሐይቁን የመጠበቅ ሥራንም ያካተተ መሆኑን አስታውቀው፤ በሐይቁ ዙሪያ በማልማት አካባቢውን የበለጠ ሳቢ ለማድረግ በቂ ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል።

በፕሮጀክቱ የመንገድ፣ የመናፈሻዎች ግንባታና አካባቢውን የማስዋብ ሥራ እንዲሁም የዓሣ ልማትና ሌሎች ተያያዥ የቱሪዝም ልማት ሥራዎች እንደሚከናወኑ አስረድተዋል።

የልማት ፕሮጀክቱ ከአካባቢው ተፈጥሮ ጋር የሚጣጣምና ሐይቁን ለመጠበቅ የሚያግዝ ሥራ መሆኑን ገልጸው፤ ወደ ከተማ የሚመጡ ጎብኚዎችን ፍሰት ለመጨመርና ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ከፍ ለማድረግ የሚያግዝ መሆኑን ተናግረዋል።

በከተማዋ በተያዘው ዓመት ለሚሠሩ የተለያዩ ፕሮጀክቶች 400 ሚሊዮን ብር በጀት መያዙን ጠቅሰው፤ በዕቅድ የተያዙት 24 ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ የነዋሪዎችን የረጅም ዘመናት የልማት ጥያቄ የሚመልሱ መሆናቸውን ከንቲባዋ አስታውቀዋል፡፡

ፕሮጀክቶቹ የከተማዋን ገጽታ የመቀየርና ለነዋሪዎች የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ያስችላሉ ያሉት ዶክተር ኢፍራ፤ በተለይም የመንገድ፣ የመንገድ ዳር መብራቶች፣ የቱሪዝም ልማትና የተለያዩ የመሠረተ ልማት እንደሚከናወኑ ተናግረዋል።

የማያ ከተማ አስተዳደር በኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት የሀሮማያ፣ አዴሌና አወዳይ ከተሞች በአንድ እንዲደራጁ ወስኖ ያቋቋመው ከተማ ነው።

# «የከተማዋ አስተዳደር...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በመዲናዋ ከሚከናወኑ ሰው ተኮር ተግባራት መካከል የምገባ ማዕከላት አገልግሎት አንዱ መሆኑን ጠቁመው፤ ከ777 ሺህ በላይ ተማሪዎች እንዲሁም ከ35 ሺህ በላይ የሚሆኑ የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸው ወገኖች በየቀኑ የምገባ አገልግሎት እንዲያገኙ እየተደረገ ነው ብለዋል።

በተጨማሪም በመዲናዋ የኑሮ ውድነቱን ለማርገብ አምራችና ሸማቹ በቀጥታ የሚገናኙበት የገበያ ሥርዓት ተዘርግቷል፤ ይህም የገበያ ሰንሰለቱን በማሳጠርና የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ያግዛል ሲሉ ገልፀዋል።

ከንቲባዋ እንዳመለከቱት፤ ከተለያዩ አካባቢዎች የሚገቡ ምርቶችን በአምስት ግዙፍ የገበያ ማዕከላት በማቅረብ ጥራት ያላቸው ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ለኅብረተሰቡ ማቅረብ ተችሏል።

በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሦስት ወራት ብቻ በአቃቂ ቃሊቲ፣ ለሚ ኩራና ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተሞች የግብርና ምርቶችን በቀጥታ ለነዋሪው የሚቀርቡበት ማዕከላት መቋቋማቸውን ተናግረዋል።

በዘመናዊ መልክ በተገነቡት የገበያ ማዕከላት የተለያዩ ምርቶችን ለነዋሪው በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ገበያውን ለማረጋጋት ጥረት እየተደረገ መሆኑን አስረድተዋል።

በተጨማሪ በከተማው የሚገኙ 172 የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች የኑሮ ውድነቱን በማረጋጋት በኩል እያበረከቱ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን አንስተዋል።

አዲስ አበባ ምርት የምታስገባ ብቻ ሳትሆን የምታመርት ከተማ እንድትሆን በከተማ ግብርና ላይ በሠፊው እየተሠራ መሆኑን ገልፀዋል።

በመዲናዋ በጓሮ አትክልት ልማት፣ በዶሮና እንቁላል እንዲሁም በእንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ተችሏል ብለዋል።

የከተማ ግብርናና የሌማት ትሩፋት መርሐ-ግብሮች የዋጋ ግሽበትንና የኑሮ ውድነቱን በማረጋጋት በኩል በጎ አስተዋጽኦ እያበረከቱ መሆኑን ከንቲባዋ ተናግረዋል።

ለኅብረተሰቡ ከፍተኛ ጥቅም ያላቸውን የከተማ አውቶቡስ ትራንስፖርት አገልግሎት፣ የጤና መድህንና የሸገር ዳቦ አቅርቦትን የማሳደግ ሥራዎች በትኩረት እየተከናወኑ መሆኑን አውስተዋል።

ከንቲባዋ በተጨማሪ እንዳስረዱት፤ በ2016 በመዲናዋ 14 የተለያዩ ሜጋ ፕሮጀክቶች በግንባታ ሂደት ላይ ናቸው። የዓድዋ ዜሮ ኪ.ሜ ሙዚየም ግንባታ፣ የትራንስፖርት ማዕከል ግንባታ፣ የሴቶች ተሀድሶና የልህቀት ማዕከልና የየካ መኪና ማቆሚያ ተጠቃሽ ሜጋ ፕሮጀክቶች መሆናቸውን ገልፀዋል።

በፕሮጀክት ግዢ ሂደትና ማኔጅመንት ላይ ሰፊ የሙስና ተጋላጭነት መኖሩን አንስተው ችግሮችን በመቅረፍ ለበርካታ ሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡትን ግንባታዎች በተያዘላቸው ጊዜና በጀት ለማጠናቀቅ በትኩረት እንደሚሠራም አመላክተዋል።

# ስሙስና ሲውል...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በኮሚሽኑ የጥቅም ግጭት መከላከል መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ መስፍን በላይነህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2016 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ድረስ በተሠራ የቅድመ መከላከል ሥራ ከዘጠኝ ቢሊዮን በላይ ብር ማዳን ተችሏል፡፡

በተጨማሪም በተጠቀሰው ጊዜ ከአራት ሚሊዮን ካሬ ሜትር በላይ መሬት ከምዝበራ ማዳን ተችሏል ብለዋል፡፡

ባለፉት ሦስት ዓመታት ብቻ የፍርድ ውሳኔ ካረፈባቸው ንብረቶች ውስጥ ወደ መንግሥት እንዲገቡ የተደረጉ ስለመኖራቸውም አንስተዋል፡፡

በተጠቀሱት ዓመታት የፍርድ ውሳኔ ካረፈባቸው ንብረቶች ውስጥ 12 ቀላል ተሽከርካሪዎች፣ 179 ከባድ ተሽከርካሪዎች እና 17 ኮንቴነሮች እንዲሁም 10 ቤቶች ወደ መንግሥት ገቢ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም ከ829 ሚሊዮን 229 ሺህ በላይ ብር እና 1 ነጥብ 09 ኪሎ ግራም ወርቅ ወደ መንግሥት ካዝና እንዲገባ ተደርጓል ሲሉ አቶ መስፍን አብራርተዋል፡፡

ከ960 በላይ የአሠራር ሥርዓት ጥናት በማካሄድ ሙስና እና ብልሹ አሠራርን ለመቅረፍ የሚያስችል ምክረ-ሃሳብ እና የትግበራ ክትትል ሥራ መሠራቱንም ኃላፊው ገልጸዋል፡፡

ሕግን ለማስከበር በተደረገ እንቅስቃሴም 11 ሺህ 350 የሙስና ወንጀል የክስ መዝገቦች ላይ በ20 ዓመታት ውስጥ ውሳኔ መሰጠቱን አያይዘው ጠቅሰው፤ በዚህም ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ለማስመለስ ተችሏል ብለዋል፡፡

መንግሥት ግልፅነትና ተጠያቂነት አሠራርን ለማስፈን የፖለቲካ ቁርጠኝነት የሚያሳዩ የተለያዩ እርምጃዎችን መውሰዱን በመጠቆም፤ የፀረ ሙስና ትግሉን ተቋማዊ እና ሀገራዊ በሆነ አደረጃጀት እንዲመራ መደረጉን አንስተዋል፡፡

ኢትዮጵያ ሙስናን ለመከላከል እና የትውልድን ሥነምግባር ለመገንባት ልዩ ልዩ ተግባራትን አከናውናለች ያሉት አቶ መስፍን፤ ከ20 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ግንዛቤ እንዲያገኙ መደረጉን ጠቅሰዋል፡፡

በኢትዮጵያ ከ2005 እስከ 2014 ዓ.ም በዓመት በአማካይ ከአንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን እስከ ሦስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዶላር በሙስና እና በሌሎች የወንጀል ድርጊቶች ከሀገር ይሸሽ እንደነበር ኃላፊው ተናግረዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ተኪ ምርቶች ሀገርን በብዙ መልኩ እየታደጉ ነው!

የሀገሪቱ የወጪና የገቢ ንግድ ሚዛን ከፍተኛ ልዩነት እንደሚታይበት ይታወቃል፡፡ ይህንንም ሀገሪቱ ለውጭ ገበያ ከምታቀርባቸው ምርቶች ከምታገኘው የውጭ ምንዛሬ ዝቅተኛነትና ለገቢ ምርት ከምታወጣው የውጭ ምንዛሬ ከፍተኛነት መረዳት ይቻላል፡፡

ሀገሪቱ ይህን ክፍተት ለማጥበብ በርካታ ተግባሮችን ታከናውናለች፤ ከእነዚህም መካከል የውጭ ምንዛሬ ለሚያስገኙና የውጭ ምንዛሬ ወጪን ለሚያስቀሩ ወይም ለሚቀንሱ ምርቶች ትኩረት ሰጥታ እየሠራች ያለችበት ሁኔታ ይጠቀሳል፡፡ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የግብርና፣ የኢንዱስትሪ እንዲሁም እንደ ወርቅ ያሉ የማዕድን ምርቶችን በስፋት በማምረት ለውጭ ገበያ ከማቅረብ በተጨማሪ፣ ከውጭ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን እንዲሁም የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በሀገር ውስጥ ለመተካትም በስፋት እየተሠራ ይገኛል፡፡

እንደሚታወቀው በሀገሪቱ በርካታ የኢንዱስትሪ ፓርኮች በመንግሥት ተገንብተው ወደ ሥራ ገብተዋል፤ የግሉም ዘርፍ እንዲሁ ኢንዱስትሪዎችን በስፋት እየገነባ ወደ ሥራ አስገብቷል፤ እያስገነባም ይገኛል፡፡ ኢንዱስትሪዎቹ ምርቶቻቸውን ለውጭና ለሀገር ውስጥ ገበያ እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡

በግብርናውም ዘርፍ እንዲሁ ከውጭ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት የሀገሪቱን የግብርና ምርቶች ፍላጎት ለመሸፈን በሚደረገው ጥረት በየዓመቱ ምርትና ምርታማነቱን መጨመር ተችሏል፡፡

ለእነዚህ ተኪ ምርቶች ትኩረት ተሰጥቶ መሠራቱን ተከትሎ አመርቂ ውጤቶች መታየት ጀምረዋል። ባለፈው በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት ሁለት ቢሊዮን ዶላር የሚያወጡ ተኪ ምርቶች መመረታቸውን ለእዚህ በአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በቅርቡ እንዳስታወቀው፣ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት በሦስት ወራት ውስጥ ብቻ የ350 ሚሊዮን ዶላር ተኪ ምርቶች በሀገር ውስጥ ተመርተዋል፡፡ 96 የሚደርሱ አዲስ ተኪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ማምረት እንደሚቻል በጥናት ተለይቶም ወደሥራ ተገብቷል።

በግብርናው ዘርፍ በኩልም ተመሳሳይ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ተመድቦለት ከውጭ የሚመጣውን ስንዴ በሀገር ውስጥ የስንዴ ምርት መተካት ተችሏል፡፡ በሀገሪቱ በመኸርም በበጋ መስኖ ስንዴ ልማትም እየተካሄደ የሚገኘው የስንዴ ልማት የሀገሪቱን የስንዴ ፍላጎት ብቻ ሳይሆን ማሟላት ያስቻለው ለጎረቤት ሀገሮች ስንዴ በመሸጥ የውጭ ምንዛሬ ማስገኘትም ችሏል፡፡ ለቢራ ብቅል የሚያስፈልገውን ገብስ ሙሉ ለሙሉ በሀገር ውስጥ ማምረት የተቻለበትን ሁኔታም ሌላው ማሳያ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል፡፡

በማዕድን ዘርፉም እንዲሁ ከውጭ የሚመጣውን የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ ምርት መተካት የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ባለፈው በጀት ዓመት አንድ ነጥብ 186 ሚሊዮን ቶን የድንጋይ ከሰል በሀገሪቱ መመረቱን የማዕድን ሚኒስቴር ሰሞኑን አስታውቋል፡፡ ሀገራዊ ዓመታዊ የድንጋይ ከሰል ፍጆታው ከአንድ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ቶን በላይ ስለመሆኑ ባለፈው ዓመት የተደረገ ጥናትን ዋቢ አድርጎ ሚኒስቴሩ ጠቁሟል፡፡ ይህም የድንጋይ ከሰል ፍላጎትን በሀገር ውስጥ መተካት ስለመቻሉ አንድ ማሳያ ነው፡፡

ይህ ሁሉ መንግሥት በተኪ ምርቶች ማምረት ላይ የያዘው አቅጣጫ ትክክል መሆኑን ያመለክታል፡፡ እስከ አሁን የተገኘው ውጤት በተኪ ምርቶች ላይ መሥራት ውጤታማ እንደሚያደርግ ያመላክታል፡፡ የሀገሪቱ የኢንዱስትሪ ዘርፍ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙና የውጭ ምንዛሬን የሚያድኑ ሥራዎች ላይ በተለይ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ በተኪ ምርቶች ላይ በስፋት እየተከናወነ ያለውን ተግባር አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

በግብርናው ዘርፍም እንዲሁ ስንዴ በስፋት የማምረት ሥራው ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት መሆኑ እንዳለ ሆኖ ከውጭ የሚመጣውን የሩዝ ምርት በሀገር ውስጥ ለመተካት የተጀመሩ ሥራዎች መስፋፋት ይኖርባቸዋል።

በማዕድን ዘርፍም በድንጋይ ከሰል ላይ የታየው ውጤት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ ላይ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ የድንጋይ ከሰል ምርቱ ሀገሪቱ ለድንጋይ ከሰል የምታወጣውን የውጭ ምንዛሬ ያስቀረ፣ የፋብሪካዎችን የግብዓቱን ጥያቄ በቅርቡ የመለሰ፣ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል የፈጠረ፣ የዘርፉ ኩባንያዎች እንዲፈጠሩ ያስቻለ ትልቅ ስኬት ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

ኢንዱስትሪዎች በድንጋይ ከሰል ላይ የሚያነሱትን የጥራት ችግር ጥራቱን የሚያስጠብቁ ፋብሪካዎች እየተገነቡ ያሉበት ሁኔታ ሊፈታው ይችላል፤ የኢንዱስትሪዎች የድንጋይ ከሰል ፍላጎት እየጨመረ ሊመጣ ስለሚችል ያንን ታሳቢ ያደረገ የድንጋይ ከሰል ምርት አቅርቦት እንዲኖር ከወዲሁ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

መንግሥት በተኪ ምርቶች ላይ መሥራቱን አጠናክሮ እንደሚቀጥል በተደጋጋሚ አስታውቋል፡፡ ተኪ ምርት በማምረት የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ማሟላት መቻል፣ በዚህም ሂደት የተገኘው ተሞክሮ በራሳቸው ተኪ ምርት ላይ አተኩሮ ለመሥራት ትልቅ አቅም በመሆን ያገለግላሉ፤ በሀገሪቱ የተኪ ምርቶች ፋይዳ በሚገባ ተለይቷል፤ በተጨባጭም ታይቷል፡፡

ተኪ ምርትን በስፋት ለማምረቱ ሥራ በትኩረት መሥራት የመንግሥት ተግባር ብቻ መሆን የለበትም። ውጤቱን ያጣጣሙት ወገኖችና የመላው ሕዝብና የሚመለከታቸው ባለድርሻዎች ሥራ ጭምር መሆን ይኖርበታል፡፡ ተሞክሮውን ማስፋት፣ አዳዲስ ተኪ ምርቶች ላይ አተኩሮ መሥራት፣ የሀገር ውስጥ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን መጠቀም ላይ ያለውን የተሳሳተ አመለካከትም ማረቅ በስፋትና በትኩረት ሊሠራባቸው የሚገቡ ተግባራት ናቸው፡፡ ይህ ሲሆን ሀገርን በብዙ መልኩ እየታደጉ ያሉት ተኪ ምርቶች ተቀባይነት ይጨምራል፤ የማምረቱም ሥራ ይጠናከራል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሀገራዊ ምክክር ለጋራ ሰላም

**ብርሀን ፈይሳ**

በኢትዮጵያ የተለያዩ ዓላማዎችን አንግበው በፖለቲካው መድረክ ላይ የሚገኙ ኃይሎችና ልሂቃን የሃሳብ ልዩነቶች እየሰፉ መሄዳቸው ሀገርን ለብዙ ውጥንቅጥ ዳርጓል፡፡ ልዩነት ተፈጥሯዊ ነው፣ ነገር ግን እነዚህን ልዩነቶች በሠለጠነ መንገድ ማስተናገድ ባለመቻሉ በየአካባቢው ግጭቶች እንዲበራከቱ ሆኗል፡፡

ግጭት ያስነሱትንም ሆነ ያላስነሱትን ልዩነቶች እና ጥያቄዎች መሠረት በማድረግ ተቀራርቦ በውይይት ችግሮች እንዲፈቱ በማድረግ ሀገራዊ አንድነትን የመገንባት አስፈላጊነት አያጠያይቅም። ለዚህ ደግሞ ሀገራዊ ምክክር አወንታዊ ሚና ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል።

በኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የተፈጠሩ ልዩነቶችን ለማርገብ ይቻል ዘንድ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን በአዋጅ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ ኮሚሽኑ ለሥራው ይረዳው ዘንድም በክልሎች ተዘዋውሮ ከተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ውይይት አድርጓል፡፡

ከህብረተሰቡም አጀንዳዎችን ተቀብሏል። በተጨማሪም ለመገናኛ ብዙኋን የተለያዩ ሥልጠናዎችን ሰጥቷል፡፡ የኮሚሽኑ መቋቋም በተለይ ሰላም ወዳድ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ትልቅ ተስፋን የጫረ ጉዳይ ነው፡፡ በየጊዜው አዳዲስ የብጥብጥ አጀንዳ እየቀረጹ ሀገሪቱን ሰላም ለማሳጣት የሚጥሩ ኃይሎች በበዙበት በዚህ ወቅት ችግሮችን ሊፈታ የሚችል አካል መፈጠሩ የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ ነው። ህብረተሰቡም ኮሚሽኑን ለመርዳት በቻለው መጠን እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል፡፡

ኮሚሽኑ በአዋጅ ከተሰጡት ሥራዎች መካከል ከዚህ በፊት በመንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት የተደረጉ ሀገራዊ የምክክር ሂደቶችን እና የተገኙ ውጤቶችን ያጠናል፣ በቀጣይ በሚያካሂዳቸው ሀገራዊ ውይይቶች በግብዓትነት የሚጠቀማቸው መሆኑንም ይጠቀሳል፡፡

ቀደም ብሎ ሀገራዊ መግባባት ለማምጣት ይረዳሉ የተባሉ ውይይቶች የተደረጉ ቢሆንም በሊህቃን መካከል መግባባት ስላልነበረባቸው ውጤት አላመጡም፡፡ በተለይ በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት በሚደረጉ ክርክሮች ላይ የሚነሱት የተሳሳቱ ትርክቶች በአንድ ጉዳይ የተለያየ እውነታ እንዲፈጠር አድርገዋል፡፡

እነዚህ የተሳሳቱ ትርክቶች እንዲታረሙ የምክክር ኮሚሽኑ ዋነኛ ሥራ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ከዚህም ባለፈ ፤ በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ያለውን የተራራቀ የአመለካከት ልዩነት በአግባቡ እንዲያስተናግዱ ማድረግ የሚያስችል አስቻይ ሁኔታ ለመፍጠርም መልካም አጋጣሚ የሚፈጥር ነው፡፡

ይህ ሲባል በሀገራችን ክልል አቀፍና ሀገር አቀፍ ፓርቲዎች የሚያራምዱት የፖለቲካ ርዕዮተዓለም ኢትዮጵያ ከሚለው ሀገራዊ መንፈስና ስሜት የሚቀዳ በማድረግ ሀገራዊ አንድነትን በጠንካራ መሠረት ላይ ለማዋቀር የተሻለ እድል የሚፍጠር ነው፡፡

በአጠቃላይ ኮሚሽኑ በልሂቃኖች መካከል ሀገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ያሉትን ልዩነቶች በጥናት፣ በሕዝባዊ ውይይቶች ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መንገዶችን በመጠቀም የመለየት ሥራ ካከናወነ በኋላ ትኩረት የሚደረግባቸው ነጥቦችን በመለየት ሀገራዊ መግባባት እንዲፈጠርባቸው ያደርጋል፡፡

በዚህም ቁጭ ብሎ የመነጋገር ልምድ ይዳብራል፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትም ይሰፍናል። ከዚህ በዘለለ በሚደረጉ ህዝባዊ ውይይቶች በሚነሱ ሃሳቦች ላይ በመመርኮዝ ወደፊት የተሻለ ሀገር ለመፍጠር የሚያግዙ ውሳኔዎች ሊተላለፉ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡

በርግጥ ኮሚሽኑ በዋነኛነት በተለያዩ አካባቢዎች የሚታዩትን ግጭቶች እንዲቆሙ ለማድረግ ቅድሚያ ተቀራርቦ መወያየት ላይ ማተኮር እንዳለበት በተለያዩ ጊዜያት በሰጠው መግለጫ አሳውቋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ኃላፊነቱን ወስዶ አቀራርቦ ለማወያየት በትጋት እየሠራ ነው።

ይህ ቢያንስ ሰላም ለመፍጠር ብዙ አማራጮች እንዳሉ ያመላከተ ነው። ሁሉን ያሳተፈ ሀገራዊ መግባባት መፍጠር ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አለመሆኑ ታውቆ በተቃራኒ ወገን የቆሙ አካላት ወደ ውይይት መምጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ለኮሚሽኑ መጠናከር የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለምክክር የሚሆኑ አጀንዳዎችን መምረጥ፣ ከኮሚቴዎችም ሆነ ከሕዝብ የሚገኙ ምክረ ሃሳቦችን ለመንግሥት ማቅረብ፣ ለኮሚሽኑ እንቅስቃሴ የሚያስፈልጉ የውስጥ ደንብ እና መመሪያዎችን ማውጣትን ጨምሮ መሠረታዊ የአስተዳደራዊ ተግባራትን በበላይነት እንደሚመራ በአዋጅ ተደንግጓል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ የሚገኙ አባላት ከተለያየ የሕዝብ ክፍል እንደመምጣታቸው ከመጡበት አካባቢ የሚነሱ ሃሳቦችን ማንፀባረቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑም ያልተገደበ ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

ኮሚሽኑ አጀንዳዎችን ለይቶና ለምክክር የሚሆኑ ግብዓቶችን ካሟላ በኋላ ምክክሮች ብቃት ባለው ገለልተኛ በሆነ አካል የሚመሩ፤ ያለመግባባት መንስኤዎችን በትክክል የሚዳስስ አጀንዳ ላይ የሚያተኩሩ ይሆናሉ፡፡ ግልጽ ብሎም ለማስፈጸም የሚያስችሉ ውጤታማ ሀገራዊ ውይይትን የሚያስተናግድ ሥርዓትን የመዘርጋት ሥልጣኑን ተጠቅሞ ውጤት የሚያመጣ ሥራ እንደሚሠራ ይጠበቃል።

ልዩነቶች በነበሩባቸው ሃሳቦች ላይ ሰፊ ውይይት ተደርጎ ሀገራዊ አንድነት የሰፈነባት ኢትዮጵያ እንደምትፈጠር የሁሉም ዜጋ እምነት ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን ጉዳዩ ለኮሚሽኑ ብቻ የሚተው መሆን የለበትም፡፡ ኮሚሽኑ ሂደቱን የሚያስፈጽም ተቋም ነው፤ ለዚህ ጉዳይ መሳካት ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ኃላፊነቱን መወጣት አለበት፡፡

በየመድረኮች የምንሰማው፣ በመገናኛ ብዙኃን የምናየውና የምንሰማው ሰላም ለማምጣት ሁሉም መረባረብ እንዳለበት የሚመክር ነው። ለዚህ ግን ሁሉም ኃላፊነት ወስዶ የሚሳተፍ መሆን አለበት፡፡ ተፈጥሯዊ የሆነውን ልዩነት ዋጋ እያሳጣነው ነው፡፡ ልዩነት ወደ ግጭት የሚወስድ አስመስለነዋል፡፡

ሙዚቃ አለመውደድ መብት ነው፡፡ ሙዚቃ መውደድም መብት ነው፡፡ ሙዚቃ የሚወድ ሰው የማይወዱትን ከጠላ፣ ሙዚቃ የማይወድም የሚወዱትን ከጠላ ችግሩ ያኔ ነው፡፡ ፖለቲካው ላይ የምናየው ልዩነት ልክ እንደዚህ አይነት ነው፡፡ መሠልጠን ማለት የሰዎችን ልዩነት ማክበር ነው፡፡

የሠለጡኑ ሀገራትን የሥልጣኔ ምጥቀት መዘርዘር ወደ ሥልጣኔ አይወስድም፡፡ ወደ ሥልጣኔ የሚወስደው እነርሱን መሆን ነው፡፡ ከየት ተነስተው ዛሬ የት ላይ እንደደረሱ ማየት ነው፡፡ የራሳችንን የቁርሾ ታሪኮች እየጠቀስን ለዛሬ መጨቃጨቂያ ከማድረግ በሥልጣኔ የበለጡን ሀገራት ከየት ተነስተው ምን አድርገው ነው ኮሽ የማይልበት ሀገር የፈጠሩት የሚለውን ብናስተውል ነው ለምንቆረቆርለት ሕዝብ የሚጠቅመው፡፡

በአጠቃላይ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ተመካክረን መፍትሔ የምናመጣበትና የሠለጠነች ሀገር የምናስረክብበት ትልቅ እድል ነው ፤ ይህንን እድል በአግባቡ ተጠቅሞ ፤ የኮሚሽኑን ዓላማ ለስኬት ማብቃት የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ነው !።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# ብሄራዊ ምክክር ለሁለንተናዊ ተሃድሶ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ሀገራችን ሁለንተናዊ ተሀድሶ የሚያስፈልጋት ሰሞን ላይ ነን፡፡ በተለያዩ ትርክቶች የወየቡ ከሰላም ይልቅ ለጠብ፣ ከአንድነት ይልቅ ለመለያየት መንገድ በሚከፍቱ የጥላቻ መንፈስ ውስጥ ከወደቅን ሰነባብተናል፡፡ ሽንቁሮቻችን ከመጥበብ ይልቅ እየሰፉ ጣት ከመጠቋቆም ባለፈ የመፍትሄ አካል እንዳንሆን በራሳችን ላይ አስጨክነውናል። ኢትዮጵያዊነት የማይወክሉ እነዚህ የእኔነት ግሳንግሶች ከመካከላችን እንዲወጡ ሁሉን አቀፍ የተሃድሶ ንቅናቄ ለመተግበር የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ እንገኛለን፡፡

ብሄራዊ ምክክር ለሁለንተናዊ ተሃድሶ ስል መነሳቴ አንድም ወቅታዊ ችግሮቻችንን ለማቃለል ፤አንድም ዘላቂ ሰላምን ከማምጣት አኳያ ፋይዳው ላቅ ያለ መሆኑን በማመን ነው፡፡ ታላላቅ የሰው ልጅ ሥልጣኔዎች በልዩነት ውስጥ እንዴት ተከባብሮና ተቻችሎ መኖር እንደሚቻል በተረዳ ጭንቅላት የጥላቻ ድንበሮችን በማፈራረስ የመጣ ነው፡፡ እንደዚሁ ሁሉ መጨረሻ አልባ ኋላቀርነቶች ልዩነትን ለጸብ ከመጠቀምና የጥላቻ ድንበርን ከማፍረስ ይልቅ በማበጀት የሚመጣ ስለመሆኑ ለመረዳት ጠቢብ መሆን አይጠይቅም።

በዓለም የሥልጣኔ ታሪክ ውስጥ በደም የጠራ ፖለቲካ፣ በሞት የተመለሰ ጥያቄ አላውቅም። የሚኖርም አይመስለኝም፡፡ እንዲህ ዓይነት አስተሳሰቦች ሀገር ከማውደምና ትውልድን ከመመረዝ ባለፈ ይሄ ነው የሚባል በጎ ዐሻራ የላቸውም፡፡ አሸናፊነትን ከኃይል ጋር አቆራኝተን የፍቅርን ወደብ ላፈረስን ለእኛ ይሄ ጨዋታ ሊመስለን ይችላል፡፡

ሀገር ለመገንባት ግን ከዚህ የተሻለ አስተማማኝ አማራጭ የለንም፡፡ በብሄራዊ እርቅና ብሄራዊ መግባባትን ሳንፈጥር በያዝ ለቀቅ ከ60 የራቀ ዓመታትን አሳልፈናል፡፡ ዛሬም ከዛ የመግደልና የመሞት መንፈስ ሳንወጣ ትውልዱን በሌላ ስቃይ መጥተንበታል፡፡ ሀገር ለሁላችን እንድትበቃ ከሁላችን ለሁላችን የሆነ ሃሳብና ጨዋነት ያስፈልጋል፡፡ አድጋና በልጽጋ ሕዝብ የሚኮራባት፣ ትውልድ የሚታፈርባት እንድትሆን አብሮነትን ያገዘፈ የወንድማማችነት ባህል ያስፈልጋታል፡፡

አሁን ባለው ወቅታዊ ሁኔታ እንዲህ ነበርን ብለን ታሪክን የኋሊት መልሰን ከማውራት ባለፈ ምንም እያደረግን አይደለም፡፡ ያለፈው ትውልድ በደሙ ታሪክ ጽፎ ለምንጊዜም የምንኮራባትን ሀገር ሰጥቶናል፡፡ ያለፈው ትውልድ የእኔ የአንተ የሌለባትን በእኩል የምትጠራን ኢትዮጵያ በምንም ከማይላላ የብዙሃነት ውህደት ጋር አስረክቦናል፡፡ እኛ የዚህ ትውልድ ሰዎች ግን የተሰጠንን የአደራ ሀገርና ታሪክ ስንጠብቅ አንታይም፡፡ ትልቋን ኢትዮጵያ ትንሽ እያደረግናት ነው፡፡ የጋራ ታሪካችንን ወደምንምነት እየቀየርን ነው፡፡

ታሪክ ይጠበቃል እንጂ አይሸረፍም፡፡ ሙሉ ሀገር እንደተረከብን ሁሉ ሙሉ ሀገር የማስረከብ ግዴታ አለብን፡፡ የኮራነው፣ በዓለም አደባባይ ቀና ብለን የቆምነው በተረከብነው ያልተሸራረፈ ታሪክና እውነት ነው፡፡ መጪው ትውልድ እንዲኮራና ቀና ብሎ እንዲራመድ ያልተሸራረፈ ታሪክ ልናስረክበው ግዴታ አለብን፡፡ የተያያዙና የተጠላለፉ ብዙሃን እጆች የነደፉትን የታሪክ ገድል ሀገር ጠል በሆነ ፖለቲካና ግብረ ኑባሬ እየሸራረፍን የማንም እንዳይሆኑ ለማድረግ ዳር ዳር እያልን ነው፡፡

የታሪክ ሸርፈት የማንነት ሸርፈት ነው፡፡ ያልገባንና ያልተረዳነው አንድ ነገር ታሪኮቻችንን ስንሸርፍ ኢትዮጵያዊነታችንን እየሸረፍን መሆኑ ነው፡፡ እውነትን ስናዛናፍ አብሮነታችንን እያዛነፍን ነው፡፡ የዚህ መጨረሻው ደግሞ ጦርነትና ማህበራዊ ቀውስ ነው፡፡ ተነጋግሮ የማይግባባ ትውልድን ለመፍጠር መንገድ የሚከፍት ነው፡፡ ጦርነትና ጥላቻን፣ እልህንና ማንአለብኝነትን የፈጠሩብን ፖለቲካዊም ሆኑ ማህበራዊ ነውሮቻችን የታሪክ ሸርፈት የፈጠራቸው እንደሆኑ ቢገባን ስቃዮቻችንን በግማሽ ማስቀረት እንችል ነበር፡፡

ብሄራዊ ምክክር ስንል ብሄራዊ እርቅ ማለታችን ነው፡፡ እርቅ ስንል ሁሉን አቀፍ ሰላምና ተግባቦት፣ ይቅርታና ተሃድሶ ማለታችን ነው፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ ለሰላም በተዘጋጁ አዕምሮና ልብ፣ ለይቅርታ በበረቱ አንደበቶች ነው፡፡ አንተም ተው አንተም ተው ብሎ ማስታረቅ የባህላችን ፊተኛ ሆኖ ከጥንት ወደዛሬ የመጣ ነው፡፡ ኢትዮጵያ እየተጎዳች ያለችው በጥቂት ራስወዳድ እና በብሄርና በጎሳ ሽፋን በተደበቁ ጽንፈኞች ነው፡፡ ብዙሃኑ ከድሮ ቀለሙ ጋር..አብሮነትን ሽቶ፣ ብዙሃነትን ናፍቆ የሚኖር ነው፡፡

ትግላችን አንድነታችን መመለስ፣ ኢትዮጵያዊነትን ማስቀጠል ከሆነ ቅደም ተከተላቸውን ስተው የተዘበራረቁብንን ስሜት ለበስ አካሄዶቻችንን ማስተካከል አለብን። ባልተስተካከለ ሃሳብ ውስጥ የተስተካከለች ሀገር የለችም፡፡ ባልተስተካከለ ፖለቲካ ውስጥ የሰመረ ትውልድ የለም፡፡ በየዘርፉ ያለው ሀገራዊ ሥርዓት የተሃድሶ ህክምና ያስፈልገዋል። ዋናውና ከስቃይ ሊታደገን የሚችለው ህክምና ደግሞ ምክክር ነው፡፡

ላለፉት 50 እና 60 ዓመታት ውስጥ ፖለቲካችንን ለማስተካከል፣ የልዩነት ቁርሾዎቻችንን ለማከም የሄድንባቸው የምክክር አቅጣጫዎች ዒላማቸውን ስተው ዛሬ ላይ ደርሰናል፡፡ አሁን ላይ ተግባራዊ ሊደረግ ከጫፍ የደረሰው የምክክር መድረክ ከብዙ ጊዜ በኋላ የተመለሰ ምናልባትም ለጀመርነው የሰላምና የአንድነት ትልም እንደመጨረሻ እድል ሊታይ የሚገባው እንደሆነ ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡

ሀገርን ለመታደግ ምክክር ከሁሉም የተሻለው መንገድ መሆኑ የማይካድ ቢሆንም ላልተጠቀመበት እና እልኸኝነቱን ላልተወ ማህበረሰብ ግን ትርጉም አይኖረውም፡፡ ያለፉት ጊዜያቶች በምን ሁኔታ ይሄን እድል እንዳጣ ስንጠይቅና ስንመረምር የተለያዩ ምክንያቶችን እናገኛለን፡፡ የትኛውም ምክንያት ከሀገር መፍረስና ከማህበረሰብ መለያየት ስለማይበልጥ በየትኛውም ሁኔታ ላይም ሆነን ሀገራዊ ምክክር ማድረጉ ተመራጭ ነው ባይ ነኝ፡፡

ብሄራዊ ምክክር ለሁለንተናዊ ተሃድሶ ብዬ ስነሳ በምክንያት ነው፡፡ እንደሀገር ሰላም ለማምጣትም ሆነ ሰላምን ለማስቀጠል እንደብቸኛ አማራጭ ሊወሰድ የሚገባው ድርጊት ነው፡፡ ከኃይል ፖለቲካ ወደ አጽንኦት ፖለቲካ መውረድ በሰላም እጦት ለምትሰቃይ ሀገር ከፍታ እንጂ ዝቅታ አይደለም፡፡ ከክርክር ወደ ምክክር፣ ከፉክክር ወደ ንግግር መመለስ በጥላቻና በዘረኝነት እጣፈንታው ለሚያሰጋው ማህበረሰብ ክብር እንጂ ውርደት አይደለም። ተነጋግሮ ከመታረቅና ከመተቃቀፍ የላቀ ወደአንድነት የምንመለስበት ሁነኛ ጥበብ የለንም፡፡

‹ቤት በጥበብ ይሠራል በማስተዋልም ይጸናል› የሚል መጽሀፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ አውቃለው፡፡ በቅዱስ ቃሉ ላይ ቤት ትዳር ሆኖ የተገለጸ ቢሆንም እኔ ግን ቤት የሚለውን በሀገር መንዝሬ እንዲህ አልኩ፡፡ ቤት ሀገር ናት..ሀገር ትዳር፣ ማንነት፣ ህልም፣ ራዕይ ናት፡፡ ሀገር ክብር፣ ታሪክ፣ ስምና መታበያ ናት፡፡ እናም ሁሉንም የሆነች ይቺ ሀገራችን በጥላቻ እንዳትፈርስ በጥበብ ቆማ በማስተዋል እንድትጸና ያስፈልጋታል፡፡ ጥበብ ማረፊያዋ አስተውሎት ነው፡፡ አስተውሎት ደግሞ በመስከንና በመደማመጥ ውስጥ የሚንጸባረቅ የክብር ጸሀይ ነው፡፡ ሰክነንና ተደማምጠን የልዩነታችንን ምንጭ ካላደረቅን ሌላ መዳኛ የለንም፡፡

በከንቱ ያባከናቸው የምክክር እድሎቻችን ሰምረው ቢሆን ኖሮ ዛሬ ላይ ብዙ ጥያቄዎቻችን መልስ አግኝተው ድህነትን ካሸነፉ፣ ኋላቀርነትን ከረቱ ጥቂት ሀገራት ውስጥ እንሆን ነበር፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ እድሎቻችንን ሳንጠቀም ዛሬ ላይ ደርሰናል፡፡ ዋናውና ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ እንዳለፈው ጊዜ እድሎቻችንን አባክነን የሚቆጭ ትውልድ እንዳንፈጥር ካለፈው በመማር ብዙ ማትረፍ ይኖርብናል። ይሄን በመሰለው ጉዳይ ላይ አያሌ ሀገራት ችግሮቻችውን በቁጥጥር ስር አውለዋል፡፡ እኛም በምክረ ሃሳብ ችግሮቻቸውን ከረቱ ሀገራት ውስጥ ሆነን ስማችን በአሸናፊነት እንዲጠቀስ ለምክክር ከመቀመጥ ባለፈ እድሎቻችንንም መጠቀም ትርፉ የላቀ ነው ፡፡

ብርቱዎች ሀገር ይሠራሉ እንጂ የተሠራ አያፈርሱም፡፡ ብልሆች ታሪክ ይጠግናሉ እንጂ ታሪክ አይሸራርፉም፡፡ ኢትዮጵያን እንወዳለን የምንል ሁሉ ከቃል ባለፈ የሀገር ፍቅር ስሜታችንን አንድም ታሪክ ባለማጣመም አንድም እውነትን አግዝፎ በመስበክ ፍቅራችንን ወንዝ ተሻጋሪ ማድረግ እንችላለን፡፡ ሠላምን በማምጣት ሂደት ውስጥ የማያቸው አንዳንድ ትዝብቶች አሉ፡፡ አንዳንዶቻችን ጠባቂዎች ነን፡፡ የተቀረነው ደግሞ ምንም ይሁን ግድ የማይሰጠን፡፡ ሀገር የጋራ ቅርስ ከሆነች ሰላምም የጋራ ውርስ መሆን አለበት፡፡ ይሄ ማለት በእርቀ መድረኩ ፊት ስለሰላም ሁላችንም አስተዋጽኦ አለን ማለት ነው፡፡

ከዛሬ ርቀን ነገን ባለማየታችን ብዙ ዋጋዎችን ከፍለናል፡፡ ከዛሬ አርቀን ነገን ማየት ብንችል ኖሮ አሁናዊ ስቃዮቻችን ማብቂያቸው በሆነ ነበር። ትናንት ላይ ዛሬን ባለማየታችን ለዛሬ ሀገራዊ ስቃይ ተዳርገናል፡፡ ዛሬ ላይ ሆነን ነገን በማየት መጪውን ትውልድ ከፈተና መታደግ እንችላለን። ለዚህ እንዲረዳን ደግሞ ሁለንተናዊ ተሀድሶን በሚያመጣ ሀገራዊ ምክክር ፊት ቆመናል፡፡

ታሪክ ጠባቂዎች እንሁን፡፡ ወንድማማች ሆነን በቅለን ወንድማማች ሆነን ካልገዘፍን መሳቂያ ነው የምንሆነው፡፡ እንደጣውንት የምንተያይባቸው የልዩነት አውዶች በፍቅር ሚዛን ፊት እዚህ ግቡ የሚባሉ አይደሉም፡፡ ግን ማክረርና ማባባስ ስለሚቀናን ለዓላማቸው የመስዋዕት በግ ሆነን ቀርበንላቸዋል። እስከመቼ? በትናንሽ እንከኖች ብዙ ዋጋ እየከፈልን ስለመሆኑ ከእኛ ወዲያ ምስክር የለም፡፡ ሁላችንም ተነጋግረን በመግባባት ሀገር እናድን፡፡

ትውልድ የፖለቲካ አስተሳሰብ ውጤት ነው፡፡ ከአጼው ሥርዓት ወዲህ ያሉ የፖለቲካ አስተሳሰቦች ትውልዱ ላይ የልዩነት ቀንበር ጭነውበታል ። አሁን ያለው ትውልድ የዛ ዘመን የፖለቲካ አስተሳሰብ ውጤት ነው፡፡ ይሄ ብሄር ተኮር እሳቤ እንዲጠራ ደግሞ ሰፊ ልብ፣ ከሰፊ ሃሳብና መድረክ ጋር አስፈልጓል፡፡ በእንዶድ እንደጠራ ሸማ ከልዩነትና ከጥላቻ ጠርተን ኢትዮጵያን የምንመስልበት ጊዜ ላይ ነን፡፡

የጸብ ከተማ የፍቅርን ታሪክ ያፈርሳል፡፡ ታሪክ የፈረሰባት ሀገር ደግሞ በምንም አትቆምም። ከአሉባልታ ርቀን ሕዝብ በሚያቀራርብ መፍትሄ ተኮር መድረክ ላይ መሳተፍ ለሀገር የምናዋጣው መዋጮ ነው፡፡ ወቅታዊ ችግሮቻችንን በአስታራቂና በአግባቡ በምክረ ሃሳቦች መቃኘት አለብን፡፡ ብሄራዊ ምክክር በሁለንተናዊ ተሃድሶ ኢትዮጵያን የሚታደግ ነውና አሻራችንን ለማሳረፍ እንረባረብ፡፡

> **አሁን ባለው ወቅታዊ ሁኔታ እንዲህ ነበርን ብለን ታሪክን የኋሊት መልሰን ከማውራት ባለፈ ምንም እያደረግን አይደለም። ያለፈው ትውልድ በደሙ ታሪክ ጽፎ ለምንጊዜም የምንኮራባትን ሀገር ሰጥቶናል፡፡ ያለፈው ትውልድ የእኔ የአንተ የሌለባትን በእኩል የምትጠራን ኢትዮጵያ በምንም ከማይላላ የብዙሃነት ውህደት ጋር አስረክቦናል**

ኢኮኖሚ

# ግብርና

## አምራችና ሸማችን በዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጂ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት የግብርናውን ዘርፍ ለማዘመን ከተቋቋሙ ተቋማት መካከል አንዱ ነው፡፡ ተቋሙ በግብርናው ዘርፍ ለረዥም ጊዜ የቆዩና ትላልቅ ማነቆ የሆኑ ችግሮችን በመለየት ለተለዩት ችግሮችም እንዲሁ የመፍትሔ ሃሳቦችን በማመንጨት ምርትና ምርታማነት እንዲያድግና አምራችና ሸማቹ ተጠቃሚ እንዲሆን እንዲሁም ከዘርፉ በሚገኘው ውጤት የሀገር ኢኮኖሚ እንዲያድግ የሚሠራ ተቋም ነው፡፡

ተቋሙ ለምርትና ምርታማነት ዕድገት እንዲሁም የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከሚያከናውናቸው ተግባሮች መካከል በዲጂታል ቴክኖሎጂ ለአርሶ አደሩ የሚሰጠው የምክር አገልግሎት አንዱ ነው፡፡ ተቋሙ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለአርሶ አደሩ የሚሰጠውን የምክር አገልግሎት ቀልጣፋ፣ ቀላልና ምቹ ማድረግ የሚያስችለውን 8028 የተባለ ፕላት ፎርም አልምቶ ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ገበሬዎቹም በእጅ ስልካቸው ወደ 8028 እየደወሉ በግብርና ሥራቸው ሁሉ ለሚገጥማቸው ማንኛውም ችግር መፍትሔ እያገኙ መሆኑን የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ጪምዶ ዋንጫላ ገልጸዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ በዚህ ሥርዓት በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ የሆነ የምክር አገልግሎት ለአርሶ አደሩ ይሰጣል፡፡ አርሶ አደሩ በ8028 ነጻ ጥሪ ደውሎ ያጋጠመውን ችግር በአጭሩ በመግለጽ ፈጣን ምላሽና የምክር አገልግሎት እያገኘ ነው፡፡

እስካሁን በዚህ ሥርዓት ውስጥ የምክር አገልግሎት እየተሰጠ የነበረው በሰብል ምርቶች ብቻ እንደነበር ያስታወሱት ዶክተር ጪምዶ፤ በአሁኑ ወቅት ደግሞ የገበያ መረጃን ለማካተትና ለአርሶና አርብቶ አደሩ ተደራሽ ማድረግ የሚያስችለውን ሲስተም ለማልማት ዝግጅቱ ተጠናቅቋል፡፡ ለዚህም ተቋሙ ከሜርሲ ኮርፕስ እና ከዩኤስአይድ ፊድ ዘ ፊውቸር ትራንስፎርሚንግ አግሪካልቸር/ MERCY CORPS Ethiopia እና ከUSAID Feed The Future Transforming Agriculture/ ከተሰኙት ድርጅቶች ጋር ለመሥራት መስማማቱን አስታውቀዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ በሰብል ምርቶች ብቻ የነበረውን የምክር አገልግሎትና የገበያ መረጃ ተደራሽነት በእንስሳት ሀብትም ማስፋት አስፈልጓል። በተለይም በአፋርና በሶማሌ ክልሎች የሚሰጠው የግብርና ምክር አገልግሎት በእንስሳት ሀብት ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡ በእንስሳት ሀብት የሚሳተፉ የአፋርና የሶማሌ ክልል አርሶ አደሮች ወይም አርብቶ አደሮች ይህን መረጃ አግኝተው በሚገባ የሚጠቀሙበትን ዕድል መፍጠር የሚያስችል ይሆናል፡፡

በእስካሁኑ ሂደትም በእነዚህ ክልሎች 130 ሺ የሚደርሱ አርብቶ አደሮች በዚህ መረጃ እየተጠቀሙ ሲሆን፤ ይህም ከፍተኛ ፍላጎት መኖሩን ያመለክታል። በእነዚህ ክልሎች ሲስተሙን አስፍቶ መጠቀም እንዲቻልም ተቋሙ ከሁለቱ አጋር ድርጅቶች ጋር ስምምነት አድርጓል፡፡

ድርጅቶቹ የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያደርጉ የጠቀሱት ዶክተር ጪምዶ፤ የ USAID Feed The Future Transforming Agriculture የ23 ሚሊዮን ብር እንዲሁም MERCY CORPS Ethiopia ደግሞ አምስት ሚሊዮን የሚደርስ ብር ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት በበኩሉ ስድስት ሚሊዮን ብር ድጋፍ በማድረግ በጋራ ሲስተሙን በማልማት አርሶና አርብቶ አደሩን ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል ብለዋል፡፡ ዲጅታል ሲስተም ማለት ህጻን ልጅ እንደማሳደግ ነው ያሉት ዶክተር ጪምዶ፣ በየጊዜው አዳዲስ ነገሮችን በመጨመር አቅምን በማሳደግ ሲስተሙን ማልማት የግድ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ይህ ሲስተም የአርሶና አርብቶ አደሩን አቅም ለማሳደግ ከፍተኛ ድጋፍ የሚያደርግ ሲሆን፤ በተለይም ለአርሶና ለአርብቶ አደሩ በሚያመች መንገድ ሲስተሙ የሚለማ ይሆናል፡፡ ይህ ሲስተም ከለማ በኋላ በክልል የሚገኙ አርሶ አደሮች በተለይም አርብቶ አደሮች እንዲሁም በክልሉ የሚገኙ የልማት ሠራተኞች ይህን መረጃ የሚያገኙ ይሆናል፡፡

መረጃው እጅግ በጣም ፈጣን ምላሽ የሚሰጥበት መሆኑን የጠቀሱት ዶክተር ጪምዶ፤ አርብቶ አደሮች ደውለው በ24 ሰዓት ውስጥ መልስ የሚያገኙበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ መልስ ካላገኙ መረጃው በቀጥታ ወደ ኢንስቲትዩቱ እንደሚመጣ ጠቅሰው፣ ኢንስቲትዩቱም ክትትልና ድጋፍ እንደሚያደርግ ተናግረዋል፡፡ ይህም አርሶና አርብቶ አደሩ ስለግብርና ወቅታዊ መረጃዎችን በፍጥነት ማግኘት ያስችላል ብለዋል፡፡

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እንዳብራሩት፤ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ በቴክኖሎጂው ከሚያገኛቸው የተለያዩ መረጃዎች መካከልም የአንበጣና ሌሎች ተባዮች መረጃዎች ይገኙበታል፤ እነዚህን ችግሮች በጥናት በመለየት አስቀድሞ ከሳተላይት በሚገኘው መረጃ መሠረት እየመጣ ያለውን አደጋ ለአርሶ አደሩ እንዲደርስ በማድረግ አስፈላጊውን የቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ ያስችላል፤ መረጃውም አስፈላጊ ከሆኑ ምክሮች ጋር ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ አርሶና አርብቶ አደሩም ይህንኑ የምክር አገልግሎት በመቀበል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይችላል፡፡

ሲስተሙ ለአርሶ አደሩ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እጅግ የላቀና የጎላ ነው፡፡ በተለይም ምርትና ምርታማነትን እንዲጨምር እና የገበያ መረጃ ማግኘት እንዲችል ጉልህ አበርክቶ ይኖረዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት አርብቶ አደሩ የገበያ መረጃ የለውም፤ ምን ያህል እና የት ቦታ ወስዶ እንደሚሸጥ ምንም አይነት መረጃ የሌለው በመሆኑ በመሀል ለደላሎች ተጋላጭ ይሆናል፡፡ ደላሎች በተለይም በግብርና ምርቶች ሰፊ ድርሻ ያላቸው በመሆኑ አምራቹም ሆነ ሸማቹ ተጎጂ ናቸው፡፡

በዚህ ሲስተም ውስጥ አምራቹንና ሸማቹን በማስገባት ሁለቱም አካላት መረጃው እንዲኖራቸው ይደረጋል ያሉት ዶክተር ጪምዶ፤ ሲስተሙ ደላላውን ከመሀል ለማስወጣት እጅግ ጠቃሚ እንደሆነም አመልክተዋል፡፡ ሲስተሙ በተለይም አምራቹንና ሸማቹን በማስተሳሰር ህጋዊ ያልሆነውን ደላላ ሙሉ ለሙሉ ማስወጣት እንደሚችልም አስታውቀዋል፡፡

በሀገሪቱ በአሁኑ ወቅት በግብርና ምርቶች ላይ ትልቅ ችግር እየፈጠሩ ያሉትና ሰፊ ድርሻ ያላቸው ሕገወጥ ደላሎች መሆናቸውን ገልጸው፤ እነዚህ ደላሎች ምርት እያለ ምርት የለም በማለት ዋጋ እንዲጨምር የሚያደርጉና ምርቱ ወደ ሸማቹ እንዳይደርስ ሰው ሰራሽ እጥረት የሚፈጥሩ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

በአሁኑ ወቅትም በየወረዳው የገበያ መረጃ የሚሰበስቡ ባለሙያዎችን በመቅጠር ወደ ተግባር መግባት መቻሉን ጠቅሰው፣ በየሳምንቱ የገበያ መረጃ ተሰብስቦ ትክክለኛነቱ ሲረጋገጥ ወደ ሲስተሙ እንደሚገባና እንደ አስፈላጊነቱ አምራቹና ሸማቹ እንዲጠቀምበት እንደሚደረግም ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩቱ እያደራጀ ያለው ብሔራዊ የገበያ ሥርዓት እንደሆነ የጠቀሱት ዶክተር ጪምዶ፤ ይህ የገበያ መረጃ ሁሉም ቦታ ላይ ተደራሽ ይሆናል ማለት እንዳልሆነም አስታውቀዋል፡፡ የኢንተርኔት ተደራሽነትን እንደሚጠይቅ ገልጸው፣ ሁሉም አርሶ አደር መረጃው እንዲኖረውና ስለ ሲስተሙ በቂ ግንዛቤ ይዞ ተጠቃሚ መሆን እንዲችል በሚዲያ የማስተዋወቅ ሥራ መሥራት ተገቢ እንደሆነም አመላክተዋል፡፡

ሌላው በግብርና ግብዓት አቅርቦት ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ያስችላል የተባለው ዲጅታል የክፍያ ሥርዓት ነው፤ ይህም ልማዳዊ አሠራርን የሚያስቀር እንደሆነ ነው ዶክተር ጪምዶ ተናግረዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ ግብርና የተለያዩ ግብዓቶችን የሚጠቀም ሲሆን፤ የሀገሪቱ አርሶ አደር በተለይም ማዳበሪያ፣ ምርጥና የተሻሻሉ ዝርያዎችን ይጠቀማል። እነዚህን የግብርና ግብዓቶች የሚጠቀመው አርሶ አደርም ግብዓቶቹን

> **ይህ የመረጃ ሥርዓት አርሶ አደሩንና ሸማቹን ተጠቃሚ ያደርጋል። አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ምርቱን እና እንስሳውን ያለአግባብ እንዳይሸጥ የሚያደርግ ሲሆን፣ ሸማቹም ያለአግባብ ከዋጋ በላይ እንዳይገዛ ያስችለዋል**

የሚገኝበት ሥርዓት እጅግ ኋላቀር በመሆኑ የግብዓቶቹን ጥራትም ሆነ ዋጋ መቆጣጠር አይቻልም፡፡

እነዚህን መረጃዎች ለማወቅ የልማት ሠራተኛው የግድ አርሶ አደሩ ቤት ተገኝቶ መመዝገብ ይጠበቅበት እንደነበር አስታውሰው፣ በአሁኑ ወቅት ዘመናዊ በሆነ መንገድ በዲጅታል የክፍያ ሥርዓት መቆጣጠር እንደሚቻል ጠቁመዋል፡፡

ለአብነትም ማዳበሪያ ከጅቡቲ ተጓጉዞ ታች ቀበሌ ደርሶ ለአርሶ አደሩ እስከሚሰራጭ ድረስ መቆጣጠር የሚያስችለው የኤሌክትሮኒክ ክፍያ ሥርዓት የማዳበሪያ አሰጣጡንም ዘመናዊ የሚያደርግ እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡ አርሶ አደሩ የእጅ ስልኩን በመጠቀም የሚፈልገውን የግብርና ግብዓት ይጠይቃል፡፡ ክፍያውንም በኤሌክትሮኒክ የክፍያ መንገድ ይፈጽማል፡፡ ለዚህም ከሲስተሙ ጋር የተናበበ የመለያ ቁጥር የሚሰጠው ሲሆን፤ ይህም ግብዓቱን መችና የት ቦታ ላይ መውሰድ እንደሚችል መረጃ ይሰጠዋል፡፡ በመሆኑም በአካባቢው በሚገኙ የህብረት ሥራ ማህበራት ቀርቦ መውሰድ የሚያስችለው ይሆናል፡፡ አገልግሎቱ ለአጠቃቀም ቀላል፣ ምቹና ወጪ ቆጣቢ እንደሆነም ተነግሮለታል፡፡

አርሶ አደሩ በሲስተሙ ሲጠቀም በቤቱ ሆኖ የእጅ ስልኩን ብቻ በመጠቀም የሚፈልገውን የግብርና ግብዓትና መጠን መጠየቅ ይችላል፤ ጥያቄውም ወደ ሲስተሙ ይገባል፡፡ በዚህ መሠረት ግብዓቱ ዝግጁ ሲሆን፣ አርሶ አደሩ የሚደርሰውን መልዕክት ተከትሎ ግብዓቱን መውሰድ የሚችልበት ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡

ይህ ሥርዓት በሙከራ ደረጃ የተጀመረ መሆኑን የጠቀሱት ዶክተር ጪምዶ፤ በ65 ወረዳዎች ሥርዓቱ በሙከራ ደረጃ መጀመሩንም አስታውቀዋል፡፡ ከዚህ በኋላ በማዳበሪያ ዙሪያ የሚነሱ ማጨበርበሮች ይወገዳሉ፤ ስግብግብ ነጋዴዎችንም ጭምር ሲስተሙ ያስወግዳቸዋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ‹‹በሌሎች ሀገራት የሚታየው ቴክኖሎጂ በእኛም ሀገር ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል›› ብለዋል፡፡

የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ማንደፍሮ ንጉሴ በበኩላቸው ኢንስቲትዩቱ አጠቃላይ በግብርናው ዘርፍ ውስጥ ያሉ መሠረታዊ ችግሮችን በጥናትና በምርምር የመለየት ሥራ እንደሚሠራ ጠቅሰው፣ ከለየ በኋላም ለተለዩት ችግሮች የመፍትሔ ሃሳቦችን እንደሚያቀርብ ገልጸዋል፡፡

አርሶ አደሩ ከግብርና ሥራው ጋር ተያይዞ ለሚገጥመው ችግር ኢኒስቲትዩቱ የምክር አገልግሎት እየሰጠ እንደሆነም አስታውቀዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም አርብቶ አደሩ እንስሳቱን ወቅታዊ በሆነ ዋጋ መሸጥ እንዲችል የገበያ ዋጋ መረጃ የሚያገኝበትን ዘመናዊ አሠራር ለመተግበር ከአጋር ድርጅቶች ጋር ለመሥራት መግባባት ላይ መድረሱን ገልጸዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ የእንስሳት ግብይቱን ጨምሮ በእንስሳት ጤና አጠባበቅና አረባብ ላይ ትኩረት ተደርጎ የሚሠራ ሲሆን፤ በየወረዳው ማለትም የእንስሳት ገበያዎች ባሉባቸው አካባቢዎች የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች ተገኝተው በየአካባቢው ያለውን የገበያ ሁኔታ በማጥናት መረጃው ተሰብስቦ መልሶ የሚሰራጭ ይሆናል፡፡ መረጃውም ለማንኛውም መረጃውን ለሚፈልግ ሰው ተደራሽ ይሆናል፡፡

መረጃው ተደራሽ የሚሆነው በ6077 በስልክ የድምጽ ጥሪና አጭር የጽሁፍ መልዕክት እንደሆነም ገልጸዋል፡፡ ይህ የአርሶ አደሮችና የአርብቶ አደሮች የግብርና መረጃ መስጫ አገልግሎት እንዲሁም የሀገር አቀፍ የገበያ መረጃ ሥርዓት ዲጅታል አገልግሎት በተለያዩ ቋንቋዎች እንደሚቀርብም ዶክተር ማንደፍሮ አስታውቀዋል፡፡ መረጃው ተደራሽ የሚሆነው ለአርሶ አደር፣ ለአርብቶ አደርና ለከፊል አርብቶ አደር ብቻ ሳይሆን ለሸማቹና የቄራ አገልግሎት ለሚሰጡም ጭምር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

መረጃውም የት ቦታ፣ በምን ያህል ዋጋ፣ ምን አይነት እንስሳ እንደሚሸጥ እንደሚያሳይ ጠቁመው፣ ለሰብል ምርትም ተመሳሳይ አገልግሎት እንደሚሰጥ አስታውቀዋል፡፡ ይህም አርሶ አደሩንና ሸማቹን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ጠቁመዋል፡፡ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ምርቱን እና እንስሳውን ያለአግባብ እንዳይሸጥ እንደሚያደርግ አብራርተው፣ ሸማቹም ያለአግባብ ከዋጋ በላይ እንዳይገዛ የሚያስችለው አሠራር ነው ብለዋል፡፡ ይህ የመረጃ ሥርዓት ለአርሶ አደሩም ሆነ ለሸማቹ መፍትሔ የሚሰጥ የመረጃ ሥርዓት ሆኖ እንደሚያገለግልና የአርብቶ አደሩና የአርሶ አደሩን ምርታማነት ማሳደግና ገቢ መጨመርን ዓላማ አድርጎ እንደሚሠራ አመልክተዋል፡፡

ይህ የመረጃ ሥርዓት ከዓመት በፊት ተግባራዊ እንደሆነና አርሶና አርብቶ አደሩ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ እየተጠቀመቡት መሆናቸውን ያስታወሱት ዶክተር ማንደፍሮ፣ በአሁኑ ወቅት ይህንኑ አሠራር ለማስፋትና ባልተዳረሰባቸው ክልሎች ጭምር ተደራሽ ለመሆን ስምምነት መደረሱን ገልጸዋል። አገልግሎቱ እየሰፋ መሆኑን መሆኑን ጠቅሰው፣ በአሁኑ ስምምነት የአፋርና ሱማሌ ክልልን መጨመር እንደተቻለ ገልጸዋል። ይህን ተከትሎም የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ከ157 ወረዳዎች ወደ 250 ወረዳዎች ከፍ ማለቱንና ተደራሽነቱ እየሰፋ መምጣቱን ተናግረዋል፡፡

ግብርናን ለማዘመን እየተጋ ያለው የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ይህን ሥራ የሚሠራው ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ሲሆን፤ ግብርና ሚኒስቴር በዚህ ሲስተም ውስጥ ገብቶ አቅሙ እንዲጎለብት ያደርጋል፡፡ ከዚሁ ሲስተም የተገኘውን ዕውቀትና ልምድ የግብርና ሚኒስቴር ቀምሮና በበቂ ሁኔታ አዘጋጅቶ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ሥራውን ሲያቆም በከፍተኛ ሁኔታ አስፋፍቶ የሚቀጥልበት እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

ማህበራዊ

# አስኳላ

# የፈተና አሰጣጥን ከመቀየር ባሻገር

**አስናቀ ፀጋዬ**

የትምህርት ሚኒስቴር ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ የተለያዩ ተግባራዊ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ የፈተና አሰጣጥ ሥረዓቱን ማሻሻልና መቀየር ነው፡፡ በዘንድሮው በጀት ዓመትም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የፈተና አሰጣጥ ሥርዓቱን በማጠናከሩና ከኩረጃ ነፃ በማድረጉ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ውጤት በትምህርት ጥራት ረገድ ያለውን ክፍተት በተዘዋዋሪ ፍንትው አድርጎ አሳይቷል፡፡

ከአሁን ቀደም በትምህርት ተደራሽነት እንጂ በጥራት ላይ ጉልህ ትኩረት ተሰጥቶ ባመለሠራቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተፈተኑ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ 3 ነጥብ 2 ከመቶ ያህሉ ብቻ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ነጥብ ማግኘት ችለዋል፡፡ ይህም ጠንካራ የፈተና አሰጣጥ ሥርዓት በመኖሩ ከዚህ በፊት በኩረጃና በስርቆት ተግበስብሶ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በቀላሉ መግባት እንደማይቻል አመላክቷል፡፡

ፈተናው በዚህ መልኩ እንዲሰጥ የተፈለገው ከኩረጃ፣ ፈተናን ከመሰረቅና ከመሳሰሉ ችግሮች ነፃ ለማድረግ እንደሆነም የትምህርት ሚኒስቴር በተደጋጋሚ ገልጿል፡፡ ፈተናዎቹን በዚህ መልኩ የመስጠቱ ጥቅም ከትምህርት ጥራት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባይኖረውም በተዘዋዋሪ ጥራት ያለውና ብቁ ተማሪ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም እንዲገባ በማድረግ በኩል ጉልህ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተናግሯል፡፡

በሌላ በኩል የፈተና አሰጣጡ ተማሪዎች በአቋራጭና በስርቆት ፈተና ማግኘት እንደ ማይችሉ ሲረዱ በሚገባ እንደሚያጠኑና መምህራንም ተማሪዎቻቸውን በሚገባ ማስተማር እንዳለባቸው በቂ ትምህርት ሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ከፈተና ስርቆት ጋር በተያያዘ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚያመጣውን የሞራል ችግርም እንደቀረፈ ተነግሯል፡፡

ይህ ሲባል ግን እንደሀገር በትምህርት ጥራት በኩል የገጠሙ ችግሮች የፈተና አሰጣጥን በማጠናከርና በመቀየር ብቻ መቅረፍ እደማይቻል የብዙዎች እምነት ነው፡፡ ትምህርት ሚኒስቴርም የፈተና አሰጣጡን በመቀየር ብቻ የትምህርት ጥራትን ማሻሻል እንደማይቻል በተደጋጋሚ አስታውቋል፡፡

ሁሉንም ሊያስማማ የሚችለው ጉዳይ ግን ፈተናው ሀገሪቷ ያለችበትን የትምህርት ጥራት ችግር በሚገባ ማሳየቱ ነው፡፡ የፈተናው ውጤት አሁን ያለውን የትምህርት ጥራት ችግር ለማሻሻል መወሰድ ያለባቸውን ርምጃዎችን በተጨበጡ ማስረጃዎች ላይ ተንተርሶ ጠቁሟል፡፡ ከዚህ በመነሳት የትምህርት ሚኒስቴር የፈተና አሰጣጥ ሥርዓቱን ከመቀየር ባሻገር በትምህርቱ ዘርፍ ያሉ ሌሎች የሪፎርም ሥራዎችን በማከናወን የትምህርት ጥራቱን ለማረጋገጥ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡

የትምህርት ሚኒትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እንደሚናገሩት የፈተና አሰጣጥ ሥርዓቱን ከመቀየር ባሻገር የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የተለያዩ የትምህርት ሪፎርም ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ አንደኛውና ዋነኛው ሥርዓተ ትምህርቱን /ካሪኩለም/ ማሻሻልና አስፈላጊ የትምህርት ቁሳቁሶችን በተለይ ደግሞ መፃህፍት ማቅረብ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት/ካሪኩለም/ ተከልሷል። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ካሪኩለም ባለፈው ዓመት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ የነበረ ቢሆንም ዘንድሮ ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉሞ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

በዚህ ዓመት የግብረ-ገብነት ትምህርት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ትመህርትም እንደዚሁ ከዚህ በፊት ከነበረው ሁኔታ የተቀየረውና በጣም አስፈላጊው በፊት የነበሩት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሆኑ መደረጋቸው ነው፡፡ በዚህም ከሚሰጠው የአካዳሚያዊ ትምህርት በተጨማሪ ተማሪዎች ከአስረኛ ትምህርት በኋላ የቴክኒክና ሙያ ትምህርቶችን የሚያገኙበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ተማሪዎችም ሁለት አይነት ክህሎት እንዲያገኙና እንደየፍላጎታቸው የአካዳሚያዊንና የቴክኒክ ትምህርቱን እንዲመርጡ ያስችላቸዋል። በዚሁ መሠረት በአንድ የክፍል ደረጃ አስራ ሶስት መፃህፍት ተዘጋጅተዋል፡፡

ሁለተኛው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል እያከናወነው ያለው ተግባር የመምህራንን ብቃትና ችሎታ እንዲሁም የትምህርት ቤት አስተዳደር በተቻለ መጠን ከምንም አይነት የፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ አውጥቶ ከትምህርት ጋር ብቻ የተያያዘ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት የትምህርት ቤቶች አስተዳዳሪዎች የሚመረጡበት መስፈርት በተቻለ መጠን በችሎታቸውና በብቃታቸው ብቻ መሆን አለበት በሚልና ይህንኑ ለማድረግ ካለፈው ዓመት መጀመሪያ አንስቶ አራት ሺህ የሚሆኑ ትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች አንድ ዓመት የፈጀ የተግባር ሥልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡ ይህ ደግሞ ለአንድ ዓመት ብቻ የሚሆን ሳይሆን ቀጣይነት ያለው ነው፡፡

የትምህርት ሚኒስቴር የዘንድሮ ትልቁ ትኩረት የመምህራንን ሥልጠናን በሚመለከት ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ በተለይ የክረምት የመምህራን ሥልጠና እንደ ካሁን ቀደሙ ዲፕሎማ ወይም ዲግሪ ለማግኘት የሚደረግ ሳይሆን ከሚያስተምሩበት ትምህርትና ከትምህርት ማበልፀጊያ ጋር የተያያዘ ብቻ እንዲሆን ተደርጎ ይሰጣል፡፡ ዩኒቨርሲቲዎችም በዚህ ክረምት ሰኔ ሰላሳ መደበኛ የማስተማር ሥራቸውን ጨርሰው በሀምሌና ነሐሴ ወራት የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ መምህራን ማሠልጠኛ እንዲሆኑ መርሃ ግብር ተይዟል፤ የማስተማሪያ ሞጁሎችም ተዘጋጅተዋል። ስለዚህ በመምህራን ብቃትና ችሎታ እንዲሁም በትምህርት ቤቶች አስተዳዳሪዎች ላይ ሥራ ይሠራል ማለት ነው፡፡

የትምህርት ሚኒስትሩ እንደሚያብራሩት የትምህርት ጥራትን ከማሻሻል አንፃር ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሶስተኛ ደረጃ የሚያከናውነው ሥራ የትምህርት ቤቶችን መሠረተ ልማት ማሻሻል ሲሆን ይህም ሥራ በጥናት የተደገፈና የተማሪዎችን ትምህርት የመቀበል አቅም ባገናዘበ መልኩ እየተከናወነ የሚገኝ ነው፡፡ ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ምቹና ሳቢ እንዲሆኑ፣ የመማሪያ ክፍሎች በጣም የተጣበቡ እንዳይሆኑ መሠረት ባደረገ መልኩና በአንድ ክፍል ውስጥ በአማካኝ ከ 40 እስከ 50 ተማሪዎች ብቻ ሊማሩበት የሚያስችል ከፍተኛ የሆነ የመማሪያ ክፍሎችን የማሻሻያ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

በዚህም ከአርከቴክት ባለሙያዎች ማህበር ጋር በመሆን ዘመኑን የዋጁ አዳዲስ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት የሚያስችል ዲዛይን የልጆች ሥነ - ልቦና ባለሙያዎችና የትምህርት ቤተሰቦችን ጭምር በማሳተፍ እንዲዘጋጅ ተደርጓል። ያሉትንና የተበላሹትን በሀገር አቀፍ ደረጃ ወደ 50 ሺ የሚጠጉ ትምህርት ቤቶችን ደግሞ ለማስተካከል ካለፈው ዓመት ሰኔ ወር ጀምሮ «ትምህርት ለትውልድ» የተሰኘ ፕሮጀክት ተጀምሯል፡፡

በዚህ «ትምህርት ለትውልድ» እንቅስቃሴ ባለፉት ሶስት ወራት ብቻ በህብረተሰቡ ተሳትፎ 14 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር የሚገመት የገንዘብ፣ የጉልበትና የቁሳቁስ ሀብት ተሰብስቧል፡፡ ወደ 3 ሺ 180 የሚሆኑ ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወደ 4 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር በሚያወጣ ገንዘብ ተሠርተዋል፡፡ አንዳንዶቹ ተሻሽለዋል፤ ሌሎቹ ደግሞ በአዲስ መልክ ተሠርተዋል፡፡ ወደ 1 ሺ 366 የሚሆኑ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተጠግነዋል፡፡ 236 የሚሆኑ አዳዲስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተገንብተዋል፡፡ ባጠቃላይ ወደ 10 ሺ 117 የሚሆኑ የትምህርት ቤት እድሳቶችና ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡

ከዚህ ባለፈ ቀደም ሲል የነበሩትን ትምህርት ቤቶችን ከማሻሻል ባሻገር አዳዲስና በተለይ ደግሞ በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት የፈረሱትን መልሶ የመገንባትና ትምህርት ቤት ያልተዳረሰባቸውን አካባቢዎች ተደራሽ ለማድረግ ትምህርት ቤቶችን በአዲስ የመገንባት ሥራዎች ተጀምረዋል፡፡ በዚህ ዓመት 50 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአፋርና በአማራ ክልል እየተገነቡ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ግማሽ ያህሉ ተጠናቀዋል፡፡ የተቀሩት ግማሾቹ በቀጣዮቹ ሶስት ወራቶች ውስጥ ይጠናቀቃሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

እነዚህም ባለፉት አራት ወራት ውስጥ የተከናወኑ ናቸው፡፡ ይህ ክንውን በዚሁ ከቀጠለና ከትምህርት ቤቶች ጋር በተያያዘ ያለውን ችግር መፍታት ከተቻለ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል ለሚደረገው ጥረት ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም 50 ሞዴል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመሥራት በተያዘው እቅድ መሠረት የአስራ ስድስቱ ግንባታ በዚህ ዓመት ተጀምሯል፡፡ በተቻለ መጠን ሀብቱ እንደተገኘ በሁሉም ክልሎች እነዚህን ትምህርት ቤቶች ለመገንባት ውጥን ተይዟል፡፡

ከሁሉም ክልል የተውጣጡና በጣም ጎበዝ የሆኑ ተማሪዎች የሚማሩባቸው በየክልሉ አንድ አንድ አዳሪ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት ቃል በተገባው መሠረት በዚህ ዓመት ስድስት አዳሪ ትምህርት ቤቶች የማስተማር ሥራ ይጀምራሉ። ከነዚህ ውስጥ ሶስቱ ወይ አራቱ በ2017 ዓ.ም ተማሪ ይቀበላሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ትምህርት ሚኒስትሩ እንደሚሉት በከፍተኛ ትምህርት ደረጃም የተለያዩ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ ዩኒቨርሲቲዎችን ራስ ገዝና ከምንም አይነት የፖለቲካ ተፅእኖ ነፃ የማድረግ ብሎም ራሳቸውን ማስተዳደር የሚችሉና ዋና ሥራቸው የትምህርት ጥራትን ማስጠበቅ ሥራ ነው፡፡ ይህም ሥራ ዩኒቨርሲቲዎችን ከቀጥታ የመንግሥት አስተዳደር ማውጣትና ራሳቸው ተወዳድረው ጎበዝ ተማሪዎችን እየተቀበሉ ማስተማር የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠርን ያጠቃልላል፡፡

በዚህ መሠረት ይህ ሥራ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተጀምሯል፡፡ በዚህም በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በርካታ የለውጥ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡ የራስ ገዝ አሠራር በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በዚህ ዓመት የተጀመረ ቢሆንም በዓመቱ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የወሰዱትን ይቀበላል፡፡ ነገር ግን በሙከራ ደረጃ በምደባ ከተቀበለው ተማሪ በተጨማሪ በተመላላሽ ከፍሎ መማር የሚፈልግ ሊማር የሚችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር ጥናት እየተደረገ ነው፡፡ ይህም ዘንድሮ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ተግባራዊ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ የወረቀት ሥራዎችም እየተከናወኑ ነው፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ በድሮው አሠራር መሠረት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ወደ 3 ሺ 200 ተማሪዎችን እንዲቀበል ተመድቦለታል። በተጨማሪም ተመላልሰው መማር የሚፈልጉ ካሉ ከፍለው ሊማሩ የሚችሉበት እድል ለመፍጠር እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ነው። ከራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ አሠራር ባሻገር ዩኒቨርሲቲዎች ሁሉም ሁሉንም የትምህርት አይነት የሚያስተምሩ ሳይሆኑ በተልእኮ እንዲለዩና በተወሰኑ የትምህርት አይነቶች ላይ ጠንካራ ሆነው እንዲፈጠሩ በተለይ ደግሞ ዩኒቨርሲቲዎቹ ካሉበት አካባቢ የሕዝብ ኑሮና የኢኖሚና ሁኔታ ጋር የሚቀራረቡ ሥራዎችን መሥራት የሚችሉ ጠንካራ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲኖሩ ለማድረግ እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡

በዚህ ዓመት እንቅስቃሴው ሥራ ላይ እየዋለ ይገኛል። ስለዚህ ዩኒቨርሲቲዎች በተልዕኮ የሚለዩ ይሆናል፡፡ አንዳንዶቹ የጥናትና ምርምር ይሆናሉ። ሌሎቹ ደግሞ አጠቃላይ ትምህርት የሚሰጡ ይሆናሉ፡፡ በዚህ መሠረት ተማሪዎችን መቀበል እንዲጀምሩ ነው እየተሠራ ያለው፡፡ ለአብነትም የኮተቤ ዩኒቨርሲቲ ሙሉ በሙሉ የትምህርት ዘርፍ ማስተማሪያ ዩኒቨርሲቲ እንዲሆን ተደርጓል። በተመሳሳይ ሌሎቹም ዩኒቨርሲቲዎች በተወሰነ ደረጃ ተማሪዎች ወደፊት የት ዩኒቨርሲቲ ሄደው መማር እንዳለባቸው ሲያስቡ ሊማሩ ከሚፈልጉት ትምህርት ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ የማድረግ እንቅስቃሴ ነው እየተደረገ ያለው፡፡

ይህ ሁሉ ባጠቃላይ እየተከናወነ ያለው ሥራ ትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ያለው የፈተና አሰጣጥ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ምንም አይነት ሚስጢር የለውም፡፡ እንደውም ፈተናው ከብዶ ሊሆን ይችላል እንዲህ አይነት ውጤት የተመዘገበው የሚለውን ብዥታ ለማጥራት በፈተናው ዙሪያ በገለልተኛ አካል ጥናት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አስጠንቶ በቀጣዩ ሳምንት በሚካሄደው የትምህርት ጉባዔ ላይ የጥናቱ ውጤትና ሪፖርት የሚቅርብ ይሆናል፡፡



# «በከተማዋ በአቅርቦቱና በፍላጎት መካከል ሰፊ ክፍተት መኖሩ የትራንስፖርት እጥረት ፈጥሯል»

-አቶ ምትኩ አስማረ
የአዲስ አበባ ከተማ ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ



አፀገነት አክሊሉ

**የኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ማህበራዊ አልፎ ተርፎም ፖለቲካዊ መረጋጋትን ከሚያሰፍኑ ነገሮች መካከል የተሳለጠ የትራንስፖርት አገልግሎት አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ በአንድ ሀገር ላይ የተሳለጠ ትራንስፖርት በኖረ መጠን የህብረተሰብ ከቦታ ቦታ የመዘዋወር ነጻነት ከማግኘቱም ባሻገር በዚህም ምክንያት ኢኮኖሚያዊ እድገቶች መመዝገባቸው እውን ነው፡፡**

**በተቃራኒው የትራንስፖርት ሁኔታ በተለያዩ ምክንያቶች ከታወከ የህብረተሰብ እንቅስቃሴ ይገታል፤ ይህ ሆነ ማለት ደግሞ ኢኮኖሚያዊ ዝውውር ስለማይኖር እድገት ይሉት ነገር የሚታሰብ አይሆንም፡፡**

**በተለይም በመዲናችን አዲስ አበባ ከህዝቡ ቁጥር ከፍተኛነት አንጻር የትራንስፖርት ጉዳይ ዋናና መሠረታዊ ነው፡፡ ይህንን መሠረታዊ የሆነ ነገር በተቻለ መጠን የህብረተሰቡን ፍላጎት ለማርካት እንደ ከተማ አስተዳደር በርካታ ጥረቶች ይደረጋሉ፡፡ ያም ቢሆን ግን በየእለቱ እየጨመረ ከሚመጣው የሕዝብ ቁጥር አንጻር አሁንም ድረስ የትራንስፖርት ጉዳይ የተመለሰ ጥያቄ ሲሆን አልቻለም፡፡**

**በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ያለው የትራንስፖርት እጥረት ህብረተሰቡ ሳይወድ በግድ ረጃጅም ሰልፎችን ይዞ ጊዜውን በጎዳናዎች ላይ እንዲያጠፋ እያስገደደው ነው፡፡ እኛም በከተማ ደረጃ ያለውን የትራንስፖርት ሁኔታ አስመልክተን ከቢሮው ሃላፊ ከአቶ ምትኩ አስማረ ጋር ቆይታን አድርገናል፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- የአዲስ አበባ ከተማ ትራንስፖርት ቢሮ ሥልጣንና ሃላፊነትን በማንሳት እንጀምር፤የተሰጠው ሥልጣንና ሃላፊነት እስከ ምን ድረስ ነው ?**

**አቶ ምትኩ ፡-** ትራንስፖርት ቢሮው በአዋጅ 1074 /2014 መነሻነት አጠቃላይ የከተማዋን ትራንስፖርት እንዲመራ እና እንዲያስተባብር የተቋቋመ ሲሆን በስሩም የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ፤ የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ቁጥጥር ባለሥልጣን፣ የቀላል ባቡር አገልግሎት ድርጅትና የከተማ አውቶቡስ ድርጅት ይገኛሉ፡፡

እነዚህን ቀላቅሎ የሚገኝና በከተማ አስተዳደሩም ከፍተኛ የሆነ በጀት የተበጀተለት እና 12ሺ አካባቢ ሠራተኞችን የሚያስተዳድር ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ትራንስፖርት ቢሮ የከተማዋን አጠቃላይ የትራንስፖርት ዘርፍ ስምሪትና ቁጥጥር ይሠራል፤ በዚህም 11 ቅርንጫፎች በየክፍለ ከተሞቹ አሉት ፤ የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲም በከተማዋ ያለውን የትራፊክ ፍሰትና ደህንነት በ 11 ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶቹ አማካይነት ይቆጣጠራል፡፡ የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥጥር ባለሥልጣንም አጠቃላይ የመንጃ ፍቃድ አሰጣጥ ሥርዓቱን የተሽከርካሪ ምዝገባና ቁጥጥሩን እንዲሁም ደህንነቱን በ12 ቅርንጫፎቹ በመቆጣጠር ላይ ይገኛል፡፡ ቢሮው እነዚህን አቀናጅቶ በመያዝ ነው የከተማዋን የትራንስፖርት ዘርፍ እየመራ ያለው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ ልክ በትራንስፖርት ዘርፉ ላይ እየተሠራ ካለው ሥራ አንጻር ከስፋቱም የተነሳ የሚታዩ ችግሮች ምንድን ናቸው?**

**አቶ ምትኩ፡-** እንደ ከተማ የትራንስፖርት ፍላጎቱ እለት በእለት እየጨመረ ባለበት ሁኔታ እንዲሁም ከተማዋ ከእለት እለት እየሰፋች ከመምጣቷ ጋር ተያይዞ የትራንስፖርት ፍላጎቱም በጣም ሰፊ መሆኑ ለማንም የሚደበቅ አይደለም፡፡ ከዚህ አንጻር ቢሮው ዘርፉን በአግባቡ ለመምራት ከፍ ያለ ጥረትን የሚያደርግ ቢሆንም የአቅርቦትና ፍላጎት መጠኑ የተስተካከለ አለመሆኑ ከፍተኛ ተግዳሮት ነው፡፡

ለምሳሌ በዚህ ዓመት 3 ነጥብ 2 ሚሊዮን ጉዞዎችን በቀን እንፈጥራለን ብለን አቅደን ነበር።ይህንንም እቅድ እንግዲህ ባሉን ባሶች ታክሲዎች ሀይገርና በተለምዶ ቅጥቅጥ የሚባሉትን እንዲሁም ባቡርን ተጠቅመን ነው፡፡ በዚህም ግቡን ያሳካን ቢሆንም የሚፈለገው ግን ከ 4 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ጉዞዎች በቀን ማድረግ ነው፡፡

ይህንን ስል ምን ለማለት ፈልጌ መሰለሽ እንደ ከተማዋ ነዋሪነቱ ሕዝቡ በእግር መሄድን ሳይቀር የትራንስፖርት አማራጭ አድርጎ እየተጠቀመ ነውና ይህ ሲጨመር በጣም ሰፊ ይሆናል፡፡ ግን ደግሞ እኛ እንደ ቢሮ የምናቀርበው የትራንስፖርት አማራጭና የሕዝቡ ፍላጎት ሲነጻጸር ሰፊ ርቀቶች አሉ፡፡ በመሆኑም ለከተማዋ ትራንስፖርት ትልቁ አስቸጋሪ ሁኔታ የፍላጎትና አቅርቦት የተመጣጠነ አለመሆን ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በከተማዋ በተለይም በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ላይ ረጃጅም ሰልፎችን መመልከት የተለመደ ሆኗል፡፡

**አዲስ ዘመን ፡- እዚህ ላይ ግን የአቅርቦትና ፍላጎት አለመመጣጠን ከባድ ችግር እንደሆነ ተስማምተናል፤ ነገር ግን ያሉንንስ የትራስፖርት አማራጮች በትክክ ለኛው ወይም ችግሩን በሚያቃልል መልኩ አሰማርተን እየተጠቀምንበት ነው ማለት ይቻላል?**

**አቶ ምትኩ፡-** ያሉንን የትራንስፖርት አማራጮች ከማስተካከል በአግባቡ ከመጠቀም አንጻር ሁለት ነገሮች ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ አንደኛው የምልልሱ ሁኔታ ሲሆን አንድ የትራንስፖርት አማራጭ አንድ ቦታ ደርሶ ለመመለስ የሚወስድበት ጊዜ መንገዶች ስለሚዘጋጉ ይዘገያል ፤ ይህ ደግሞ ምልልሱ ላይ ከፍ ያለ ጫናን ያሳድራል፡፡ በመሆኑም የቁጥጥሩ ማነስ እንደተጠበቀ ሆኖ በመንገድ መዘጋጋት ምክንያት ቶሎ ቶሎ ተመላልሰው ሰውን አለማንሳታቸው ችግሩን ያሰፋዋል።ሌላው ያሉንን ትራንስፖርት አማራጮች በአግባቡ ከማስተዳደር አኳያ የቴክኖሎጂ ሥርዓቶችን በአግባቡና በስፋት እየተጠቀምን ካለመሆኑ ጋር እስከ አሁንም ሥራዎች ሰዎች ስለሚሠሩ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ ከመሠረተ ልማት ጋር የተያያዘው ችግርም ሌላው ነው። ትራንስፖርት ስንል ብቻውን የሚሄድ ነገር አይደለም፤ የተሻሉ አውቶቡሶች እንዲወጡ ብዙ ዴፖዎች ያስፈልጉናል፤ ህብረተሰቡም ተረጋግቶ ትራንስፖርት ሊጠብቅባቸው የሚችል ተርሚናሎች ያስፈልጋሉ፡፡ ከዚህም ባለፈ ራሳቸውን የለዩ መንገዶች ያስፈልጋሉ፡፡ የመቆሚያ ቦታዎችም ያስፈልጋሉ፤ እንግዲህ እነዚህ ሁሉ እጥረቶች ናቸው ችግሮቹን እያባባሱ ያሉት፡፡

በሌላ በኩል አንድ ቦታ መንገድ መዘጋጋት ካለ መኪኖች በየቦታው ይቆማሉ፤ ይህ ደግሞ የሚያወጡት የተቃጠለ ጭስ አየሩን ለብክለት ይዳርገዋል፡፡ በመሆኑ ዘርፉ ለአየር ብክለትም የራሱ ድርሻ እያበረከተ ነው ማለት ይቻላል፡፡ እንደ ከተማ አብዛኛው ተሽከርካሪዎቻችን 20 እና ከዚያ በላይ ዓመታትን ያስቆጠሩ በመሆናቸው እንደ ልብ ተንቀሳቅሰው እንዳይሠሩ አብዛኛውን ጊዜያቸውን በጋራዦች አካባቢ እንዲያሳልፉም ያደርጋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ችግሮቹን ስመፍታትስ ከተማ አስተዳደሩ ምን ዓይነት ርምጃዎችን እየወሰደ ነው?**

**አቶ ምትኩ፡-** ችግሮቹን ለመፍታት እንደ መንግሥትም ሆነ እንደ ከተማ አስተዳደር በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው፡፡ ባለፈው በጀት ዓመት ብቻ ወደ 310 አውቶቡሶች ተገዝተዋል፡፡ በነገራችን ላይ ለእኛ አንድ አውቶቡስ በቀን እስከ 1 ሺ ሰዎችን ነው የሚያጓጉዘው ፤ 310 አውቶቡሶች ተገዙ ስንል 310 ሺ አዳዲስ ሰዎች ይጓዛሉ ማለት ነው። በመሆኑም ይህ አካሄዳችን አቅርቦትን ለማሳደግ ነው፡፡

በተጨማሪም በዚህ በጀት ዓመት 67 አውቶቡሶች አስገተብተናል፡፡ አሁን ላይም የሚያስፈልጋቸውን ህጋዊ ሂደት እየጨረሱ በመሆኑ በቅርቡ ወደአገልግሎት ይገባሉ፡፡ አቅርቦትን ከማሳደግ አንጻርም የሚኖረው ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም፡፡

በሌላ በኩልም የጥገና አቅማችንን በከፍተኛ ሁኔታ ማሻሻል ሲሆን የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት የተለያዩ ዲፖዎች ያሉት ቢሆንም የተሻለ ሥራን መሥራት እንዲችሉ የጥገና አቅማቸው ተጠናክሮ አንድም ባስ እንዳይቆም የማድረግ ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በአሁኑ ወቅት በአማካይ 138 ገደማ ባሶች በቀን ወጥተው አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን ከእነዚህ ምክንያት ደግሞ 1 ሚሊዮን የሚጠጋ ተጓዥ አገልግሎቱን እያገኘ ነው፡፡

አቅርቦትና ፍላጎት ሊጣጣምበት ከሚችለው መንገድ ሌላው የቁጥጥር አቅምን ማሳደግ በመሆኑ እንደ ቢሮ ከ አራት መቶ በላይ የሚሆኑ ተቆጣጣሪዎች አሉን፤ እነሱን በሁለት ፈረቃ በማሰማራት በተለይም መነሻና መድረሻ ቦታዎች ላይ በተቻለ መጠን ቁጥጥር እንዲያደርጉ የታክሲውን አገልግሎት አሰጣጥ ለማሳለጥ ይሠራል፡፡

እንደ ከተማ ይህ ሥራ ያስፈለገውን ባለን መረጃ መሠረት የከተማዋ የትራንስፖርት እንቅስቃሴ ከ 69 በመቶ በላይ በታክሲዎች የሚሸፈን በመሆኑ ሲሆን እነዚህ ታክሲዎች ህብረተሰቡን በአግባቡ እንዲያገለግሉ ከማስቻል አንጻር የቁጥጥር ሥራው ይደረጋል፡፡ ያሉንንን አውቶቡሶችም በተገቢው ሁኔታ ተመላልሰው አገልግሎት እየሰጡ ነው፡፡ በዚህም ወደ ስድስት የሚሆኑ የተለዩ መስመሮችን በማዘጋጀት መስመሮቹ ባሶች ብቻ ቅድሚያ አግኝተው የሚመላለሱባቸው እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው፡፡

ከዚህ ባለፈ ግን ችግሩን ለመቅረፍ መሠረተ ልማትን ማስፋፋት አይነተኛ መንገድ በመሆኑ የከተማ ባሶቹ የሚገለገሉበት የሸጎሌና የቃሊቲ ዴፖዎች እንዳሉ ሆነው ሌላ ተጨማሪ መካኒሳ ላይ ትልቅ ዴፖ ለማስገንባት ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ምክንያቱም የተሻሉና ደህንነታቸው የተጠበቁ አውቶቡሶች ከሌሉን ህብረተሰቡን በአግባቡ ማስተናገድ አንችልም፤ ከዛም ባለፈ ደግሞ የትራፊክ ፍሰቱን ሰላማዊ ከማድረግ አንጻር ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እናንተ ተቆጣጣሪዎችን አሰማርታችሁ ከምትሠሩት ሥራ ባሻገር ግን ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር የተራመዱ ሥራዎችን በመሥራት በኩል ያለው ነገር ምን ይመስላል?**

**አቶ ምትኩ፡-** የትራፊክ ፍሰቱን ሰላማዊና የተረጋጋ ለማድረግ የቁጥጥር ሥራም ለመሥራት መገናኛ ላይ ትልቅ የትራፊክ ማኔጅመንት ሴንተር በማስገንባት ላይ ነን። ከጥቂት ጊዜያት በኋላም ቢሮ ቁጭ ብለን አጠቃላይ የትራንስፖርት ሥርዓቱን ማየት የምንችልበት ሁኔታ ይፈጠራል።

**አዲስ ዘመን ፡- በካሜራ ማለት ነው?**

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# «በከተማዋ በአቅርቦቱና በፍላጎት...

ከ ገጽ 9 የዞረ

**አቶ ምትኩ፡-** ያው የመቆጣጠሪያ ማዕከል ነው። ከመንገድ ላይ ከካሜራዎች እንዲሁም ከሌሎች አማራጮች መረጃዎችን ይወስዳል። በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ የትራፊክ ፍሰቶች የሚታወኩት መጋጠሚያ መንገዶች ላይ ከመሆኑ አንጻር ቅድሚያ ማግኘት ያለበትን እያየን የምንሠራው ሥራ አለ፡፡ አሁን ላይ የቤቱ ግንባታ በመጠናቀቅ ላይ ሲሆን ወደታች አራት ወለል አለው ሰፊ በጀትም ነው የወጣበት፤ በመሆኑም በቀጣይ ፍሰቱን ከማስተካከል አንጻር ውጤታማ ያደርገናል ብለን እናስባለን፡፡

ይህ አይነቱ አሠራር ደግሞ በሌሎች ሀገሮች የተለመደ ከመሆኑም በላይ እኛም የአንዳንድ ሀገሮችን ተሞክሮ አይተናል በመሆኑም አሁን ላይ ያለንበትን ችግር ከማቃለል አንጻርም ሚናው በቀላሉ የሚታይ አይሆንም፡፡ በመጀመሪያው ዙር ወደ 99 መገናኛዎች ይሠሩና በቀጣይ ደግሞ መንገድ ላይ መቆምን የሚከታተል ቅድሚያ ለባሶች የሚሰጥ የሚቆጣጠር እና አደጋዎች ሲደርሱም በቶሎ ምላሽ እንዲያገኙ የሚያደርግ ይሆናል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ህብረተሰቡ ከቤቱ ከመውጣቱ በፊት በየትኛው መንገድ ቢሄድ ይሻለኛል የሚለውን መረጃ የሚሰጥ ነው፡፡

ሌላው ቢሮው ትልቅ ሃላፊነት ያለበትና በርካታ ሥራ የሚሠራበት ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ለዋና መሥሪያ ቤትነት የሚሆን 20 ወለል ያለው ህንጻ በመገንባት ላይ ነው፡፡ ይህ ሲጠናቀቅ ደግሞ ተበታትነው ያሉ ቢሮዎችን በአንድ አሰባስቦ የተወሰኑ ክፍለ ከተሞችም አብረውት የሚሆኑበትን ሁኔታ ስለሚፈጥር ምቹ የሥራ አካባቢን ይፈጥራል፡፡ ህብረተሰቡም በአንድ ቦታ ሁሉንም አገልግሎቶች ማግኘት የሚችልበት አጋጣሚ ይሰፋል፡፡ ይህ የሚያሳየው ደግሞ ከተማ መስተዳድሩ ለትራንስፖርቱ ዘርፉ የሰጠውን ልዩ ትኩረት ነው።

ይህ የቴክኖሎጂ ሁኔታ ደግሞ በማጠናከር ከዓለም ባንክ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎትን ማዘመን ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ይህም ሲባል የአውቶቡሶቻችንን አጠቃላይ እንቅስቃሴ መቆጣጠር የሚያስችል ነው፡፡ አሁን በሙከራ ላይ ባለበት ሁኔታ እንኳን ባሶቹ የትና በምን ሁኔታ ላይ ነው የሚውሉት የሚቆሙት የሚለውን በጫናቸው ሁለት መቶ ገደማ ካሜራዎች ለማየት ችለናል። በቀጣይም ወደካርድ ሥርዓት ለመግባትም እየሠራን ነው፡፡ እነዚህ ሥራዎች ሲጠናቀቁ ደግሞ የቁጥጥር ሥራችን ውጤታማ ከመሆኑም በላይ የስምሪት ሥርዓታችንም የተሻለ ስለሚሆን እነዚህ ሥራዎችን አጠናክረን እንቀጥላለን።

**አዲስ ዘመን ፡- አዎ በተለይም ስምሪት ላይ ከፍ ያለ ችግር ያለ ይመስላል ፤ ይህንን ያልኩበት ዋና ምክንያቴ ደግሞ አንዳንድ መስመሮች ተሳፋሪ የለም ግን ደግሞ ትራንስፖርት አማራጩ ብዙ ነው ሌሎች ላይ ሰው ይበዛል ግን ደግሞ ትራንስፖርት የለምና ቴክኖሎጂው እነዚህንም ያስታርቃል የሚል እምነት ያለ ይመስለኛል እርስዎ ያሉት ከገባኝ?**

**አቶ ምትኩ፡-** አዎ አሁን አውቶቡሶቻችን ላይ በጀመርነው ክትትል ምሳ ሰዓት ሻይ ምናምን ብለው ይደበቃሉ እሱን ሁሉ ማየት ችለናል ፤ሌላው ተጓዡ የት አካባቢ ይበዛል ? የሚለውንም እያየን ነው። አሁን ላይ አሠራራችን በሰው ስለሆነ ምደባ ላይ ከፍተኛ ክፍተቶች አሉ፡፡ ይህንን ለማመጣጠን ደግሞ ቴክኖሎጂው አቅም ይሆነናል፡፡ ሌላውና ዋናው ግን ለህብረተሰቡ መረጃ መስጠት ነው፡፡ አሁን ላይ እንኳን ሶስት ቦታዎች ላይ ለህብረተሰቡ በተለይም የአውቶቡሶችን መዳረሻ ሰዓት የማሳወቅ ሥራ ተጀምሯል፡፡ በመሆኑም ለህብረተሰቡ የሚፈልገው ባስ በዚህ ሰዓት በዚህ ደቂቃ እዚህ ትደርሳለች የሚል መረጃ መስጠት እየሠራን ነው፡፡

በመሠረቱ ሥራው ቀላል አይደለም ግን ደግሞ



ወደዘመናዊነቱም መሄድ ስላለብን እየሠራን ነው፡፡ እነዚህን ከሠራን ደግሞ ችግሮቹን መፍታት እንችላለን የሚል እምነት አለን፡፡ መንግሥት ዘርፉን ለማሳደግ አቅሙ የፈቀደውን ሁሉ እያደረገ ቢሆንም በተለይም የግል ባለሀብቶች በትራንስፖርት ዘርፍ መሠማራት መቻል አለበት፡፡ የእነሱ መግባት ደግሞ ዘርፉን ውጤታማ ያደርገዋል፡፡

በሌላ በኩል እስከ ዛሬ ስንጠቀምበት የነበረውን የትራንስፖርት አጠቃቀም ልምምድ ማሻሻል ይገባል። በተለይም ለአጭር ኪሎ ሜትሮች መሰለፍን በማቆም ትንሽ መንገድ በእግር በመጓዝ ብስክሌትና ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም ሁኔታውን ማመቻቸት ይገባል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የከተማዋን ትራንስፖርት ከሚያውኩ ነገሮች መካከል የመኪና ማቆሚያዎች (ፓርኪንጎች) ናቸውና እንደው እነሱን ዘላቂ መፍትሔን የሚያገኙበትን መንገድ ከመፍጠር አንጻር የተሠራው ሥራ ምን ይመስላል?**

**አቶ ምትኩ፡-** አዎ መሠረተ ልማት ለትራንስፖርት መሳለጥ አይነተኛ ሚና ያለው ነው። ይህንንም በመረዳት የካ ላይ እየተገነባ ያለ ትልቅ የመኪና ማቆሚያ አለ። ወደላይ ሶስት ወደታች ሁለት አምስት ወለል ያለው ነው፡፡ በዚህም 910 ተሽከርካሪዎችን በቀላሉ የሚይዝ ነው፡፡ ይህም መንገድ ላይ ከመቆም ጋር ተያይዞ ያሉትን ችግሮች በመቅረፍ በኩል አይነተኛ ሚና ይኖረዋል። ሌሎችም በዚህ አይነት መልኩ የሚሠሩ ሥራዎች ይኖራሉ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ሰዎች የሚፈልጉትን ትራንስ ፖርት በችግርና ከብዙ ጥበቃ በኋላ አግኝተው እንኳን መንገድ ስለሚዘጋጋ ጊዜያቸውን መንገድ ላይ ለማጥፋት ይገደዳሉ ከዚህ አንጻር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሠራር ምን መልክ አለው?**

**አቶ ምትኩ፡-** ብዙ መንገዶች የሉንም ማለት አይቻልም ፤ መንገዶች አሉን፤ ከዚህ ይልቅ እንደውም የውስጥ ለውስጥ መንገዶቻችን ብዙ አይደሉም፤ አብዛኛው ሰውም የሚሄደው በዋና መንገድ ላይ ብቻ ነው፤ የምንወጣባቸውም ሰዓቶች ተመሳሳይ ናቸው። ይህ አጠቃቀማችን ደግሞ በመንገዱ ላይ ጫና ይፈጥራል ፤ መጨናነቁም ይመጣል፡፡ በመሆኑም የሚችል ሰው ቀደም ብሎ ቢወጣ አንደኛ ለመንገዱ ሰላማዊነት ሁለተኛ ለራሱም ያሰበበት በሰዓቱ ከመድረስ አንጻር ሚናው ከፍተኛ ነው፡፡

በቅንጅት ከመሥራት አንጻር በተለይም ወሳኝ ሰዓት በሚባሉት ጠዋትና ማታ ላይ ከተፈቀደላቸው የጭነት ተሽከርካሪዎች ውጪ እንዳይንቀሳቀሱ የማገድ ሥራ ተሠርቷል፡፡ ሌላው ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ በቢሮው ስር የሚገኝ ተቋም ነው ከእርሱም ጋር በአግባቡና በቅንጅት እየሠራን ነው፡፡ ከመንገዶች ባለሥልጣን ጋርም ጥሩ የሥራ ግንኙነት ፈጥረን ተናበን እየሠራን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የትራንስፖርት ችግርን ይፈታል ተብሎ እምነት ከተጣለበት አንዱ ቀላል ባቡር ነውና እንደው አሁን ባለው ሁኔታ ለትራንስፖርት ችግሩ መፍትሄ ሆኗል ማለት ይቻላል?**

**አቶ ምትኩ፡-** ከቀላል ባቡር ወደከተማ አስተ ዳደሩ ከገባ አንድ ዓመት ሆኖታል ፤ ባቡሩ ወደሥራ ሲገባ 41 አካባቢ ፉርጎዎች ነበሩት ፤ በእነዚህ ፉርጎዎች ደግሞ በቀን እስከ 120 ሺ ሰዎች ያጓጉዟል ተብሎ ነው የተጀመረው፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜም ጥሩ ግልጋሎትን ሰጥቷል ፡፡

ባቡር ሰፊ ጥቅም ያለው ነው በተለይም ምንም አይነት የትራፊክ መጨናነቅ የማያግደው ከመሆኑ አንጻር ብዙ የህብረተሰብ ክፍሎችን በአንዴ የሚያነሳ ረጃጅም ርቀቶችን የሚጓዝ በመሆኑ ጥቅሙ ብዙ ነው፡፡ ነገር ግን ከጥገና ከመለዋወጫ ጋር የተያያዙ ችግሮች አሉበት። የጥገና አቅምም ሌላው ችግሩ በመሆኑ በተለይም ከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ከገባ በኋላ ባቡሩ በሙሉ አቅሙ እንዲሠራ ለማድረግ ብዙ ሥራዎች እየተሠሩ ሲሆን የቻይናንም ድጋፍ አግኝተናል፤ መለዋወጫዎችም እየመጡ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ሰባት አዳዲስ ባቡሮች ወደሀገር እንዲገቡ የማድረግ ሥራውም እየተሠራ ነው፡፡ እንደ ከተማ አስተዳደር ደግሞ አጠቃላይ ጥገናውን የተሻለ ቀጣይና ዘላቂ እንዲሆን ለማድረግ ሰፊ ሥራዎች በመሠራቱ በቀጣይ በሙሉ አቅሙ ወደሥራ የሚገባበት ሁኔታ ይፈጠራል።

በጠቅላላው የባቡር ትራንስፖርት ለሀገር ኢኮኖሚ ሰፊ ድጋፍ ያለው ከመሆኑ አንጻር የተሻለም ትኩረት ቢያገኝ ረጅም ርቀት ከመሄዱ የምንመድበውን የትራንስፖርት አገልግሎት ወደሌሎች መስመሮች ለማዞር ስለሚጠቅምን በመኪና የሚመጣውም ሰው ባቡርን ተጠቅሞ የመንገድን መጨናነቅ እንዲቀንስ በማስቻሉ በኩል ሚናው የጎላ ስለመሆኑ መታወቅ ይኖርበታል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ከተማ የትራንስፖርቱን ፍሰት የሚያሳልጡ ተርሚናሎች ግንባታ ብዙ ትኩረት አልተሰጠውም፤ ለምንድ ነው?**

**አቶ ምትኩ፡-** እንደ ከተማ ብዙና ሰፋፊ ተርሚናሎች ያስፈልጉናል፤ አሁን ባለው ሁኔታ ጥሩ ተርሚናል ያለን መርካቶ ላይ ነው፡፡ ይህ ተርሚናል በቀን 5 ሺ ያህል ሰዎች ያስተናግዳል ሰዎች ቁጭ ብለው ነው አገልግሎት የሚያገኙት ንጽህናው የተጠበቀ ነው፡፡ ልክ እንደዚህ ሁሉ ሌሎችንም ማገንባት ያስፈልጋል፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ ግን ተርሚናሎች ብለን የምንላቸው የታክሲ መጫኛና ማውረጃ ቦታዎችን ነው። ህብረተሰቡ ይንገላታል ልክ ነው ግን ደግሞ ከአንዱ ተርሚናል ወደሌላው ለመሄድ ቢያንስ አምስት መቶ ሜትር ቢሆን ነው፡፡ ይህንን ጉዞ በቀን ውስጥ ማድረግ ደግሞ ይመከራል፡፡ ግን ደግሞ ችግሮቹን ለመፍታት የተርሚናል ግንባታዎች ያስፈልጉናል ለምሳሌ መገናኛ ተርሚናልን ለመገንባት እቅድ አለ ፤ በቀጣይም ሌሎችን እየገነባን ችግሮቹን ለማስተካከል እንሞክራለን።

ለጊዜው ግን መዳረሻ ቦታዎችን ተቀራራቢ በማድረግ ሰዎች እንዳይንገላቱ ማድረግ ጊዜያዊ መፍትሔዎችን የመስጠት ሥራ እንሠራለን፡፡

**አዲስ ዘመን ፡-አሁን በቅርብ ጊዜ ውስጥ ቢሯችሁ የመንገዝ በተለይም ለታክሲዎች የታሪፍ ማሻሻያ አድርጓል፡፡ አንዳንድ አስተ ያየት ሰጪዎች የተደረገው ማሻሻያ በጣም የበዛ ነው ይላሉና በዚህስ ላይ ያልዎት አስተያየት ምንድን ነው?**

**አቶ ምትኩ፡-** በቢሮው የሚሠሩ ሥራዎች ታሪፍን ጨምሮ በጥናት የተደገፉ ናቸው ፤ የህብረተሰቡንም የኑሮ ሁኔታም ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ ነገር ግን አሁን ልንነጋገር የሚገባው ታሪፉ ላይ ሳይሆን ታሪፉን በአግባቡ የማስፈጸም የቁጥጥር ሥራው ላይ ነው። በቅርቡ የጨመርነው ታሪፍ የከተማ አውቶቡስንና ባቡርን የሚመለከት አይደለም፡፡ በመሆኑም አማራጭ እየፈጠርን ነው ማለት ነው፡፡

አሁን እኛ ጋር በተደጋጋሚ እየመጣ ያለው ታክሲዎች በተጨመረላቸው ታሪፍ መሠረት እየሠሩ አይደለም የሚል ነው፡፡ ቢሮው እንግዲህ ከላይም እንዳነሳሁልሽ የቁጥጥር ሥራውን በሰዎች አማካይነት በሁለት ፈረቃ እየሠራን ነው፡፡ ነገር ግን ህብረተሰቡም በራሱ ግዴታውን ተወጥቶ መብቱን መጠየቅ ይገባዋል ይህ ሲሆን ደግሞ የጋራ አቋም መያዝ ቢቻል ብዙ ለውጦች ይመጣሉ፡፡

እኛ ደግሞ ህብረተሰቡን ብቻህን ተጋፈጥ ሳይሆን ያልነው በልዩ ሁኔታ ታሪፉ በታክሲው ውስጥ እንዲለጠፍ መለጠፍ ብቻም ሳይሆን ታርጋ ቁጥሩም አብሮ እንዲካተት የማድረግ ሥራ እየሠራን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም እንደዚህ አይነት ችግር ያጋጠመው ሰው ወደ 9417 ላይ በነጻ ስልክ በመደወል መረጃ መስጠት ይችላል፡፡

ከሁሉም በላይ ግን በተለይም የታክሲ አሽከርካሪዎች ሥራቸውን ሲያከናውኑ ፍጹም ሥነ ምግባር የተላበሱ ሊሆን ይገባል። በአንጻሩ ተገልጋዩም ገንዘብ ከፍያለሁ በሚል ብቻ ከሥነ ምግባር ውጪ የሆኑ ተግባራትንም ሊፈጽም አይገባም፡፡

ቢሮው በያዝነው በጀት ዓመት ብቻ 21ሺ ገደማ ቅጣቶችን ቀጥቷል፡፡ ያለን ታክሲ 14 ሺ አይደርስም ቅጣቱ ግን ደብል ነው፡፡ ይህም አሠራር አስተማሪ ስላይደለ ቢሮው ቅጣቱን ጠንካራ ከማድረግ ጎን ለጎን የማስተማርና ልዩ ፍቃድን ለመስጠት በዝግጅት ላይ ነው፡፡

ለምሳሌ አንድ ሰው በትራንስፖርት ዘርፉ ላይ ለመሠማራት ከፈለገ ግዴታ የኦፕሬተርነት ፍቃድ ያስፈልገዋል እያልን ነው፡፡ መንጃ ፈቃድ ስለያዘ ብቻ ታክሲ አይነዳም፡፡ ይህንን ሳብራራልሽ ኦፕሬተርነት ሲባል ቢሮው አሠልጥኖ የሚሰጠውን ልዩ ፍቃድ መያዝ የግድ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ሰውም ለተጋነነ የትራንስፖርት ወጪ እንዳይዳረግ የብዙሃን ትራንስፖርትን ማሳደግ ትልቅ መፍትሔ ነው፡ ፡ ምክንያቱም አንበሳ አውቶቡስ ላይ ከታሪፍ በላይ ተጠየቁ ብሎ ቅሬታ የሚያሰማ ሰው የለም፡ ፡ በመሆኑም ይህንን ማሳደግ ይገባል ፤ እኛም የተባሉትን ችሮች ሁሉ ለማቃለል እየሠራን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ።**

**አቶ ምትኩ ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## በልጆቻቸው አደራ ተረካቢነት የዘመነው የአባት የሽመና ሙያ

ወርቅነሽ ደምሰው

ወጣት ሃያት ጀማል ትባላለች፡፡ ትውልድና እድገቷ በጎንደር ከተማ ነው፡፡ በሀገር ባህል አልባሳት ሥራ ላይ የተሰማራችው ሃያት ሙያውን ከአባቷ ነው የቀሰመችው። አሁንም ከአባቷ እና ከወንድሟ ጋር በመሆን ሙያውን በማዘመን ለማሳደግ ጥረት እያደረገች ትገኛለች፡፡ ‹‹ሃያት እና አብዱልቃድር ዘመናዊ የሽመና ሥራ›› የተሰኘ ድርጅት በመክፈት ከአባቷና ከወንድሟ ጋራ ባሕላዊ አልባሳትን እያመረቱ ይገኛሉ፡፡

የእነ ሃያት አባት በሙያው ላይ ረጅም ጊዜ ቆይተዋል፤ በሽመና ሥራዎች አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎችን በመሥራት የተለያዩ ባህላዊ አልባሳትን በተለያዩ ዲዛይኖች ሲሠሩ እንደነበር ሃያት ታስታውሳለች። ‹‹የኛን ቤተሰብ ለየት የሚያደርገው የምንጠቀመውን እያንዳንዱን ልብስም ሆነ ቁሳቁስ ራሳችን የምንሰራቸው ናቸው›› የምትለው ሃያት፤ ተማሪዎች እያሉ አባታቸው የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም) ሳይቀር ከሸማ ውጤቶች ያዘጋጁላቸው እንደነበር ታስታወሳለች፡፡ አልባሳቱን ከትምህርት ቤቱ የደንብ ልብስ ጋር እንዲመሳሰሉ አድርጎ ከነቦርሳው ጭምር በሽመና ይሠራልን ነበር›› ስትል ትገልጻለች፡፡

እነ ሃያት የሽመና ሥራውን ከ12 ዓመታት በላይ ቆይተውበታል። ከአባታቸው የወረሱትን ይህን የሽመና ሥራ በማስቀጠል ዘመናዊ አድርገው እየሠሩ እንደሆነ ሃያት ትናገራለች፡፡ ከልጅነቷ ጀምሮ እያየች ያደገችው የአልባሳት ሥራ ዲዛይነር የመሆን ፍላጎት እንዲያድርባት እንዲመጣም አድርጓል፤ ሙያውን በወረቀት ላይ ሳይሆን በቀጥታ በጨርቅ እየተለማመደች ሙያውን እያዳበረች መምጣቷን ትገልጻለች ፡፡

ሃያት የሽመና ሙያውን በማስቀጠል ከትውልድ ወደ ትውልድ የማስተላለፍ ኃላፊነት እንዳለባት ታምናለች፡፡ ከወንድሟ ጋር በመሆን የአባቷን ሙያ በማስቀጠሏም ደስተኛ ናት፡፡ ‹‹ሙያው ላይ የቆየ ልምድ ያለው አባቴ ቢሆንም፣ እኔና ወንድሜ ደግሞ ወጣቱ ምን ይፈልጋል? በምን መልኩ ቢሠራ ለየት ያሉ የፋሽን አልበሳትን መሥራት ይቻላል? የሚለው ላይ ትኩረት አድርገን አብረን ሆነን እንሠራለን፤ ለዚህም እኛ የምንለብሳቸው ልብሶች ሁሉ ዘመኑን የተከተሉ የፋሽን አልባሳት ናቸው›› ትላለች፡፡

‹‹በባህላዊ ሽመና የተዘጋጁ አልባሳት ሲባል ቶሎ ብሎ ወደ አእምሮአችንን የሚመጣው በዓላትን ጠብቀን የምንለብሳቸው የሀበሻ ልብሶች ናቸው›› የምትለው ሃያት፤ የሸማ አልባሳትን ለሁልጊዜም እንዲሆኑ አድርጎ በዘመናዊ መልኩ መሥራት እንደሚቻልም



ድርጅቱ የባህል አልባሳትን በዘመናዊ መንገድ እያዘጋጀ ለገበያ ያቀርባል፣

ጠቁማለች፡፡ ድርጅታቸው በአሁኑ ወቅት አልባሳት፣ ቦርሳዎች፣ አልጋ ልብሶች፣ መጋረጃዎች፣ የጠረጴዛ ልብስ፣ የመኪና ወንበር ልብስ እና ጫማዎችም በዘመናዊ መልኩ እየሠራ ለገበያ ያቀርባል፡፡

ድርጅታቸው የሀበሻ አልባሳትን ዘመናዊ ሆነው ሁሉም ሰው ወዶ የሚለብሳቸው እንዲሆኑ በማድረግ ይሰራቸዋል፡፡ ሙሉ ቀሚስ፣ ጉርድ፣ አጭር ቀሚስ፣ ሱሪ፣ የእስልምና እምነት ተከታዮች የሚለቡሷቸው ጀለቢያና ሙሉ ለሙሉ ጀለቢያ፣ ፓኪስታን ሻል የሚባል ሙስሊም ወንዶች ከጀለቢያ በላይ የሚለብሱት ልብስና የመሳሰሉትም ድርጅቱ ከሚያመርታቸው መካከል ይጠቀሳሉ፡፡

በድርጅቱ ጥራት ያላቸው የሽመና ምርቶች እንደሚሠሩ የምትገልጸው ሃያት፣ እነዚህም ምርቶቹ የፋብሪካ ምርቶችን ሊተኩ የሚችሉ እንደሆኑ ነው የተናገረችው፡፡ ጥራታቸውን የጠበቁ መሆናቸው ከሀገር ውስጥ ገበያም አልፎም ተርፎ ለውጭ ገበያ እንደሚመጥኑ ትገልጻለች፡፡

አባታቸውም ወደ ሙያው ሲገቡ የሽመናና የልብስ ስፌት ሥልጠና ወስደው እንደነበር አስታውሳ፣ ይህም አዳዲስ የፈጠራ ሃሳቦችን እያፈለቁ የተለያዩ የፋሽን ዲዛይን ያላቸው እልባሳት እንዲሠሩ እንዳስቻላቸው አመልክታለች፡፡ የሽመናውና የልብስ ስፌቱን ሥራ በአንድ ላይ ይዘው ሲሠሩ እንደነበርም ጠቅሳ፣ እስካሁንም ራሳቸው የሸመኑትን ልብስ ራሳቸው ሰፍተው እየለበሱ እንደሆነ ትናገራለች፡፡

ቀደም ሲል በጎንደር በነበራቸው የመሸጫ ሱቅ በተለያዩ ዲዛይን የሚሠራቸው አልባሳት ለውጭ ሀገር ዜጎች ጎብኚዎች ይሸጡ እንደነበር ገልጻ፤ በአሁኑ ወቅት የሚያመርቱት መጠንና የገበያ ሁኔታው ስላልተመጣጠነላቸው ሥራቸውን ለማስፋፋት በማሰብ ሰፊ ፍላጎት ወደአለበት አዲስ አበባ መምጣታቸውን ትናገራለች፡፡

እሷ እንደምትለው፤ የእነርሱን የሽመና ሥራ ከሌላው ይለያል፤ ለእዚህም ምክንያቱ ለሽመና ሥራው የሚጠቀሙበት ማሽን ልዩ ነው፤ ይህ ማሽን ዲዛይን ተደርጎ የመጣው ከጀርመን ሀገር ቢሆንም፣ ለኢትዮጵያ ሽመና በሚመች መልኩ አባቷ ማሻሻያዎች አድርገውለታል፡፡ የማሽኑ ስፋቱ 2 ሜትር በ10 ሳንቲ ሜትር ስፋት ያለው ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ደረጃ የመጀመሪያው ነው፡፡ በዚህም በሦስት ሸማኔ የሚሠራውን የሽመና ሥራ በዚህ ማሽን በአንድ ሸማኔ መሥራት ያስችላል፡፡ ይህ ደግሞ ጊዜንና ጉልበትን ለመቆጠብ ይጠቅማል፡፡

“የሰው ፍላጎት የተለያየ ነው፣ በጣም የሚጮህ ልብስ የሚፈልግ እንዳለ ሁሉ ዝም ያለ ቀለም ያለው ልብስ የሚመርጥም አለ” የምትለው ሃያት፤ ድርጅታቸው የሁሉንም ሰው ፍላጎት ሊያሟሉ የሚችሉ አልባሳትን ዲዛይን አድርጎ እንደሚያቀርብ ጠቁማለች፡፡

ሃያት እንደምትለው፤ ምርቶቻቸውን በአብዛኛው በውጭ ሀገር ዜጎች ተፈላጊና ተወዳጅ ናቸው፡፡ ለየት ያሉ ጥራት ያላቸው ምርቶች መያዛቸውም ገበያው ጥሩ እንዲሆን አድርጎላቸዋል። ድርጅቱ ጀሞ አካባቢም የማምረቻ ቦታ አለው፤ ሥራዎችን በትዕዛዝ የሚሠራ ሲሆን፣ ምርቶቹን በባዛርና በኢግዚቢሽኖች ላይ ያቀርባቸዋል፡፡

የድርጅቱ ምርቶች ጥራት የተጠበቀ መሆኑን ገልጻ፣ ልምዳቸውን የሚያጋሩበት የልምድ ልውውጥ ለማድረግ ወደ ተለያዩ ሀገራት እንደሚሄዱም አስታውቃለች፡፡ ይህንን ሙያ ለመማር ለሚፈልጉ ብዙ ሰዎች ሥልጠና መስጠታችውን ጠቅሳ፤ ሥልጠናውን ከወሰዱት ውስጥ በአብዛኛው ሴቶች መሆናቸውን ትናገራለች፡፡ ከሥልጠናው በኋላ ብዙዎቹ በራሳቸው እያመረቱ መሸጥ ውስጥ መግባታቸውንም ጠቅሳለች። እነ ሃያት ሙያውን የበለጠ ለማሳደግና ባሕላዊ ልብሶች ይዘታቸውን ሳይለቁ እንዲዘምኑ ለማስቻል ከሥራቸው ጎን ለጎን ራሳቸውን በትምህርት እያበቁ ናቸው፡፡

እነ ሃያት የፋሽን አልባሳቱን ከሠሩ በኋላ ማህበራዊ የሚዲያ አማራጮችን (ፌስቡክ፣ ቴሌግራም፣ ኢንስታግራም፣ ቲክቶክ) በመጠቀም ያስተዋውቃሉ፡፡ ቀደም ሲል ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ ያቀርቡ የነበረው በትውውቅ ነበር፤ የገበያ መዳረሻዎቻቸውም ካናዳ፣ አሜሪካና ፈረንሳይ ነበሩ፡፡ አሁን ላይ ግን ለሀገር ውስጥ ገበያ ብቻ ያቀርባሉ፡፡

ምርቶቻቸው ከጥራቱ አንጻር ዋጋቸውም ቢሆን ተመጣጣኝ የሚባል እንደሆነ የምትናገረው ሃያት፣ አልባሳቱ ከሚፈጁት ጊዜና ከሚወጣባቸው ጉልበት እንዲሁም ከጥሬ እቃው አቅርቦት አንጻር ዋጋቸው እንደሚሰላም ገልጻለች፡፡ የእያንዳንዱ ምርት ዋጋም እንደወቅቱ ሁኔታ እንደሚለያይ አስታውቃለች፡፡

“የሀገራችንን ምርቶች እኛ ለብሰን ካልደመቅንባቸው፣ ካልኮራንባቸውና ካላስተዋወቅናቸው ማን ሃላፊነቱን ይወስድልናል” የምትለው ሃያት፤ ሙያው እንደ ሙያ፤ ባለሙያው እንደ ባለሙያ ተከብሮ እንዲኖር ሁሉም የበኩሉን ኃላፊነት መወጣት አለበት ስትል ታስገነዝባለች፡፡ ወጣቱም በዚህ ሙያ ተሰማርቶ የሀገሩን ምርት በማምረት ለራሱም ለሀገሩም መትረፍ ይችላል ስትል ምክረ ሃሳቧን ለግሳለች፡፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ዝም ይባላል እንዴ ?

መልካምሥራ አፈወርቅ

ዛሬም ቪዲዮው በግልጽ ተከፍቶ ያጠነጥናል፡፡ እየተላለፈ ያለው ስርጭት የሚሄደው በዩቲብ ነው። መቼም ይህ ማህበራዊ ሚዲየ ይሉት ከመጣ ወዲህ ቴክኖሎጂው በየሰዉ እጅ መመላለሱ ብርቅ አልሆነም ፡፡ እንዲህ መሆኑ ባልከፋ ነበር፡፡ ማንም እንደትኩስ ሻይ የሚደርሰውን መረጃ ሳይቀዘቅዝ ፉት ቢል አይጠላም፡፡

አንዳንዴ ግን ለማየትም ለማመንም የሚከበዱ መረጃዎች ይደርሳሉ፡፡ የሌላውን ዓለም ተወት አድርገን የኛውን ሀገር እውነት እንቃኝ ብንል እስከዛሬ ብዙ ሰምተን፣ አይተናል፡፡ የሚታመነው የትኛው ይሁን አይሁን ሳናውቀው የፈሰሰልንን ሁሉ ፊታችንን ሳናዞር አይተን ተደንቀናል፣ አዳንቀናል፡፡

አንዳንዴ ጆሮ መርጦ አይሰማ ፣ ሆኖብን ለውስጣችን የሚደርሰውን ሁሉ መቀበላችን ተጽዕኖው የጎላ ነው፡፡ እንዲያም ሆኖ ልብ የሚለው ያለ አይመስልም፡፡ አብዛኛው በተቀደደለት የአመኔታ ቦይ መፍሰሱን ይቀጥላል፡፡ ባየው እየተደነቀ ፣ በሰማው እየተገረመ መኖር ምርጫው ነው፡፡ ከሰሞኑ በዚሁ የማህበራዊ ሚዲያ የሚመላለሰውን መረጃ በርካታው ተመልካች ቃኝቶታል ፡፡

መረጃው በጽሁፍ ከመድረስ አልፎ ቪዲዮ ተሰርቶለት መታየቱ የመታመኑን ስፋት አልቆታል፡፡ ይህን ተከትሎም ጉዳዩ ለበርካቶች ፌዝና ጨዋታ ሰፊ በር መክፈቱ አልቀረም፡፡ የሃሳቡን ጫፍ የያዙ አንዳንዶች ከቁም ነገር በዘለለ ቀልዳቸው አሁን ድረስ ነገሩን እያቀለሉት ይገኛል፡፡

ለጊዜው ጥርስ ያስፈግግ የሚመስለው ታሪክ የብዙሃኑን ቤት ማንኳኳቱና ከስጋት መጣሉ አይቀሬ ሆኗል፡፡ ዛሬ በዚህ ጉዳይ የማይሳቀቅ የማይጠራጠር የለምና። ወዳጆቼ ስለምን እያወራሁ እንደሆነ ልንገራችሁ፡፡ አንኳር ርዕሰ ጉዳዬ ስለ አህያው ስጋ ሽያጭና ስለ ጥቂት ሉካንዳ ቤቶች ሚስጥር ነው፡፡

እውነት ለመናገር ይህን ቃል ደፍሬ ለመጻፍ ውስጤ ክፉኛ ተሸማቋል፡፡ እንዲህ አይነቱ ስሜት ከእኔ አልፎ ለበርካቶች እንደሚጋባም እገምታለሁ፡፡ ከጥቂት ጊዜያት ጀምሮ ርዕሰ ጉዳዩ በየቤታችን ገብቷል፡፡ ምንም እንኳን ጆሯችን ብዙ ወሬዎችን እየተላመደ ነው ቢባልም ለስጋ ወዳዱ ህብረተሰብ ይህ ዜና ከክፉም በላይ አስነዋሪና አሳፋሪው ይሆናል፡፡

አሁንም በዚሁ የማህበራዊ ሚዲያ ቅኝት ላይ ነኝ፡፡ ትኩረቴን በቅርቡ በተለቀቀው አንድ ገራሚ ቪዲዮ ላይ አድርጌያለሁ ፡፡ ከዩቲዩቡ ገጸ ታሪክ መረዳት እንደሚቻለው የስጋውን ሽያጭ ‹‹የአህያውን›› ጉዳይ ማለቴ ነው፡፡ ደርሰንበታል ባሉና ድርጊቱን ፈጽሚል በተባለ ግለሰብ መሀል አንድ ውዝግብ ተነስቷል፡፡

በሚተላለፈው የቪዲዮ ምስል አናት ውርንጭላ ቢጤ ቂብ ብላለች፡፡ ከፎቶው ቀጥሎ ‹‹ገንዘብ ካገኘን የጅብም ሥጋ ቢሆን እንሸጣለን›› የሚል ርዕስ ደምቆ ተጽፏል ፡፡ ከሰውየው አስደንጋጭ ንግግሮች መሀል የተመረጠ ቃል መሆኑ ነው። ቪዲዮውን በአግርሞት ማየቴን ቀጥያለሁ፡፡ አንድ የፕሮግራሙ መሪ ፊቱን በማስክ ሸፍኖ ታሪኩን ማስረዳት፣ ማብራራት ቀጠለ፡፡ እንደዋዛ እየሰማነው ያለው እውነት የአህያ ሥጋንና የሽያጩን ጉዳይ ሆኗል፡፡

ይህ ጆሮን ጭው የሚደርግ ታሪክ እየሆነ ነው የተባለው በሌላ ቦታ አይደለም፡፡ በእኛው ሀገር ሰማይ ሥር እንጂ፡፡ ከሁኔታው ስረዳ ግለሰቡ ባለሆቴልና የሥጋ አቅራቢ ነጋዴ ነው፡፡ ይህ መረጃ ያላቸው አነፍናፊዎች በስልክ ቀጠሮ ይዘው እርሱ ይገኝበታል ወደተባለ ስፍራ ያመራሉ፡፡ ይህ ሁሉ እንቅስቃሴ በድብቁ የቪዲዮ ካሜራ ተቀርፆ ለተመልካቾች እየተላለፈ ነው፡፡

ግለሰቡ ራሱን የሚያስተዋውቀው በተለየ መተማመን መሆኑ ይስተዋላል፡፡ ‹‹ክቡር ደንበኞቼ›› ለሚላቸው አጋሮቹ ሥጋውን በተሻለ ጥራት እንደሚያቀርብ ሲናገር ያለአንዳች ፍርሀትና ያለምንም ሀፍረት ነው፡፡ የሁለቱ አይታመኔ የሚመስል ውይይት ቀጥሏል፡፡ የገዢውና የአህያ ሥጋ ሻጩ ንግግር በመተማመንና በመስማማት እየዘለቀ ነው፡፡ ሰውየው አፉን ሞልቶ የአህያ ሥጋ ለተጠቃሚው እንደሚያቀርብና ሥራውም የተፈቀደ ስለመሆኑ ማብራራት ይዟል፡፡ አሁንም ድብቅ ካሜራው ሥራውን አላቆመም፡፡ እያንዳንዷን እንቅስቃሴ ከነንግግሩ እየቀረጸ ነው፡፡

ሰውየው ስለዋጋው፣ ስለጥራቱ፣ መናገሩን አላቆመም። ይባስ ብሎ ሰርቶ ስለመለወጥ በኩራት መዘርዘር ጀምሯል። ዘመናዊ ቤቱንና የመኪና ቁልፉን እያሳየም ኑሮው የተቀየረው በዚሁ ሥራ መሆኑን ከከመግለጽ አላፈረም፡፡

በሥራ አጋሮቹ መሀል ውይይቱ ቀጥሏል፡፡ ሰውየው ጥያቄዎችን እየመለሰ ስለ ግሉ የአህያ ቄራ ማብራራቱን ይዟል፡፡ ስለሚታከሙት አህዮችና ድንገቴ እርድ ስለሚፈጸምባቸው በግልጽ ሲናገር ያለማጋነን አንድ ለሀገር የሚሰራ ታዋቂ ባለሀብት ይመስላል፡፡

ሰውየው ስለአህዮቹ ጤንነትና የቄራው ደረጃ በኩራት እያብራራ ራሱን መካብ ቀጥሏል፡፡ የግል ተሞክሮውንና ሊኖር የሚችልን የሕግ ተጠያቂነት ጭምር በስፋት ይዘረዝራል፡፡ በዚህ ጽሁፍ ለመግለጽ የሚከብዱ ንግግሮች ፣ ለማሰብ የሚያዳግቱ ቃላቶች በሁለቱ ሰዎች መሀል እየተካሄደ ነው። ‹‹ጉድ›› እስኪባል ‹‹አጀብ›› የሚያሰኝ ድብቅ ጉዳይ ገሀድ መሆኑን አስተዋልን፡፡

አሁንም በዚሁ የማህበራዊ ሚዲያ ሌሎች የቪዲዮ ምስሎች ወደ ዓይናችን እየደረሱ ነው፡፡ ሁሉም ተመሳሳይ ታሪክና አንድ አይነት ፍላጎት አላቸው፡፡ የሚገርመው ሚስጥሩን ደረስንበት በሚሉትና ጉዳችን ገሀድ ወጣ ባሉት መካከል ያለው ፍፃሜ በጠብና ድብድብ መጠናቀቁ ነው፡፡ ባለሆቴሉ ፣ ባለ አህያ ቄራዎቹና ሌሎች ባለታሪኮች ጭምር ሚስጥራችን ታወቀ ባሉ ጊዜ ዱላ ይመዛሉ፣ ለጠብ ይጋበዛሉ፡፡

ሰሞኑን በተለያዩ ገጾች የምናያቸው ምስሎች በሙሉ ተረተትና ፊልም አስኪመስሉን ለማመን ተቸግረንባቸዋል፡፡ አብዛኞቻችን ስጋ ቤት በሄድን ጊዜ ልማዳችን እንደቀድሞው አልሆነም፡፡ ‹‹ከሸንጡ፣ ከአጥንቱ›› ማለትን ትተተናል። የስጋውን መቅላት፣ መስባት፣ መብዛትና ማነስ እያጤን የአመጣጡን ሚስጥርና ምንነቱን መመራመር ልምዳችን ሆኗል፡፡ ይህ ጥርጣሬና ሃሳብ ደጋግሞ ቢከተለን አይፈረድም፡፡ የእስከዛሬው ባህልና እምነታችን ከአህያ ሥጋ አዛምዶን አያውቅምና ፡፡ እኛ ማለት ነውርን በነውርነቱ የምናርቅ በጎውን በጥሩነት አክብረን የምንይዝ ነን፡፡

በዚሁ የማህበራዊ ሚዲያ ላይ እየተለጠፉ ያሉ አንዳንድ ጉዳዮች ከማስደንገጥ አልፈው ሳይወዱ በግድ ያስፈግጋሉ፡፡ አንዳንዱ ‹‹አፋልጉን›› የሚል ማስታወቂያ አድምቆ ይጽፍና ‹‹አህያችን ቀን ሲሰራ ውሎ ከሰአት ሳር ሲግጥ እንደወጣ አልተመለሰም›› የሚል ተማጽኖ ይጨምርበታል፡፡ ይህ በሰውኛ አሽሙር የተላለፈ መልዕክት ትርጉም የሚያሻው አይደለም፡፡

አንዳንዴ ከየት መጡ የማይባሉ አስደንጋጭ ወሬዎች በሀገር ምድሩ መናፈሳቸው ያለ ነው፡፡ እነዚህ እጅን በአፍ የሚያስጭኑ ድንገቴ ወሬዎች የመነሻ ምንጫቸው አይታወቅም ፡፡ አጥብቆ የሚጠይቅ ቢኖር ደግሞ ‹‹አሉ›› ከማለት ውጭ አንዳች ማረጋገጫ አያገኝም፡፡

እንዲህ አይነቶቹ የወሬ ንፋሶች እንደዋዛ ተጀምረው፣ ተጨምረው ተጨማምረው ይቆያሉ፡፡ እንደአመጣጣቸው ብን ብለው ለመጥፋትና ለመረሳት ደግሞ አፍታ አይቆዩም። የሰሞኑ ጆሮ አግል ወሬ ግን ከተለመዱት ሽውታዎች ሁሉ የተለየ ነው፡፡ የመነሻ ምንጩ ከመታወቅ አልፎ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

ምስልና ድምጹን የሚያስተላልፈው የዩቲብ ገጽ ማንነቱን አልደበቀም፡፡ ከዚሁ ተያይዞ መግለጫ ቢጤ ለመስጠት የደፈሩ አንዳንዶችም በገሀድ ወጥተው እየተናገሩ ነው፡፡ አሁን ላይ ብዙሃኑ በግልጽ እንደሚያወራው የአህያ ሥጋ ለውጭ ገበያ እንዲቀርብ ተፈቅዷል እየተባለ ነው፡፡

ይህ የአሉ ወሬ ግን ከሚመለከታቸው አካላት አንደበት አልተሰማም፡፡ ጉዳዩ እንዲህ በአደባባይ የባቁላ ወፍጮ ሆኖ እያለ ከሕግ አካላትና ከሃይማኖት አባቶች፣ ከባለሙያዎችና ከጤና ጥበቃ አካላት አንዲት ቃል ትንፍሽ አልተባለም፡፡ ዝምታውን እንደመስማማት የቆጠሩት አንዳንዶች ጭራሽ ብዙሃን የሚጠየፉትን የአህያ ሥጋ በየፌስቡክና ዩቲዩብ ገጻቸው እየለጠፉ ማሳቀቁን ቀጥለውበታል፡፡

እኔ ‹‹ውሸት ሲቆይ እውነት ይሆናል›› ይሉት አባባል ዕውን እንዳይሆን ስጋቱ አለኝ፡፡ ይህ ገደብ የለሽ ወሬ በወቅቱ ያለመቀጨቱና ከሚመለከተው አካላት አንዳች ያለመባሉ ጥያቄውን እያባሰው ነው፡፡ ወዳጆቼ! እናንተስ ምን ትላላችሁ? ፣ መሸፋፈን መደባበቁ እስከመቼ መቀጠል አለበት ? ኧረ ! ጎበዝ ዝም ይባላል እንዴ ?

# ዓለም አቀፍ

## የእሥራኤልና የሐማስ የእስረኞች ልውውጥ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



እሥራኤል እና ሐማስ እስረኞችንና ታጋቾችን ለመለዋወጥ ተስማምተዋል። ለአራት ቀናት ውጊያ ለማቆም ስምምነት የደረሱት እሥራኤልና ሐማስ በርካቶች ሲጠብቁት የነበረውን ርምጃ ወስደዋል።

እሥራኤል ሊፈቱ የሚችሉ 300 ፍልስጤማውያንን ስም ዝርዝር አሳውቃለች። አብዛኞቹ ዕድሜያቸው 17 ወይም 18 መሆናቸውን ቢቢሲ በዘገባው አስፍሯል። በአጠቃላይ ግን ዕድሜያቸው ከ14 እስከ 59 የሚደርሱ 274 ያህሉ ደግሞ ወንዶች መሆናቸው ተገልጿል።

ስም ዝርዝሩ ይፋ የሆነው በእሥራኤል ውስጥ ባለው ሕጋዊ አሠራር ምክንያት ነው። ማንኛውም እስረኛ ከመፈታቱ በፊት፣ የእሥራኤል ዜጎች ስሞቹን አይተው ለእሥራኤል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማለት 24 ሰዓት ሊሰጣቸው ይገባል።

በመጀመሪያው ምዕራፍ ሐማስ በየቀኑ 12 ሰዎችን በመልቀቅ በአጠቃላይ 50 ሴቶችና ሕፃናት ታጋቾችን ይለቃል። ከዚያም እሥራኤል 150 ፍልስጤማውያንን ትፈታለች።

በሁለተኛው ምዕራፍ 10 ታጋቾች በተፈቱ ቁጥር የተኩስ አቁሙ በአንድ ቀን ይራዘማል። እሥራኤል እስከ 50 የሚደርሱ ታጋቾች ከጋዛ ከተለቀቁ እስከ 150 ፍልስጤማውያን እስረኞችን ትፈታለች። በኳታር ሸምጋይነት የተደረሰውን ይህን ስምምነት የዓለም መሪዎች በደስታ ተቀብለውታል።

በአውሮፓ ኅብረት፣ በዩናይትድ ኪንግደም እና በአሜሪካ በአሸባሪነት የተፈረጀው ሐማስና በእሥራኤል መካከል በተከሰተው ጦርነት በርካቶች ለሞትና ለመፈናቀል ተዳርገዋል።

እሥራኤል ሊፈቱ የሚችሉትን 300 ፍልስጤማውያን እስረኞች ፈጽመውታል ያለችውን ወንጀሎችና ጥፋቶች ዘርዝራለች።

በዚህም የግድያ ሙከራ፣ ቦምብ መወርወር፣ ፈንጂ ወይም ተቀጣጣይ ነገር መሥራት፣ ድንጋይ መወርወር፣ ከጠላት ቡድን ጋር መገናኘት፣ ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ እና የዜጎችን ንብረት በማቃጠል የታሰሩ መሆኑን አስታውቃለች።

ከቀድሞዎቹ የእስረኞች ልውውጦች በተለየ በዝርዝሩ ውስጥ ከተካተቱት ሰዎች መካከል አንዳቸውም እሥራኤላውያንን በመግደል ወንጀል አልተከሰሱም።

እ.አ.አ. ጥቅምት 2011 እሥራኤላዊውን ወታደር ጊላድ ሻሊት በሐማስ ምርኮ ውስጥ ከቆየ ከአምስት ዓመታት በኋላ ነፃ የወጣበት መንገድ እጅግ በርካታ እስረኞችን በመልቀቅ የተፈጸመ ነው።

በእሥራኤል እና በታጣቂ ቡድኑ መካከል በተደረሰው ስምምነት መሠረት አንድ ወታደር ለ1027 ፍልስጤማውያን እስረኞችን ተለዋውጠዋል።

ከተፈቱት እስረኞች መካከል የተወሰኑት በግድያ ወንጀል የተከሰሱ ሲሆን፣ በጋዛ ሰርጥ የሐማስ መሪ የሆነውና በመስከረም 26ቱ ጥቃት እሥራኤል ተጠያቂ የምታደርገው ያህያ ሲንዋር ይገኝበታል።

እ.አ.አ. በጥር 2004 በተመሳሳይ ከፍተኛ የሚባል እስረኛ ልውውጥ ተከናውኗል። መቀመጫውን በሊባኖስ ባደረገው እና በኢራን ከሚደገፈው ታጣቂ ሄዝቦላህ ጋር በተደረገ ስምምነት እሥራኤል 436 ፍልስጤማውያን እና ሌሎች የዐረብ እስረኞችን ልውውጥ አካሂዳለች።

ይህም በድንበር ኬላ ላይ ታፍነው የተወሰዱ ኤልሃናን ታኔንባም የተባለውን እሥራኤላዊ ነጋዴ እና ሦስት የሞቱ የእሥራኤል ወታደሮችን አስከሬን እንዲመለሱ በር ከፍቷል።

እሥራኤል አንድ ሰው የቀረበበትን ክስ ሳይሰማ ወይም ችሎት ሳይቀርብ ሊታሰር የሚችልበት 'አስተዳደራዊ እስር' የሚባል አሠራር አላት።

የእሥራኤል የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅት ሃሞከድ እንዳለው እሥራኤል ውስጥ 1 ሺህ 70 ፍልስጤማውያን የአስተዳደር እስረኞች ነበሩ። ይህ ቁጥር በሐማስ ጥቃት ወቅት አንድ ሺህ 319 ነበር።

የሃሞከድ ዋና ዳይሬክተር ጄሲካ ሞንቴል ስምምነቱን በደስታ ተቀብለዋል።

«ሰዎችን አግቶ መያዝ በራሱ ሕገወጥ ነው፣ የጦር ወንጀል ነው። ሐማስ ሁሉንም ታጋቾች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መልቀቅ አለበት» ሲሉ በመግለጫቸው ተናግረዋል። «ይህን ዓላማ ለማሳካት እሥራኤል እስረኞችን መፍታት አለባት» ብለዋል።

በእሥራኤል እና ሐማስ ስምምነት መሠረት በአስተዳደራዊ እስር ላይ የሚገኙት ፍልስጤማውያን ሴቶች እና ሕፃናት እንደሚፈቱም ገልጸዋል።

እነዚህ ሰዎችም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መፈታት ነበረባቸው። ስለዚህ የእሥራኤል ታጋቾችን እና የፍልስጤም አስተዳደር እስረኞችን ለመፍታት የተደረገው ስምምነት ደስ የሚያሰኝ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እና ሴቭ ዘ ችልድረን የተባለው መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት በየዓመቱ ከ500 እስከ 700 የሚደርሱ ፍልስጤማውያን ሕፃናት ለእስር እንደሚዳረጉ ገልጸዋል።


ፈጣን ሎጂስቲክስ
FETAN LOGISTICS

### ፈጣን ሎጅስቲክስና እና ትሬዲንግ አክሲዮን ማህበር

### ለባለአክሲዮኖች 1ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ እና 1 አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የተደረገ ጥሪ ማስታወቂያ

በንግድ ሕጉ 1243/2013 በፀደቀው መሠረት በንግድ መዝገብ ቁጥር NL/AA/3/0023525/2015 የተመዘበውና ዋናው መ/ቤት ን/ስ/ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 02 የሚገኘው ፈጣን ሎጅስቲክስ እና ትሬዲንግ አክሲዮን ማህበር 1ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ እና 1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤውን ታህሳስ 13 ቀን 2016 ዓ.ም ቅዳሜ ከጠዋቱ 2፡30 ሰዓት ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው ኢትዮጵያ ሆቴል አዳራሽ ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤውን የሚያካሂድ በመሆኑ የአክሲዮኑ አባላት የሆኑ በአካል ወይም በሕጋዊ ወኪሎቻቸው አማካኝነት ከላይ በተጠቀሰው ቀን እና ሰዓት በጉባኤው ላይ እንድትሳተፉ የአክሲዮን ማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ በአክብሮት ጥሪውን ያቀርባል፡፡

**የስብሰባው አጀንዳዎች፣**

**የ1ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳ፣**

1. የጉባኤውን አጀንዳዎች ማፅደቅ፣
2. የ2015 ዓ.ም የበጀት ዓመቱን ማጠቃለያ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ማድመጥና ማፅደቅ፣
3. የ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት የውጪ ኦዲተር ሪፖርት፣ የሀብትና ዕዳ ሚዛን እና ትርፍና ኪሳራ መግለጫ ማድመጥ መወያየትና ማፅደቅ፣
4. ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ስለተጠናቀቀው ሂሣብ ዓመት የተጣራ ትርፍ አደላደልና አከፋፈል ላይ በቀረበው ውሳኔ ሀሳብ መሠረት መወያየትና ማፅደቅ፣
5. የጠቅላላ ጉባኤውን ቃለ ጉባኤ ማፅደቅ ናቸው፡፡

**የ1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች፣**

1. በማህበሩ መመሥረቻ አንቀጾች ማሻሻያ ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ ፣
2. ቀሪ የአክሲዮን ክፍያ መሰብሰብን አስመልክቶ ተወያይቶ መወሠን ናቸው፡፡

**ማሳሰቢያ፣**

1. በዕለቱ የምትሳተፉ ተወካዮች ሕጋዊና አግባብ ካለው የፌደራል ወይም የክልል የሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የተሰጠ በስብሰባ ለመሳተፍ ድምፅ ለመስጠት የሚያስችል የውክልና ሠነድ ዋናውንና ፎቶ ኮፒውን ይዘው በመቅረብ መሳተፍ የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እናስታውቃለን፡፡
2. ባለአክሲዮኖችም ሆናችሁ ሕጋዊ ወኪሎች ወደ ስብሰባው ቦታ ስትመጡ ማንነታችሁን የሚያረጋግጥ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ ይዛችሁ እንድትቀርቡ እንዲሁም ተወካዮች የወካያችሁን ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ በተጨማሪ ይዛችሁ እንድትቀርቡ እናሳስባለን፡፡
3. በውጪ ኦዲተር የተዘጋጀውን የአ/ማህበሩን የሀብትና ዕዳ ሚዛን እና ትርፍና ኪሣራ መግለጫ ሪፖርት ኮፒ ዋናው መ/ቤት በአካል በመምጣት መውሰድ የምትችሉ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**ለበለጠ መረጃ ፡- ስልክ ቁጥር** 0113-69 85 31/0944-12 33 55/0113- 69 85 34 ይደውሉ

**የፈጣን ሎጅስቲክስ እና ትሬዲንግ አክሲዮን ማህበር**
**የዳይሬክተሮች ቦርድ**



### INVITATION FOR BID

**IFB Reference No. ECWCT/NCB/PG/72/2016**

The Ethiopian Construction Works Corporation (ECWC) here by invites registered eligible bidders for Supply & install wireless security system on a frameless glass and x-ray baggage scanner for Ministry of Revenue head quarter renovation and compound Works under National Competitive Bidding -NCB.

1. Interested Potential Bidders are required to present renewed relevant Trade License for the fiscal year, VAT Registration Certificate, Tax Clearance Certificate, Online Supplier list Registration certificate.
2. Bidding document should be prepared in English language.
3. Interested Potential Bidders May obtain a complete set of bidding document from the Procurement department against payment of none refundable fee of Birr 400.00 upon presentation of Trade License renewed for the fiscal year; VAT Registration Certificate, Tax Clearance certificate and Online Supplier list Registration Certificate.
4. This invitation of bid is open to all interested potential bidders regardless of their nationality bid evaluation and award shall be determined in accordance with the provision indicated in bidding document.
5. The deadline for bid Submission shall be on December 15,2023 at 03:00 PM.
6. Bid must be accompanied with a Bid Security of an amount of 200,000 (two hundred thousand)in the form of certified cheque (CPO) or Bank guarantee.
7. Bids must be delivered or deposited in the Tender Box situated at the office of the Procurement Department, before the closing date and time.
8. Bids will be opened on December 15,2023 at 03:30 PM, in Ethiopian Construction Works Corporation Procurement Department office, in the presence of bidders and/or their representatives who choose to attend.
9. The Ethiopian Construction Works Corporation reserves its rights to reject any or all bids.
10. Bidders may get further information at the following address:

**Ethiopian Construction Works Corporation**

**Procurement Team 3**

**P.O. Box 21952/1000, Addis Ababa, Ethiopia**

**Gurd Sholla, in front of Andinet International School**

**Tel. No. +251118722958/0118962991/0118678089/+251118723086**

**Telegram channel ##ECWC**

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ethiopian Press Agency

አዲስ ዘመን ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ስትግራይ ክልል ስፖርት መልሶ ግንባታ ጥረቶች ሊጠናከሩ ይገባል

ብርሃን ፈይሳ

የትግራይ ክልል በአትሌቲክስ፣ እግር ኳስ፣ ብስክሌት፣ ባድሜንተንና ሌሎችም ስፖርቶች ውጤታማ ስፖርተኞችን በማፍራት ይታወቃል፡፡ ክልሉ ባለፉት ዓመታት በነበረው ጦርነት ምክንያት ከስፖርት ርቆ የቆየ ሲሆን፤ እንደክልል ከፍተኛ ውድመት ካስተናገዱ ዘርፎች መካከል አንዱ ስፖርት ነው፡፡

በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ዘርፈብዙ ጉዳት የደረሰበትን የትግራይ ክልል ስፖርት መልሶ ለመገንባት የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ ሲሆን፣ እነዚህ ጥረቶች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ተጠቁሟል፡፡ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን 27ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ትናንት እና ከትናንት በስቲያ በትግራይ ክልል መቀሌ ከተማ አከናውኗል። በጉባኤው ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት አቶ ጌታቸው ረዳ፣ ለክልሉ ስፖርት በሚደረገው የመልሶ ግንባታ የስፖርቱ ዘርፍ የተጠናከረ እገዛ ማድረግ እንደሚገባው ገልፀዋል፡፡

በክልሉ በነበረው ጦርነት ምክንያት በከፍተኛ ሁኔታ ጉዳት ከደረሰባቸው ዘርፎች መካከል አንዱ ስፖርት መሆኑን የጠቆሙት ፕሬዚዳንቱ፣ በክልሉ በሚደረገው መልሶ ግንባታ ላይ የስፖርቱ ዘርፍ የራሱን ምልከታ ሊያደርግ ይገባል ብለዋል፡፡ በመሆኑም ጉባኤው እንዲሁም ጉባኤተኛው በሚኖረው ቆይታ ክልሉ በሚያደርገው የመልሶ ግንባታ የሚኖረውን ተሳትፎ አጠናክሮ መቀጠል እንደሚኖርበት አስገንዝበዋል፡፡


በጉባኤው የተለያዩ የአትሌቲክሱ ችግሮች ለውይይት ቀርበዋል፣

አቶ ጌታቸው አክለውም፣ በጦርነቱ ወቅት በነበረው ሁኔታ የትግራይ አትሌቶች ሥነልቦና እንዳይጎዳ እንዲሁም ከጦርነቱም በኋላ አትሌቶችን ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲገናኙ በማድረግ ረገድ የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ ላደረገችው አስተዋጽኦ አድናቆታቸውን ገልጸዋል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን ስም ያስጠሩ የትግራይ ተወላጅ አትሌቶች የመኖራቸውን ያህል በርካቶች ደግሞ ወደፊት ስመጥር አትሌት ሊሆኑ የሚችሉ በመኖራቸው ፌዴሬሽኑ እገዛ ሊያደርግላቸው ይገባል ሲሉም ተናግረዋል፡፡ የአትሌቲክስ መንደርን ለማነጽ ቀደም ብሎ የተጀመረውንም እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት ጥረት እንደሚደረግም ያላቸውን ተስፋ ገልፀዋል፡፡ ስፖርት ጤናማ ማኅበረሰብን ለማፍራት የሚኖረውን ሚና የጠቀሱት ፕሬዚዳንቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እንደሚሠሩም ተናግረዋል፡፡

በጉባኤው የመክፈቻ ንግግር ያደረገችው የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ፤ በጦርነቱ ምክንያት ከስፖርቱ ርቆ በቆየው የትግራይ ክልል በድጋሚ መገናኘት መቻል አስደሳች መሆኑን ገልፃለች፡፡

በጉባኤው የ2015ዓም የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ቀርቦ ውይይት የተደረገበት ሲሆን፤ የተለያዩ ሃሳቦች በጉባኤተኛው በኩል ተሰንዝረዋል፡፡ በተለይም የስፖርት ማዘውተሪያ ጉዳይ፣ የብሔራዊ ቡድን ምልመላ በተለይም የአትሌቶችና የአሰልጣኞች አመራረጥ፣ ዓለም አቀፍ ውድድሮች ከተካሄዱ በኋላ የነበሩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመገምገም ለቀጣይ እርማት አለመውሰድ፣ በፌዴሬሽኑ ሥራ አስፈጻሚዎች መካከል አለመግባባት መኖሩ፣ የቴክኒክ ባለሙያዎችና የሥራ አስፈጻሚ ሥራ መደበላለቅ እንዲሁም ጣልቃ ገብነት መኖሩ ተጠቁሟል፡፡

በዓመቱ ኢትዮጵያ በተካፈለችባቸው ዓለም አቀፍ ውድድሮች የተመዘገቡት ውጤቶች አበረታች ከነበሩ የዓመቱ አፈጻጸም መካከል ዋናው ነው፡፡ በፋይናንስ በኩልም የተለያዩ ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን፤ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር የተደረገው የስፖንሰር ስምምነትም ለዚህ ማሳያ መሆኑንም በፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት ተገልጿል፡፡

ክልሎች ከፌዴሬሽኑ የሚያገኙት ድጋፍን በተመለከተ ችግሮች መኖራቸው እንዲሁም የስፖርት አበረታች ቅመሞችና የዕድሜ ተገቢነት ችግር አሁንም የስፖርቱ ዋነኛ ስጋት ሆኖ መቀጠሉንና ጠንካራ ውሳኔ የሚያስፈልገው መሆኑም ተመላክቷል፡፡ በአዲስ መልክ የተዋቀረው የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ያቀረበውን የአባልነት ጥያቄም በጉባኤው ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

በጉባኤው ላይም የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት፣ የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት አቶ ጌታቸው ረዳ፣ የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ተወካይ፣ የፌዴሬሽኑ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት እንዲሁም የጠቅላላ ጉባኤው አባላት ተገኝተዋል፡፡

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን 27ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤውን እንዲሁም 19ኛውን የማራቶን ሪሌ ውድድር በትግራይ ክልል መቀሌ ከተማ የነበረውን የሁለት ቀናት ቆይታ ትናንት አጠናቋል፡፡

ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር
ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የበይነ መረብ መሠረተ ልማት ጥቃት እና ደኅንነት

ስሜነህ ደስታ

በይነ መረብ (ኢንተርኔት) ማለት ዓለም አቀፍ የኮምፒዩተር ግንኙነት ሲሆን በየትኛውም የዓለማችን ክፍል ያሉ ሕዝቦች መረጃን በቀላሉ ለማግኘት፣ መረጃን ለመለዋወጥ እንዲሁም የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የሚረዳ ቴክኖሎጂ ነው፡፡ ይህንን አገልግሎት ከኮምፒዩተር እና ከስልክ መስመር በማገናኘት ከአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የተገኘውን አካውንት በመጠቀም ማግኘት ይቻላል፡፡ይህን ቴክኖሎጂ በርካታ ዓይነት አገልግሎቶችን ለማግኘትና በአጠቃላይ ሕይወታችንን ለማቅለል የምንጠቀምበትን ያህል እኩይ ዓላማ ባላቸው አካላት በአሉታዊና በአፍራሽ መንገድ ጥቅም ላይ ሊውልም ይችላል፡፡ በዚህም ያልተገቡ ጥቅሞችን ለማግኘት ሲባል የተለያዩ ጥቃቶችና ወንጀሎች ሲፈጸሙበት ይስተዋላል፡፡በይነ መረብን በመጠቀም ጥቃት ማድረስ የበይነ መረብ ጥቃት ወይም ወንጀል ይባላል።

በሌላ በኩል ደግሞ በይነ መረብን በመጠቀም ጥቃት እንዳይደርስ ለመከላከል የሚደረጉ ሥራዎች እና ፖሊሲዎች የበይነ መረብ ደኅንነት በመባል ይታወቃል። ይህም በኮምፒዩተር ሥርዓት ውስጥ የተካተቱትን አስፈላጊ መረጃዎችን (ሶፍትዌር፣ የኮምፒዩተር ኔትወርኮች፣ ፋይሎች፣ ወዘተ.)፣ ሥርዓቶችን እና ተጠቃሚዎችን ከሚጎዱ ጥቃቶች የመከላከል ተግባር ነው፡፡የበይነ መረብ ዓለም፣ ከምናውቀው እውናዊ ዓለም የተለየ ነው፡፡በይነ መረብ ዓለም ውስጥ ድንበር (physical boundary) የለውም። ለምሳሌ ኢትዮጵያ በሳይበር ዓለም ከአሜሪካ፣ ከቻይና ወይም ከሌላ ማንኛውም ሀገር ጋር ድንበርተኛ ነች። በመሆኑም የሳይበር ጥቃት ከማንኛውም ሀገር ሊነሳ ይችላል ማለት ነው። ጥቃቱም በግለሰብ እንዲሁም በድርጅት ላይ ሊፈጸም ይችላል፡፡በተለይ ጥቃቱ በሀገር ደረጃ ሲፈጸም ከፍተኛ መዋቅራዊ ጉዳትን ያስከትላል፡፡

የበይነ መረብ ጥቃቶች በተለያዩ የማጥቂያ መንገዶች ይፈጸማሉ፡፡ጥቃት አድራሾች የግለሰቦችን ኮምፒዩተር፣ ስልክ፣ የባንክ ካርድ እና ማንኛውንም በይነ መረብ ላይ ያኖሩትን መረጃ በርብረው ሊያጠፉ ይችላሉ፤ የሲስተሞችን አቅም ባልተፈለገ ሁኔታ በማጨናነቅ ሕጋዊ ተጠቃሚው አገልግሎት እንዳያገኝ ያደርጋሉ፤ ሆን ተብሎ እና ሳይጠበቅ መልክን በመቀየር ጣልቃ በመግባት መደበኛ የኮምፒዩተር ተግባርን ያውካሉ። የተጠቂውን ድረ- ገጽ በሀሰተኛ ሰነዶች ይቀይራሉ፤ ብዛት ያለው እና የአጥፊነት ተልዕኮ ያላቸው ኢ- ሜሎችን በመላክ ጥቃት ይፈጽማሉ፤ የተለያዩ የማታለያ እና የማዘናጊያ ዘዴዎችን በመጠቀም አጭበርባሪዎች ከተጠቃሚዎች ምስጢራዊ የሆኑ መረጃዎችን ይመዘብራሉ፡፡

ማንኛውም ሰው ሆነ የትኛውም ድርጅት ለጥቃት ተጋላጭ ነው። ይሁንና ዋናው የጥቃቱ ዒላማዎች ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው መረጃ ባሏቸው ትልልቅ ተቋማት ላይ ነው። ከነዚህም መካከል የገንዘብ ተቋማት በይበልጥ ለጥቃቶቹ ተጋላጭ ሲሆኑ፣ የደኅንነት ተቋማትና መከላከያ ተቋማት እንዲሁም ትልልቅ መሠረተ ልማት ለምሳሌ እንደ ቴሌኮም፣ መብራት፣ ትራንስፖርት ዓይነቶቹ በከፍተኛ ሁኔታ ዒላማ ይደረጋሉ፡፡እንደማሳያ ኢ.ኤ.አ. በ2019 የወጡ ዓለም አቀፍ ሪፖርቶች የገንዘብ ጥቅምን ለማግኘት የሚደረጉ የበይነ መረብ ጥቃቶች ዓለም ላይ የሚገኙ ድርጅቶችን ከ11 ነጥብ 5 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ አስከፍሏቸዋል። ይህ ማለት በይነ መረባቸውን በመጥለፍ እና የመረጃ ቋታቸውን በመያዝ አስገድደው ያስከፈሉት የገንዘብ መጠን ነው።

አሁን በዓለም ላይ የሚደርሱ የበይነ መረብ ጥቃቶች ዝንባሌ (trend) ምን ይመስላል? ብለን ስናይ ዕለት በዕለት እየጨመረ ይገኛል ፡፡ኢ.ኤ.አ. በ2022 ወደ ሰባት ትሪሊዮን የሚሆን፣ በ2023 ወደ ስምንት ትሪሊዮን ኪሳራ የተከሰተ ሲሆን በ2025 ደግሞ ወደ 10 ትሪሊዮን ኪሳራ ይከሰታል ተብሎ ተገምቷል፡፡ ይህም ሀገራት ከወዲሁ ጥንቃቄ እና ቅድመ ዝግጅት ማድረግ እንደሚያስፈልጋቸው ያመላክታል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የበይነ መረብ ደኅንነት ክፍተቶችም ከ70 በመቶ በላይ ሊያድጉ እንደሚችሉ ተጠቁሟል፡፡

ሌላው የበይነ መረብ ጦርነት የኮምፒዩተር ቴክኖሎጂ መረብን ተጠቅሞ ትልልቅ የመንግሥት ተቋማት ላይ ጥቃት በማድረስ ፖለቲካዊ ፍላጎትን ለማሳካት በሀገሮች ደረጃ የሚደረግ ጦርነት ነው። የበይነ መረብ ጦርነት ዓላማው የገንዘብ ተቋማትን እንዳይሠሩ ማድረግ፣ ትልልቅ የመሠረተ ልማቶችን እንቅስቃሴ ማስተጓጎል ወይም ጠልፎ በማስገደድ ለመደራደሪያነት በማቅረብ ሀገራዊ ዓላማን ማሳካት ወይም ጉዳት ማድረስ ሊሆን ይችላል።

በዓለም ላይ እንደዚህ ዓይነት ጥቃት የሚሰነዘረው ብዙ ጥቅም ወዳለበት አካባቢ በመሆኑ በአደጉት ሀገራት በብዛት ይስተዋላል። ለምሳሌ አሜሪካ፣ ሰሜን ኮሪያ፣ ቬትናም፣ ቻይና እና ሩሲያ የሰነዘሯቸው ብዙ ጥቃቶች እንዳሉ ይነገራል፡፡ቻይናን ብቻ ብንወስድ በአሜሪካ ትላልቅ ተቋማት ላይ በርካታ ጥቃቶች እንደምታደርስ መረጃዎች አሉ። ሩሲያ በአሜሪካን ምርጫ ላይ እጇ መኖሩን የሚጠቁሙ መረጃዎች ይፋ መደረጋቸው ይታወሳል።

የበይነ መረብ ወንጀሎችን በመከላከል ሂደት በአጠቃላይ ሊነሱ የሚችሉ ዋና ዋና ተግዳሮቶች በተለይ በብዙ አዳጊ ሀገራት የበይነ መረብ ወንጀሎችን ለመከላከል የቴክኒካል እውቀት እጥረት፣ የሠለጠነ የሰው ኃይል በቂ ቁጥር አለመኖር እና ለጥቃት ብዙ ነገሮች ክፍት መሆናቸው ናቸው።

ሌላው የበይነ መረብ ደኅንነትን ለማስጠበቅ የሚረዱ ፖሊሲዎች፣ የሕግ ማዕቀፎችና የአፈፃፀም መመሪያዎች አለመኖራቸው ነው። እንዲሁም ስለበይነ መረብ ጥቃቶች እና ደኅንነት የማኅበረሰቡ ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆን ሀገራትን ለጥቃት ተጋላጭ አድርጓቸዋል። ቴክኖሎጂው ጥቃት ለማድረስ ቀላል መሆኑ ራሱን የቻለ ተግዳሮት ተደርጎም ይቆጠራል።

በኢትዮጵያ በበይነ መረብ ጥቃት እና ደኅንነት ዙሪያ ጥንቃቄ ሊደረግባቸው የሚችሉ ጉዳዮች በቅድሚያ መንግሥት ትልቁን አመራር ወስዶ ወቅቱን ያገናዘበ የበይነ መረብ ደኅንነት ፖሊሲ ማዘጋጀት አለበት፤ እንዴት ወደ ተግባር መግባት እንደሚቻልም አቅጣጫ ማስቀመጥ አለበት። እንደ ሀገር የሳይበር ደኅንነትን ለማስጠበቅ ምን አቅም አለን፣ ምን ዓይነት ስትራቴጂ መንደፍ አለብን፣ የጠላቶቻችን ደረጃስ ምን ያህል ነው የሚለውን መነሻ ያደረገ የበይነ መረብ ደኅንነት ስትራቴጂ መዘጋጀት አለበት።

በመቀጠል ከቴክኖሎጂው አንጻር አስተማማኝ የሆነ የበይነ መረብ መሠረተ ልማትን የያዘ፣ ጥሩ የደኅንነት መፍትሔዎች ያሉት አስተማማኝ በይነ መረብ ማዘጋጀት ይገባል። ከዚህ በተጨማሪ ከሀገር ውስጥ ሆነ ከውጭ ያለውን የምሁራንን አቅም በማሰባሰብ የተሻለ የበይነ መረብ ደኅንነት ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል። ጎን ለጎን ደግሞ በአጫጭር ስልጠናዎች ለኅብረተሰቡ የግንዛቤ መፍጠሪያና ማዳበሪያ ኮርስ መስጠት ይገባል፡፡ይህ ሲሆን ነው አይበገሬ የበይነ መረብ አቅም ሊኖረን የሚችለው፡፡

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ